# ሌማት



ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ

# አቦዝ

ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ (ዶ/ር)

ግንቦት ፳፻፲፪ ዓ. ም.

© ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ 2012 ዓ.ም.
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::
ALL RIGHTS RESERVED

አድራሻ
ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ (ዶ/ር)

E-mail:- Emegua2015@gmail.com

ባሕር ዳር

ኢትዮጵያ

**ዋና አከፋፋይ:-**
ዝንጉ መጻሕፍት መደብር
0920187906/0920038480



**ይህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ**

እኔን ጨምሮ የበርካቶች የሙያ አባት
ለሆነው ለቅኑና ትጉሁ ሰው

ለፕሮፌሰር ደምል ተከታይ ፋንታ
ይሁንልኝ!

# ማውጫ


የጸሐፊው ማስታወሻ .......... 6

የኔ ፕሮፌሰር .......... 9

ደጉ አሳቢዬ .......... 23

አማኞቹ .......... 33

እኔ እና ዶ/ር ተወልደ ብርሃን .......... 39

ባለቁምጣው መሀንዲስ .......... 47

ሙሉ ዶሮ (Full Chicken) .......... 59

‹እኔ ብሞትም ሰርዶ ይብቀል› .......... 65

‹የተጣለው ቴፕ ሪኮርደር› .......... 83

ተስፋ አስቆራጩ መምህሬ .......... 91

ቢዝነስ ክላስ .......... 99

‹ዝም ብለህ ተናገር› .......... 105

የካሊፎርኒያው ጋባዤ .......... 113





የአስካሪስ ሕይወት .......... 123

‹እንዲህ ብለህ ጻፍ› .......... 129

ከታሪክ መማር .......... 133

‹ነገን መፍራት› .......... 139

ገራገሯ እናት በአሜሪካ .......... 143

‹የሥልጠናው አካል ነው› .......... 153

ፍሬ ከናፍር .......... 159

‹አልጨረስክልኝም› .......... 165

# የጸሐፊው ማስታወሻ

**ውድ አንባቢያን!**

ይህ ሥራዬ ከዚህ ቀደም ካቀረብኋቸው ሦስቱ መጻሕፍቶቼ በቅርጽም በይዘትም ይለያል። ቀደም ብለው ከአንባቢ የደረሱት ሦስቱ ሥራዎቼ በአንድ ጭብጥ ላይ ተመሥርተው መጀመሪያና መጨረሻ እንዲኖራቸው ሆነው የተዘጋጁ ነበሩ።

ይኸኛው ግን የተለያየ ርዕሰ ጉዳይ ያላቸውን ገጠመኞቼን አሰባስቦ የያዘ ነው። በቅርብ ለማገኛቸው ወዳጆቼ አንዳንድ ገጠመኞቼን እያነሳሁ ሳጫውታቸው ‹ለምን በመጽሐፍ





መልክ አዘጋጅተህ አታቀርባቸውም› የሚሉ ተደጋጋሚ ግፊቶችና ማበረታቻዎች ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ጉልበት እንደሆኑኝ መጥቀስ ተገቢ ነው።

በዚህ ‹ሰበዝ› ብዬ በሰየምኩት መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሃያ (20) የሚሆኑ ትንንሽ ታሪኮች በተለያዩ ጊዜያት ካገኘኋቸው አስገራሚ ሰዎች ከሰማሁት፣ ከጎበኘኋቸው ሀገራትና ካደረኳቸው ጉዞዎች ከተመለከትኩት፣ በኑሮዬና በሥራዬ ከገጠሙኝ ጉዳዮች በአእምሮዬ ተቀርጸው የቀሩትንና በማስታወሻዬም ከትቤ ካኖርኳቸው መካከል ትምህርት ይሆናሉ፣ ግንዛቤ ይፈጥራሉ፣ ያስገርማሉ፣ ዘና ያደርጋሉ ያልኳቸውን እንዲሁም ነቀራ መሰል ትዝብቶቼንና በተለያዩ መድረኮች ተጋብዤ ካደረኳቸው ንግግሮች መካከል መርጬ እንደ ሰበዝ አንድ ላይ ሰፍቼ አቅርቤያቸዋለሁ።

‹ሰበዝ› ማለት በሀገራችን መሶብ፣ አገልግል፣ ሰፌድና የመሳሰሉት ሲሠሩ በዐለላና አክርማ ወይም ክር አንድ በአንድ እየተሰካና እየተጠቀለለ የሚሰፋበትን ሳር ወይም ሰንደዶ ያመለክታል። ሳሮቹ እያንዳንዳቸው ትንንሽ ቢሆኑም አንድ ላይ ሲገመዱና ሲሰፉ ውብና ጠንካራ ቁስ ይፈጥራሉ። ምናልባት በዚህ መጽሐፍ የቀረቡት ትንንሽ ሐሳቦች ወደ ትልቅ ሐሳብ ሊያድጉ ይችሉ ወይም የመወያያ አጀንዳ መነሻ ይሆኑ ይሆናል። እናም ትወዱቸዋላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

በተረፈ የዕድሜና የጤና ባለቤት ፈጣሪ ጸጋውንና ብርታቱን ከሰጠኝ በጅምር ላይ ባለው አንድ ወጥ በሆነ ሥራዬ እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

**ሰላም**

**ዓለማየሁ ዋሴ**





# የኔ ፕሮፌሰር

እ.ኤ.አ. አቆጣጠር ከሜይ 2004 እስከ ሴፕቴምበር 2007 በአውሮፓ ኔዘርላንድስ ቫግኒንገን ዩኒቨርሲቲ የ3ኛ ዲግሪ ወይም የፒ ኤች ዲ ትምህርት ለመከታተል ተጉዤ ነበር። የማስተርስ ዲግሪዬን ከስዊድን የግብርና ዩኒቨርሲቲ ከጨረስኩ በኋላ አጭር በሚባል ጊዜ የተለመደውን የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ሂደት ሳልከተል በፕሮፌሰር ፍራንስ ቦንገረስ ግብዣ ነበር የተጓዝኩት። ለግብዣው መሠረታዊ ምክንያት የሆነው ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የሠራሁት የመመረቂያ ጽሑፍ (ቴሰስ) ነበር። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጥንታያው አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማትና አድባራት ተጠብቀው በኖሩት ደኖች ላይ ያደረኩት ጥናት ትኩረት የሳበ ስለነበረ ይመስለኛል።

ፕሮፌሰሩ ኢትዮጵያዊ ከነበረው ሌላኛው ፕሮፌሰሬ ጋር በመነጋገር ባሕር ዳር ድረስ መጥቶ ‹ለምን እኛ ጋ መጥተህ አትማርም? የጀመርከውን ጥናትስ ለምን ለዶክትሬት ዲግሪ አትቀጥለውም? ጥሩ ጥሩ ሐሳቦችን አንስተሃል፤ እኔ አመቻችለሁ› ብሎኝ ነበረ ወደ ኔዘርላንድስ ያቀናሁት።

ቫግኒንገን ዩኒቨርሲቲ ከገባሁ በኋላ ለጥናቱ የሚያስፈልጉኝን መሠረታዊ ኮርሶች ከተማርኩና የመስክ ምርምር ፕሮፖዛሌን ካዘጋጀሁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሼ የመስክ ሥራዬን አከናወንኩ።

ለሁለት ዓመት ያክል አድካሚ ነገር ግን አስደሳች የነበረውን የመስክ ጥናቴን ካጠናቀኩ በኋላ ያገኘሁትን መረጃ ለመተንተን ብሎም የዶክትሬት ዲግሪዬን ቴሰስ ለመጻፍ ተመልሼ ወደ ኒዘርላንድስ ተጓዝኩ። በሄድኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ልጽፋቸው ካሰብኳቸው ጽሑፎች ውስጥ አንደኛውን የጥናት ዘውግ የዳታ ትንተና ጨርሼ የመጀመሪያውን ረቂቅ ለፕሮፌሰሬ ሰጠሁት። በአዕምሮዬ ውስጥ ጥሩ መረጃ እንደሰበሰብኩ፣ ጥሩ ትንተና እንዳካሄድኩ እና ትንተናውን ተመርኩዤ በጥሩ ሁኔታ እንደጻፍኩት እርግጠኛ ነበርኩ። በጥቅሉ በራሴ ተግባር በጣም ተደስቼ ነበር። ፈረንጆቹ ኮምፕለሳንት (Complacent) የሚሉት ዓይነት ሰው ሆኜ ነበር ማለት ይቻላል። እናም ለፕሮፌሰሬ በጠዋት ሄጄ ‹የመጀመሪያውን ምዕራፍ ጽፌአለሁ። እየውና እርማት ካለህ ልቀበል ዝግጁ ነኝ› ብዬ ሰጠሁት። እንደ እውነቱ ከሆነ በወቅቱ የምጠብቀው አድናቆትን እንጅ እርማትን አልነበረም።





በሰጠሁት በሁለተኛው ቀን ጠራኝና ፈገግ ብሎ፡

“አይቸዋለሁ! መስተካከል ያለባቸው ነገሮች ስላሉ እነርሱን አስተካክል!” አለኝና ሰጠኝ። እኔም አልፎ አልፎ የፊደል እርማት ወይም ጥቃቅን ጉድለቶች ይሆናሉ ብዬ ገልጩ ሳላይ አመስግኜው ወደ ቢሮዬ ወረቀቱን ይዤ ሄድኩ።

ከቢሮዬ ደርሼ ገልጬ ሳዬው እኔ ከጻፍኩት መሳ ለመሳ የሚሆን በቀይ እስክርቢቶ እጅግ የበዛ እርማት፣ ብዙ የኤክስ ምልክት ያለው፣ ትልልቅ የጥያቄ ምልክት ያለው፣ እያከበበ እላዩ ላይ የጻፈው ነገር እጅግ የበዛና የሚያስደነግጥ ነበር። ከእኔ ጽሑፍ ይልቅ የእርሱ በቀይ እስክርቢቶ የተጻፈው ጎልቶ ይታይ ነበር። በቃ በቀይ እስክርቢቶ አበራይቶታል ማለት ይቀላል። ይህን ሳይ መጀመሪያ በጣም ተናደድኩ። ‹እንዴት ይህን ያክል እርማት አገኘለሁ? እንዴት እንዲህ እሳሳታለሁ እያልኩ ስለፈልፍ ቆየሁ። ቀጥሎ ቅስሜ ተሰበረ። በቃ በእጅጉ ተስፋ ቆረጥኩ።

‹ያን ያክል ሠርቼ ይህን ያክል ሂስና ትችት ከቀረበ እንዴት አድርጌ ነው ሌላውንስ የምቀጥል? ምን አጨናነቀኝ? ለምን ወደ ሀገሬ አልመለስም? ማስተርስ ዲግሪ አለኝ› እያልኩ ራሴን ለማጽናናት ሞከርኩ። በእውነቱ በወቅቱ የምሠራበት መ/ቤት የመምሪያ ሓላፊነት ደረጃም ደርሼ ነበር። ያን ሁሉ አገናዝቤ ‹ለምንድን ነው ይህን ያክል የምጨነቀው ተመልሼ አልሄድም እንዴ? የምን አባቱ ዶክትሬት ዲግሪ ነው› አልኩ።

በዚህ ብስጭት ከቢሮ ወጥቼ መኖሪያ አፓርትመንቴ ሄጀ ተኛሁ። በማግስቱም ቢሮ አልገባሁም። በሦስተኛው ቀንም ቀረሁ። ለካ ፕሮፌሰሬ አስተያየቱን (ኮመንቱን) እንዴት እንደተቀበልኩት ለማወቅ ፈልጎ ቢሮዬ እየተመላለሰ አጥቶኝ ኖሯል። በሦስተኛው ቀን ስቀርበት ስልክ ደወለልኝ።

"ለምንድን ነው ቢሮ ያልገባኸው?" አለኝ።

"አሞኝ ተኝቼ" አልኩት።

"ገብቶኛል! አሁኑኑ በፍጥነት ወደ ቢሮ ና" አለኝ ፈርጠም ብሎ።

እንደምንም እየተጨማደድኩ ወደ ግቢ ሄድኩና ቢሮው ጋ ስገባ ፈገግ ብሎ ፊት ለፊት ያለውን መቀመጫ እያመለከተ፡

"ቁጭ በል!" አለኝ ጠንከር ብሎ ፤ ቁጭ አልኩኝ።

"ሰሞኑን ቢሮ ያልገባኸው ለምን እንደሆነ ገብቶኛል" አለ ለዘብ ብሎ። በርግጥ ከቅዳሜና እሁድ ውጪ ከጠዋት እስከ ምሽት ከቢሮ የማልጠፋ ሰው ያለልማዴ መደዳውን ስጠፋ መታወቁ አይቀርም።

"የጻፍከውን በጥልቀት ስላየሁት ያን ያክል እርማትና ትችት በማግኘትህ ተበሳጭተህ ነው አይደል?" አለኝ። እኔም

"አዎን! ጥሩ ሥራ የሠራሁ መስሎኝ ነበር። አሁን ሳስበው ግን ያንተን ደረጃና ፍላጎት የማሟላ አልመሰለኝምና ተመልሼ





ወደ ሀገሬ ብሄድ ይሻላል ብዬ ነው" አልኩት። ጅላጅል መልስ ነበር።

ከት ብሎ ሳቀና እንዲህ አለኝ፡

(ይህ የተናገረኝ ቃል በቀሪ ዘመኔ ሁልጊዜ አብሮኝ ይኖራል።) "ስማ! በእኔና በአንተ መካከል የ20 ዓመት የፕሮፌሽን ወይም የሙያ ልዩነት አለን። አንተ አሁን ከተቀመጥክበት ወንበር እኔ የተቀመጥኩት የዛሬ 20 ዓመት ነበር። በ20 ዓመት ውስጥ ከአንተ በጣም ብዙ እርቄ እንደሄድኩ መገመት ነበረብህ" አለኝ።

20 ዓመት የሚለው የዶክትሬት ዲግሪውን ያገኘበት የእኔ እድሜ ላይ የነበረበትን አስቦ ነው። ቀጠለ

"እናም የ20 ዓመት ልዩነት ስላለን የፈለገ ብትሠራ፣ የፈለገ ብትጠነቀቅ እኔ ከማውቀው ደረጃ በዚህ ወቅት ልትደርስ አትችልም። ምክንያቱም ይህ እይታ በልምድና በእውቀት መዳበር የመጣ ስለሆነ የፈለግኸው ብትጽፍ እኔን ልታረካኝ አትችልም ወይም እኔ የማይበትን እይታ ሙሉ ለሙሉ ልታገኘው አትችልም። በጥልቀት አስበህ ብትጽፍ እንኳን ከአንተ ከፍ ያለ እይታ ስላለኝ ጎደሎውን ማየቴ አይቀርም።" ለዘብ ብሎ ስለሚናገር ልብ ይሰረስራል አእምሮ ይበረብራል።

ቀጠለ የቃላት መዶሻውን፡

“አንተ ካየህበት በላይ ካላሳየሁህ ምኑን አስተማርኩህ። አሁን ያለህ እውቀት ማደግ እንዳለበት ካላሳየሁህ ምኑን አሳወኩህ። በኔ ግምት ለማወቅ የሚችል ጭንቅላት፣ ለመማር የሚሆን አእምሮ ባለቤት እንጂ አዋቂ ለመባል ብዙ ይቀርሃል። እዛ ደረጃ ማድረስ ደግሞ የኔ ሥራ ነው።” አለና

“በዚህ የምትበሳጭ ከሆነ አዝናለሁ! የመጣኸው ለመማር ከሆነ እንዳስተምርህ ፍቀድልኝ። አይ በጥልቀት መማር አልፈልግም ካልክ አሁን የጻፍከው ለመመረቂያ በጣም በቂ ነው። እንደዚሁ አድርገህ ሌሎቹንም ጨርስና በአጭር ጊዜ አስመርቄህ ወደ ሀገርህ እልክሃለሁ!” አለኝ።

ተስፋ መቁረጤና ብስጭቴ ወደ ኃፍረት እየተለወጠ ሲመጣ ታወቀኝ። በራሴ አፈርኩ። እንደ እውነቱ ከሆነ በቀይ አስክርቢቶ ያበራየው ጽሑፌን ሳይሆን በልቤ ውስጥ የነበረውን አዋቂ ነኝ ባይ ትምክህቴን እንደነበር ተገለጠልኝ።

ቁጭ እንዳልኩ ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ።

በልቤ ‹በእውነት ለምን ነበር ወደ ተከበረው ዩኒቨርሲቲ የመጣሁት? ለካ ወደ አውሮፓ ያቀናሁት ለመተቸት፣ ለመታረም ሳይሆን ለመደነቅ ነበር?! ለማወቅ ሳይሆን ማወቄን ለማረጋገጥ ኖሯል። ለካ ወደ አውሮፓ ያቀናሁት ያወቅሁ የመሰለኝን ነገር በሚሰጡኝ ዲግሪ አባብዬ ውስጣዊ ባዶነቴን ተሸክሜ በባዶ ጉራ ለመኖር ኖሯል። በዶክትሬት ዲግሪ ተከልዬ በማይምነት ግርሻ ለመሰቃዬት ነበርና› አልኩና በእጅጉ በእራሴ አፈርኩ።





ቀጠለና እንዲህ አለኝ፡

“ከዛሬ ጀምሮ ምረጥ! አሁንም በደንብ እንዳይልህ የበለጠ ስል (ሻርፕ) እንዳደርግህ ከፈለግህ እርማት እንድሰጥህ ፍቀድ። በመሠረታዊነት የሠራኸው ጥሩ ነው። እንዲያውም አንድ ምሥጢር ልንገርህ” አለና “ እኔ የተማሪዎቼን ጽሑፍ በጥልቀት አይቼ እርማት የምሰጠው ተማሪዎቹ አቅም አላቸው ሊያሻሽሉት ይችላሉ ብዬ ሳስብ ብቻ ነው። አየህ መመረቅ ማለት ብዙ ደረጃ አለው። መሠረታዊ የሆነውን ማሟላትና ከመሠረታዊ ደረጃ ከፍ ያለ ደረጃ መድረስ የተለያዩ ናቸው። አቅም አለህ ብዬ ስለገመትኩ ጽሑፉም ሥራህም ከፍ ማለት የሚችል መሆኑን ስላመንኩ በጥልቀት አይቸዋለሁ። ሊያስደስትህ እንጅ ሊያሳዝንህ አይገባም” አለኝ።

በራሴ ማፈሬንና በጣም ማዘኔን ገልጬ “በጣም ይቅርታ አድርግልኝ” አልኩት ከልቤ።

ወጥቼ ሂጄ የሰጠኝን አስተያየቶችና ትችቶች አዕምሮዬን ከፍቼ ሳይ ምን ያክል ጽሑፉን ሊያሳድገው እንደሚችል እኔንም ሊያስተምረኝ እንደሚችል ተገነዘብኩ።

በሌላ ጊዜ ያደረገው ደግሞ እጅግ የሚገርም ነው። ሦስተኛውን የጥናት ዘውግ ምዕራፍ ስጽፍ አንድ የኮምፒውተር ፕሮግራም መጠቀም ነበረብኝ። ይህ የኮምፒውተር ፕሮግራም የብዝሃ-ሕይዎት ትንተና (አናሊስስ) መሥሪያ ሲሆን እንደተለመደው የሚያስፈልጉ መረጃዎች ከገቡለት እና አስፈላዎቹ ቁልፎች ከተጫኑ ኮምፒውተሩ መረጃውን ተንትኖ የትንተናውን ውጤት ያስቀምጣል። ያስቀመጠውን ውጤት ይዞ መጻፍ ብቻ ነው። ይህን በሚገባ ችዬ ነበር።

አቋራጭ የእውቀት መንገድ የማይወደው ፕሮፌሰሬ ግን፡

“ኮምፒውተሩ የሚሠራበትን የትንተና መርህ ካላወቅኸው አውጥቶ የሰጠህን ቁጥር ብቻ ይዘህ ብትጽፈው እውቀት አታገኝም። ስለዚህ ኮምፒውተሩ የሚሠራበትን መርህ መረዳት መቻል አለብህ!” አለኝ።

ይህም ምን ማለት ነው? በቆሎ ወደ ወፍጮ ቤት የምንወስደው የበቆሎውን ዱቄት ፈልገን ነው። ወፍጮው እንዴት እንደፈጨው ማወቅ አያስጨንቀንም። በመኪና ተሳፍሮ መሄድንና ካሰብንበት መድረሳችንን እንጂ መኪናው በምን ስልትና መርህ እንደሚሽከረከር ለማወቅ ደንታ የለንም። ይህ ፕሮፌሰር እያለኝ ያለው ግን “በቆሎውን አስገብቶ ዱቄቱን መውሰድ ብቻ ሳይሆን ወፍጮው እንዴት እንደሚፈጨው ማወቅ አለብህ ነው። ምክንያቱም ያ ነው የሳይንስ ሰው የሚያደርግህ ” ነው።





በዚህ መሠረት ባቅራቢያው ካለ ሌላ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚሠራ በዚህ ሙያ የተካነ ፕሮፌሰር ዘንድ ሄጄ እንድማር ጠየቀኝ። ሰነፉና ወስላታው አእምሮዬ እያጉረመረመ ሄድኩኝ። እጅግ የጠለቀ የስታትስቲክስ ትንታኔና ስሌት በሚገርም ሁኔታ ይተነትንልኝ ጀመር። ሳይንሱ እንዴት ወደዛ ሊደርስ እንደቻለ ቁጥሮቹ ኮምፒውተሩ ሲያወጣቸው የሚሰጡት ትርጉም ምን ተቀምሮ፣ ምን ተደምሮና ተቀንሶ፣ ምን ማለት እንደሆነ ጭምር ነው በተመስጥኦ የሚተነትንልኝ። በመካከል እኔ ሰለቸሁ፣ ጨርሶ የሚገባኝም አልመሰልህ አለኝ። ከፕሮፌሰሩ ጋር አራት ሰዓታት ያክል አሳለፍኩ። ለራሴ፡

“እኔ ምን አንደዚህ እንደ መጫኛ ከረዘመ ስታትስቲክስ ጋር አዳረቀኝ፤ ዱቄቱን ካገኘሁ እንዴት እንደሚፈጭ ለመረዳት ምን አስጨነቀኝ? ዱቄቱን ይዤ መተንተንና ያንን ጽፎ በጊዜ መመረቅ ነው” አልኩና፡ ወዲያው አንድ ዘዴ መጣልኝ።

“ፕሮፌሰር አሁን ገብቶኛል” አልኩት።

“እርግጠኛ ነህ?” አለኝ እየተጠራጠረ።

“እንዴ በጣም ገብቶኛል አመሰግናለሁ” አልኩት ፈርጠም ብዬ። አከታተልኩና

“ከዚህ የበለጠ ጊዜህን አልወስድብህም በጣም ደስ ብሎኛል” አልኩት።

ከፊቱ ላይ የመጠራጠር ስሜት እያሳዬ "ከገባህ መልካም ነው፤ እ.. ካልገባህ ግን የፈለከውን ያክል ጊዜ ልስጥህ እችላለሁ፣ ብዙ አትጨነቅ" አለኝ።

"በደንብ ገብቶኛል አትቸገር" አልኩትና ወደ ዩኒቨርሲቲዩ ተመለስኩ።

እኔ መንገድ ላይ እያለሁ ይህ ፕሮፌሰር ለእኔ ፕሮፌሰር ይደውልና፡

"ተማሪህ ከእኔ ጋ ቆይቶ ሄዷል። እኔ ስገምት የገባው አልመሰለኝም እርሱ ግን ገብቶኛል ብሏል።" ብሎ ይነግረዋል።

ቢሮ እንደገባሁ ፕሮፌሰሬ መጣና፡

"መጣህ እንዴ? እንዴት ነው በደንብ ተረዳኸው?" አለኝ።

"አዎ ተረድቸዋለሁ አሁን ሥራዬን ልቀጥል ነው" አልኩት።

ፈገግ ብሎ እንዲህ አለ፡

"ይገርማል! እኔ ብዙ ጊዜ አጥፍቼ እስካሁን መረዳት አልቻልኩም። እስኪ አባክህ አስረዳኝ" አለና ወንበር ስቦ ከጎኔ ቁጭ አለ። ጉድ ፈላ! ያልገባኝን ነገር ለማስረዳት መሞከር ምን ያክል ፈተና እንደሆነ መገመት አይከብድም። ከየት ላምጣው?!

በፈገግታ በታጀበ ጠንካራ ድምጸት





"ቀጥ ብለህ ተመልሰህ ሂድ! እኔን ማስረዳት እስክትችል ድረስ ተመልሰህ እንዳትመጣ! (Go back! Don't come back till you are able to teach me!)" አለኝና ከቢሮዬ ወጥቶ ሄደ።

ተጣሞ ያደገውን ልቤን፣ ስነፉን አእምሮዬን በደንብ ያወቀው መምህሬ ትዕዛዝ ስለሆነ እየተሸማቀቅኩ ድንቁርናዬን ተሸክሜ ወደዛኛው ፕሮፌሰር ተመልሼ መሄድ ግዴታዬ ሆነ። በእውነቱ ሀፍረቴ ወሰን አልነበረውም።

ፕሮፌሰሩ ሲያዩኝ ሀፍረቴን በሚጨምር ሳይሆን በሚቀንስ ሁኔታ፡

"ምንም አይደለም እኮ! ውስብስብ ስለሆነብህ አይገባኝም ብለህ ስላሰብህ በተስፋ መቁረጥ ያደረከው እንደሆነ እረዳለሁ። በከፊል የኔም ችግር ነው" ሲል ጭራሽ ትህትናው መሬት አስገባኝ። ቀጠለና

"አሁን ለማወቅ ወስንና ተረጋጋ። እስኪገባህ የፈለከውን ያክል ጊዜ መውሰድ ትችላለህ" አለና አደፋፈረኝ።

ሳይገባኝ መመለስ እንደማልችል ሳውቅ አዕምሮዬን ክፍት አድርጌ በአግባቡ ለመረዳት ወሰንኩ። ከእንጨት ወይም ከድንጋይ አልተሠራሁምና፣ ሰው ነኝና ከሁለት ቀን በኋላ ጥንቅቅ አድርጌ ለማወቅ ቻልኩ።

ሕይወት አጭር ናት። ከነዚሁ ደግሞ በአቋራጭ ተጉዘን የበለጠ ለምን እንደምናሳጥረው አይገባኝም።

በደንብ መረዳቴን ሳውቅ ሌላኛው በሽታዬ ደግሞ ተቀሰቀሰ። የአዋቂ ነኝ ባይ እብሪት። ‹እስከ ዛሬ ድረስ እኮ እኔ አልገባኝም› ያለኝን ፕሮፌሰሬን ለማስተማር በኩራት ወደ ዩኒቨርሲቲዬ ተመለስኩ። በጠዋት ስሄድ ቢሮው ቁጭ ብሎ እንደተለመደው የተማሪዎችን ጽሑፍ ያነባል። ገና ሲያየኝ፡

"መጣህ?" አለኝ

"አዎን መጥቻለሁ" አልኩኝ በኩራት።

"እንዴት ነበር?" አለኝ ፈገግ ብሎ።

"በደንብ ገብቶኛል። እንዲያውም ላስረዳህ ነው የመጣሁት" አልኩና ወንበር ስቤ ከጎኑ ቁጭ ልልስል፡

"I already know it long time ago ! (እኔ እኮ ገና ዱሮ ነው የማውቀው!)" አለኝ እየሳቀ።

"ታዲያ በቀደም ለምን አስረዳኝ አልከኝ?" አልኩት ብሽቅ ብዬ

"That is how you teach your student!" አለኝ። "እንደዛ አድርገህ ነው ተማሪህን የምታስተምር" እንደማለት ነው።

‹ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች› የተባለው በእኔ ደረሰ ማለት ነው።





ይህ ፕሮፌሰሬ እውቀት እንድራብ፣ ምንጊዜም አለማወቄን እንዳውቅ እጅግ ከፍ ያለ ተጽዕኖ እንዳደረገብኝ ይሰማኛል። ዛሬ ድረስ ባልገባኝ ነገር የገባኝ መስዬ እንዳልታይ፣ አወቅኩ ብዬ እንዳልኮፈስ በአዕምሮዬ ታትሞ ይኖራል ፕሮፌሰር ፍራንስ ቦንገርስ!! እንዲያውም ከትምህርት ያመለጠው ድንቁርናዬ ሲያገረሽ፣ ያልታረመው ክፉ ጠባዬ ድንገት ሲገለጥ ፕሮፌሰሬ ትዝ ይለኝና ‹ምነው ይህንኔንም አርመህልኝ በነበር!› እላለሁ።

ለማንኛውም እንዲህ የተጣመመ ልብ የሚያቃኑ፣ ሰነፍ አእምሮን የሚያበረታቱ መምህራንን ማግኘት የሎቶሪ ዕጣ ያክል እድሉ ትንሽ ነው። ሲገኙ ግን ለትውልድ ህመም ፈዋሽ መድኃኒት ናቸው!!

# ደጉ አሳቢዬ

የድህረ ምረቃ ትምህርቴን በምከታተልበት ወቅት ለዚሁ ማሟያ እንዲሆን የመስክ ምርምር ስሠራ ከገጠሙኝ ነገሮች ሁሉ የማልረሳቸው አሉ። ገጠመኞቼን ከመናገሬ በፊት የምርምር ሥራዎቹ ምን ምን እንደነበሩ ለአንባቢ ጠቅለል አድርጌ ማስቀመጡ ታሪኩን ለመረዳት ያግዛል ብዬ አምናለሁ። በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል እንደሚታወቀው አብዛኛው የተፈጥሮ ደን ተራቁቶ ሲያልቅ በጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ዙሪያ ግን እነዚህ ደኖች ተጠብቀው ዘመናትን መዝለቅ ችለዋል። ወደ ሰሜን ላቀና ተጓዥ እንደነዚህ ዓይነት አገር በቀል ደኖችን አንድ አካባቢ ካዬ በመካከሉ ቤተ ክርስቲያን ወይም ገዳም ለመኖሩ እርግጠኛ መሆን ይችላል።

እነዚህ ደኖች ለዘመናት ተጠብቀው የቆዩበት ምሥጢር ሕዝቡ ለቤተ ክርስቲያኑ ካለው ክብር የመነጨና ቤተ ክርስቲያኗም ጥንቁቅና ምልዑ የሆነ የተፈጥሮ ሐብት ጥበቃ አስተምህሮ ስላላት እንደሆነ ይታወቃል። በአጠቃላይ የጸሎትና የአርምሞ፣ የምናኔ፣ የቅዱሳን መናሀሪያ፣ የትምህርትና የእውቀት ስፍራዎች፣ ክርስቲያኖች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የሚያርፉበት መካነ መቃብር በመሆናቸው ኅብረተሰቡ የሚያከብራቸው ናቸው። እነዚህን ደኖች ጠጋ ብሎ ላስተዋላቸው ሰው ለዘመናት የቆዩትን ያክል ወደፊትስ በዚህ ሁኔታ ይቀጥላሉ ወይ ብሎ ማሰቡም የማይቀር ነው። ዋናው የምርምር ሥራዬ የሚያተኩረውም በዚህ ዙሪያ ነበር።

በዚህ መሠረት በርካታ ደኖችን እየተዘዋወርኩ ሳጠና አብዛኛዎቹ ደኖች የብቅለት ችግር ያለባቸው ወይም ዘር ችግኝ ሆኖ ችግኙ ዛፍ ሆኖ የሚተካ ለመሆን የሚችልበት ምቹ ሁኔታ የሌለበት መሆኑን ተገንዝቤ ነበር። በአብዛኛው ደኖቹ ከውጭ የሚታዩት ያረጁ ዛፎች ስብስብ እንጅ በችግኝ ደረጃ ተስፋ የሚሆን ተተኪ እንደሌላቸው ለመረዳት ችያለሁ። ስለሆነም የእነዚህ የቤተ ክርስቲያንና ገዳማት ደኖች የወደፊት እጣ ፋንታ የሚወሰነው ከታች በሚያድጉትና በሚተኩት ቡቃያዎችና ችግኞች በመሆኑ በቂ ቡቃያና ችግኝ ያለመኖሩ ምሥጢር ምንድን ነው? የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ነው።

ይህ ጥናት በሁለት መላ ምት ተከፍሎ የሚታይ ሲሆን አንደኛው ዘርፍ የልቅ የቤት እንስሳት ግጦሽ መኖሩ፣ በተደጋጋሚ ለመካነ መቃብር ስለሚውሉ እና ሐውልትና





ቤቶች ስለሚገነቡባቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ዛፎቹ በተፈጥሮ ዘር የመስጠትና ዘሮቹም የብቅለት ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል በሚል የሚደርግ ጥናት የሚመለከት ይሆናል።

በሁለተኛው መላምት ስር የተፈጥሮ /Biological and natural/ የብቅለት ችግር ከምን ይመነጫል? የሚለውን ለማወቅ ወይም ለመረዳት የዛፎቹን የተፈጥሮ እድገት ዑደት መከተል ይጠይቅ ነበር። በዚህ መሠረት አንድ ዛፍ ያብባል፣ ፍሬ ይሰጣል፣ ፍሬው ወደ መሬት ይረግፋል፣ መሬት ላይ ከረገፈ በኋላ ግማሹ ይበቅላል፣ በቅሎ ችግኝ ሆኖ መልሶ ዛፍ ይሆናል። የቀረው ደግሞ መሬት ውስጥ አፈር ውስጥ ተቀብሮ ምቹ ዘመን ይጠብቃል። በመካከል ዘሩ ዛፉ ላይም ሆኖና መሬትም ከደረሰ በኋላ በእንስሳት ሊበላ ይችላል። እንግዲህ የብቅለትን ችግር ለመረዳት ይህን ዑደት እየተከተሉ ማጥናት ግድ ይላል። ለምሳሌ በበቂ መጠን ያብባሉ ወይ? የሚያብቡት መቼ ነው? አብበው ሲያበቁስ ያፈራሉ ወይ? ያፈሩት ዘርስ ብዛቱ ምን ያክል ይሆናል? መብቀል የሚችል ዘር ነው ወይ? ይሄ ከሆነ በኋላ መሬት ላይ ካረፈ በኋላ ዘሩ ምን ይገጥመዋል? እንስሳት ይበሉታል ወይስ ወደ አፈር ገብቶ ይቀበራል? ወይስ ይበቅላል ወይ? ከበቀለ ደግሞ ችግኝ ለመሆን ምን ችግር ይገጥመዋል? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ የጥናት ሥራዬ ዋና ተግባራት ነበሩ።

እና በዚህ ጥናት አንዱ ገጠመኝ ብዬ የማስታውሰው ዛፎቹ አብበው ፍሬ ከሰጡ በኋላ የፍሬው ብዛት ምን ያክል ነው? የፍሬው ዓይነትስ መብቀል የሚችል (Viable) ነው ወይ? የሚለውን የሚመልስ Phenology And Seed Rain Analysis የሚባለውን የጥናት ዘርፍ ሳከናውን ነበር። ይህም የዛፎች አበባ ዘር ማፍራቱንና ወደ መሬት መራገፉን (እንደ ዝናብ ከላይ የሚወርድ ስለሆነ seed rain ይባላል) ለማወቅ ነው። ይህን ለማጥናት ዛፎቹ የሚያብቡበትን ጊዜ ከመመዝገብና ማበባቸውን ከማወቅ በተጨማሪ ዘር በሚሰጡበት ጊዜ በደኑ ውስጥ የተለያዩ ቦታዎች በጥናት በተመረጡ እና በዘዴ በተቀመጡ የ50 ሳ.ሜ ዲያሜትር ስፋት ያላቸው ከአቡጀዲ ጨርቅ የተሠሩ ከረጢቶች በክብ መልክ ተዘጋጅተው ይቀመጣሉ። ስለዚህ ዛፉ አፍርቶ ሲያረግፍ ዘሩ ልክ ወደ መሬት በሚወድቅበት ዓይነት እነዚህ ከረጢቶች ውስጥ ይገባል።

ከረጢቶቹ ውስጥ የገባው ዘር በየሳምንቱ ለአንድ ዓመት እየተወሰደ የዘር ዓይነትና ብዛት፣ የረገፈበት ወቅት፣ እንደዚሁም ወደ ላቦራቶሪ ተወስዶ መብቀል አለመብቀሉ እየታዬ ይመዘገባል። በከረጢቱ አፍ ስፋት አንፃር ጠቅላላው ደኑ ውስጥ ምን ያክል ዘር ሊመረት እንደሚችል በዓመቱ መጨረሻ መገመት ያስችላል። በዚህ መሠረት ያ ደን በሌላ አገር ከተጠናው፣ በሳይንስ ከሚገመተውና ማምረት ከሚገባው የዘር መጠን ጋር ይተያይና ዛፎቹ በቂና ጤነኛ ዘር ያመርታሉ ወይስ አያመርቱም የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ያስችላል።





እግረ መንገዱንም የዛፎቹ ቅርንጫፍ፣ ቅጠላቅጠል እየረገፈ ከረጢቱ ውስጥ የሚገባውን ወስዶ ደግሞ ዛፎቹ ሲያረጁ ቅጠሎቹ ወደ መሬት ሲረግፉ የሚመጣውን ንጥረ ነገር እና ዑደት (Nutrient Cycling) ለመረዳት ያስችላል።

ይህን ጥናት ለማድረግ በስምንት አብያተ ክርስቲያናት ቁጥራቸው የታወቀ ከረጢቶችን በስርዓት አስቀምጬ በየሳምንቱ እየተመላለስኩ ከረጢት ውስጥ የገባውን እየገለበጥኩ ወደ ላቦራቶሪ እየወሰድኩ አንድ ዓመት ሙሉ መሥራት ነበረብኝ። አንዳንዱ ከረጢት ባዶውን ሊገኝ ይችላል። ያ ግን የምርምሩ አካል እንጂ ችግር አይደለም።

ከስምንቱ ጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናት በአንዱ የአብነት ተማሪዎች የሚማሩትና የሚያስተምሩት ደኑ/ጫካው ውስጥ ስለነበረ ምናልባት ከውጭ ሰው መጥቶ ከረጢቶቹን እንዳይወስዳቸው ተማሪዎቹ እንዲከታተሉልኝ መርጌታውን አደራ ብዬ ተስማምተን ሄድኩኝ።

መርጌታውን ስለምርምሩ በበቂ መጠን አላስረዳኋቸውም ነበር። ብቻ በየሳምንቱ እየመጣሁ ዘሩን እንደምወስድ ነግሬአቸዋለሁ። በዚህ መሠረት አንድ ወር ያክል በየሳምንቱ እየሄድኩኝ ዘሩን እየገለበጥኩ ስመለስ ይመለከታሉ። እኔም ሰላም እላቸዋለሁ እሳቸውም ሰላም እያሉኝ ከረጢቶቹን ስገለብጥ ያያሉ። አንድ ቀን፣

"እንዲያው እንደዚህ ዓመት ሙሉ እየተመላለስክ ትዘልቀዋለህ?" አሉኝ በሐዘኔታ

"አዎ አንድ ዓመት እመላለሳለሁ። ከዚህ ከረጢት ውስጥ የገባውን ዘር ስለምፈልግ በየሳምንቱ መምጣቴ ግዴታ ነው" አልኳቸው።

በዚህ መሠረት አንድ ሁለት ወር ተመላለስኩኝ። ስምንት ጊዜ ማለት ነው። በዘጠነኛው እንደተለመደው ከረጢቱ ውስጥ የገባውን ዘርና ቅጠላቅጠል ለመገልበጥ ስሄድ ደኑ ውስጥ ያስቀመጥኳቸው ከረጢቶች በሙሉ ከአፍ እስከ ገደፋቸው በዘር እና በቅጠል ተሞልተዋል። ይሕ ለእኔ የሚገመትም የሚጠበቅም አልነበረም። ምክንያቱም ያን ያክል በከረጢቱ የሚሞላ ዘር የሚገኝ ከሆነ ተአምር እንደማለት ነውና በጣም ተደንቄ ‹ይሄ ሊሆን አይችልም? እንዴት ይህን ያክል ዘርና ቅጠል በሳምንት ይረግፋል? እያልኩ ከራሴ ጋር በጥያቄ ስፋጠጥ ድምጼን ሰምተውኝ ኖሮ እኒህ መርጌታ ተማሪዎቻቸውን አስከትለው መጡ።

ሰላምታ ከሰጡኝ በኋላ መገረሜን ሲያዩ "ምነው?" አሉኝ።

"አይ ደንቆኝ ነው። ይህን ያክል ዘር እንዴት ተገኘ ብዬ እያሰብኩ ነው" ስላቸው፡

"እ.. ነው?" አሉና "እኔማ እንዲያው በየሳምንቱ መንከራተትህ ሲያሳዝነኝ ጊዜ ለምን እኛ እንሰበስብለትም ብዬ ተማሪዎችን





በየዛፉ አሰማርቼ ሸምጥጠን ከመሬት ያለውንም እያፈስን እኛ ሞልተንልህ እኮ ነው" አሉኝ።

ይህን ስሰማ ብው አልኩ። ለወዲያው የምይዘውን የምጨብጠውን አጣሁ። ምክንያቱም ያዚያን ሳምንት ምርምር አውጥቼ መድፋት ስለሚኖርብኝ ነው። የዛን ሳምንት መረጃ ለማግኘት ደግሞ በሚቀጥለው ዓመት በዛችው ወቅት መጠበቅ ሊኖርብኝ ነው። ወይም ሁለተኛው ደካማ አማራጭ የዚህን ሳምንት መረጃ መተው ይሆናል። ለማንኛውም በምርምሬ ሥራ ላይ ትልቅ ጥፋት፣ ትልቅ በደል ነበር።

እርሳቸውም ቀጠል አደረጉና፡

"መቼም የሚበቃህ ይመስለኛል ተንግዲህ አትመላለስም " አሉኝ።

እሳቸው በደግነታቸው ለእኔ ያደረጉት እርዳታ የእኔን የምርምር ሥራ የሚያጠፋና የሚያወድም እንደሆነ አልተረዱትም ነበር። ተግባራቸው ለእኔ ጥፋት እንደሆነ ብረዳም ይህን ያደረጉት ደግሞ እኔን ለማገዝ ለእኔ ባላቸው ሐዘኔታ በመሆኑ የእሳቸው ደግነትና የምርምር ሥራዬ ላይ የደረሰው ጥፋት አንድ ላይ አዕምሮዬ ውስጥ ገብቶ ጭንቅላቴን ናጠው።

"‹በዓለም ላይ ትልልቅ ጥፋቶች የተፈጸሙት በጎ ሐሳብ ባላቸው ሰዎች ነው› የሚባለው ለዚህ ይሆን? በጎና ቅን ሐሳብ በዕውቀት፣ በጥበብና አርቆ በማዬት ካልታሰበ መጨረሻው ጥፋት ሊሆን ይችላል። ወደ ገሃነም የሚወስደው መንገድ

በቅንነትና በየዋህነት የተገነባ ነው የሚባለው ለዚህ ነው" እያልኩ ብዙ ተብሰከሰኩ።

ሰከን ብዬ ሳስብ ደግሞ በትንከል ከመነጨው ‹የይሁዳ መሳም› ይልቅ በቅንነት የሆነው ‹የሙሴ መግደል› ይሻላል የሚለው አባባል ሞገተኝ።

እንዲያውም ኢማኑኤል ካንት የተባለው ፈላስፋ ስለ ደግነትና ሞራሊቲ ሲገልጽ፡

"ደግነትና ሞራሊቲ የሚለካው በሚያመጣው ወይም በሚያስከትለው ውጤት ሳይሆን ድርጊቱ በተፈጸመበት መንፈስ ብቻ ነው! በጎ ሐሳብ ውጤት ባይኖረው እንኳን እንደ እንቁ ያበራል። በጎ ሐሳብ በራሱ መልካም ነውና።

Moral worth of an action depends on motive. A good will isn't good because of what it effects or accomplishes, it's good in itself. Evenif by atmost effort the good will accomplishes nothing it would still shine like a jewel for its own sake as something which has its full value in itself" ይላል።

እንደ ካንት አባባል በበጎ የታሳበን፡ መጥፎ ውጤት አያባላሸውም፤ በሌላ በኩል መጥፎ እሳቤን፡ መልካም ውጤት አያስተካክለውም ነው። ምሳሌ ሲሰጥ፡





"አንድ ባለሱቅ በርካሽ የሚሸጥን እቃ ተመሳሳይ ከሆነና በውድ ከሚሸጥ ዕቃ ጋር ቀላቅሎ ለመሸጥ አስቦ ‹ድንገት ደንበኞቼ ዕቃውን ለይተው ቢያውቁት ለወደፊቱ ደንበኝነታቸውን ያቋርጡብኝና ገቢዬ ይቀንሳል› ብሎ ማጭበርበሩን ቢተወው የተወበት ምክንያት ከራስ ወዳድነት አንጻር በመሆኑ ውጤቱ መልካም ቢሆንም አያስመሰግነውም" ይላል።

ተረጋግቼ ይህን ሁሉ ሳስበው ከእርሳቸው ደግነት የሚበልጥ ጉዳይ እንደሌለኝ ተረዳሁና መቀየሜን ተውኩት። ራሴን እንደምንም አረጋጋሁና የምፈልገው ዝም ብሎ ዘር ብቻ ሳይሆን እራሱ በተፈጥሮ የሚገባውን እንደሆነ ለወደፊቱ እንዲያ እንዳያደርጉ የምርምሩን ሐሳብ አስረዳኋቸሁ። በዚህ ሂደት የራሴ ጥፋት ወለል ብሎ ታየኝ። ይህን ገለጻ ቀደም ብዬ ማድረግ ነበረብኝ። የሀገራችን ተመራማሪዎች የተለመደ ተራ ስህተት ነበር። እርሳቸውም ሁኔታውን ሲረዱ በአድራጎታቸው ተጸጽተው "አላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል ማለት ይኼ አይደል?" አሉኝ ደጉ መርጌታ!

# አጣጮቹ

ሁለተኛው የምርምር ገጠመኝ በመሬት ውስጥ የተከማቸን ዘር የሚመለከት ምርምር ላይ ነበር። የዕጽዋት ዘር ከእናት ዛፍ ወደ መሬት ከረገፈ በኋላ አራት እጣ ፈንታዎች ይኖሩታል። እነርሱም መብቀል፣ በእንስሳት መበላት፣ ወደ ሌላ ቦታ መወሰድ እና እዛው አካባቢ መሬት ውስጥ መቀበር ይሆናል። መሬት/አፈር ውስጥ በተለያየ ምክንያት ዘር ሊቀበር ይችላል። ይኸውም በተሰነጣጠቀና ክፍት በሆነ የመሬት ቀዳዳ ተንሸራቶ በመግባት፣ እንስሳት ሲራመዱ ሲጫኑት፣ መሬት ውስጥ የሚኖሩ እንስሳትና ነፍሳት ለምሳሌ አይጦች ለምግብነት ወደ ጉድጓዳቸው አከማችተውት በዚያው ሲቀርና በመሳሰሉት ሲሆን ይህ የዘመናት የዘር ክምችት የአፈር የዘር ባንክ (Soil Seed Bank) ይባላል።

በአፈሩ ውስጥ ምን ያክል ዘር ተከማችቷል? ከመሬት በላይ አሁን በዛፍ ደረጃ ያለው አርጅቶ ቢወድቅ እና መሬቱ ቢራቆት ከመሬት ውስጥ የተቀበረው ዘር በቅሎ መተካት ይችላል ወይ? ለመሆኑ መሬት ውስጥ የተከማቹት ዘሮች ዝርያ አሁን በቁጥቋጦና በዛፍ ደረጃ ካሉት ጋር ይመሳሰላሉ? ካልተመሳሰሉስ በዘመን ሂደት ምን የዕጽዋት ስብጥር ለውጥ መጣ? የሚለውን ጥያቄ የሚመልሰው ደግሞ የአፈር የዘር ባንክ ጥናት (Soil Seed Bank Analysis) ይባላል። የአፈር ዘር ባንክ በደንና ዕጽዋት ዓለም እንደ ቤተ መዘክር ሆነው ያገለግላሉ።

ይህን ጥናት ለማካሄድ ስምንት አብያተ ክርስቲያናትን መርጬ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ደን ውስጥ በአስር የተለያዩ ቦታዎች አስር በአስር ሳንቲ ሜትር ስፋት ላይ በሦስት የጥልቀት ደረጃ (ከ0 እስከ 3፣ ከ3 እስከ 6፣ ከ6 እስከ 9 ሳንቲ ሜትር) ያለው አፈር በጥንቃቄ ቆፍሮ በማውጣት ለየራሱ በፕላስቲክ በማስቀመጥ ወደ ላቦራቶሪ ወስዶ በመመርመር የሚሠራ ነበር።

ላቦራቶሪ ተወስዶ ሲሠራ አፈሩ በተለያዩ ቀዳዳ ስፋት ባላቸው ወንፊቶች ይነፋና በዓይን የሚታዩት ዘሮች ተለቅመው ይለያሉ። በዓይን የሚታዩት ዘሮች ከተለዩ በኋላ መብቀል አለመብቀላቸውን የብቅለት ሙከራ ይደረግላቸዋል። ቀሪው አፈር ደግሞ በዓይን የማይታይ ዘር ሊኖረው ስለሚችል በሳህን ይደረግና በፕላስቲክ ከተሸፈነ ቤት (ግሪን ሃውስ) ውስጥ ውኃ እየጠጣ የሚበቅለው ነገር እየታዬ ይመዘገባል።





(ምክንያቱም ከበቀለ የዛፍም ይሁን የቁጥቋጦ ወይም የሳር ዓይነት መለየት ስለሚቻል ምን ዓይነት እፅዋት ከርሰ ምድር ውስጥ እንዳለ ለመረዳት የሚያስችል ጥናት ነው። )

ይህን ጥናት ወደ ማድርግባቸው አብያተ ክርስቲያናት ይዞኝ የሄደው ሾፌር በአጋጣሚ ፊቱ አካባቢ የቆዳ በሽታ ያለበት ነበር። በአንደኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እኔ ጫካ ውስጥ ይህንን አፈር ለመቆፈር ስዘዋወር ከዛ ያሉ አባቶች ያዩትና የሚቀባው ነገር ይሰጡታል። ከቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ግድግዳ ላይ ካለ ሽንቁር ገብተው ማር የሚሠሩ ንቦች አሉ። የንብ ቀፎ ማለት ነው። ግን ከቤተ ክርስቲያኑ ግድግዳ ላይ ከጣራው ዝቅ ብሎ ነው። ማሩ ከቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ ካለው አፈር ጋር ተለውሶ ለብዙ ምዕመናን መድኃኒት ሆኖ ያገለግላል። እና እነዚህ አባቶች ለዚህ ሾፌር ይነግሩትና ማሩን ከአፈሩ ጋር እየቀላቀለ ፊቱን ይቀባል:: እኔ የደኑን ስብጥር አጥንቼና አፈሩን ቆፍሬ ለመጨረስ ቢያንስ ለ3 ቀናት ያክል መቆየት ስለነበረብኝ በጣም በሚደንቅ ሁኔታ በ3 ቀናት ውስጥ የዚህ ሹፌር ገጽታ ተለወጠ፣ የፊቱ ማዲያትና ቁስለት ሙሉ በሙሉ ዳነ። በዚህ እየተደሰተ ሥራችንን ጨርሰን ሁሉም ቦታ ተዘዋውረን ወደ ሁለት ኩንታል የሚሆን አፈር ተሸክመን ወደ አዲስ አበባ ተመለስን። አዲስ አበባ የምርምር ሥራዬን ለመቀጠል የላቦራቶሪና ግሪን ሃውስ አገልግሎት ወደ ማገኝበት የምርምር ተቋም ሄድኩኝ። ከምርምር ተቋሙ አካባቢ ያሉ ልምድ ያላቸውን ሴቶች ቀጠርኩኝ። በተለያዩ ወንፊት እየነፋ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ስም ባስቀመጥኩላቸው

መሠረት ዘሮቹን እየለዩ ያስቀምጣሉ። የተረፈውን አፈርም መልሰው ቋጥረው ለሚቀጥለው ጥናት እንዲሆን እንዲያደርጉ ተስማምተን ነበር።

በዚህ መልክ ሥራው በጥሩ ሁኔታ እየሄደ እያለ አብዛኛውን የቤተ ክርስቲያኖች ናሙና ጨርሰው የመጨረሻውን ቤተ ክርስቲያን ሲሠሩ ሹፌሩ የቤተ ክርስቲያኑን ስም ሲያይ እግረመንገዱን የእሱን ፊት መዳን ምሥጢር ይነግራቸዋል። ከዚህ በኋላ የተፈጠረው የሚገርም ነበር። ከቀናት በኋላ ተመልሼ ሄጄ ሳይ የዚህ ቤተ ክርስቲያን አፈር ግማሹ የለም። ከመጣው በእጅጉ ጎሏል። የሌሎቹ ግን እንዳለ ተቀምጧል። ‹ምንድን ነው የሆነው? የት ሄደ?› ብዬ ግራ ተጋባሁና ስጠይቃቸው፡

"አይ! የዚህ ቤተ ክርስቲያን አፈር መድኃኒት/ ዕምነት መሆኑን ስለሰማን መቼም ከጤና የሚበልጥ የለም ብለን ግማሾቻችን ተቀብተነዋል፣ ግማሾቻችን በጥብጠን ጠጥተነዋል፣ ለሌላም ሰው ሰጥተናል" አሉኝ።

"እንዴት የምርምር ሥራዬን፣ ለምርምር ብዬ ያመጣሁትን እንዲህ ታደርጋላችሁ?" ብዬ እብድ ሆንኩባቸው። እነሱ እቴ ሊደነግጡ ነው?!

"አይ! ምነው! ከጤና የሚበልጥ ነገር አለ እንዴ?" አለች አንደኛዋ





"የቀረው ይበቃሃል በዚያው ተመራመር። ይህንኑ ይባርክልህ!" አለች ሌላኛዋ። ሁሉም እየተቀባበሉ ቁጣዬን አጣጣሉት።

እንዲያውም አንደኛዋ ቀበል አድርጋ፡

"ሲጀመር በቅዱስ ደብር አፈር መመራመር ምን ይባላል?" ስትል ሁሉም እየተቀባበሉ ጭራሽ ጥፋተኛው እኔ ልሆን እንደሚገባ የኅሊናና የሞራል ክስ አቀረቡብኝ።

ብዙ ወጭ አውጥቼ ጊዜዬን አጥፍቼ ያመጣሁት የዚያ ቤተ ክርስቲያን የምርምር ናሙና ሙሉ ለሙሉ መቅረት ነበረበት። ለእኔ ከገንዘቡ ወጪ ይልቅ የጊዜ ችግር ነበረብኝ። መረጃ በወቅቱ ሰብስቤ ወደ ዩኒቨርሲቲው (ኔዘርላንድስ) ለመመለስ የተሰጠኝ የተቆረጠ ወራት ነበረ። ብዙ ብበሳጭም የምቀይረው ነገር አልነበረም። እነርሱ እንዲያውም ሰብአዊነቴን ተጠራጠሩት።

"ምርምር ከሆነ ያለው ይበቃሃል፤ ምንድነው ሰው ዳነ ብሎ እንዲህ መበሳጨት!" ብለው ስላጣጣሉት እራሴን እንደገና ገዝቼ በእምነታቸው ተደነቅሁ። መበሳጨቱን ተውኩና እምነታቸው እጅግ ስላስደነቀኝ በልቤ፡

"አቤቱ እባክህ ለእኔም እምነት ጨምርልኝ!" አልኩ።

# እኔ እና ዶ/ር ተወልደ ብርሃን

ኢትዮጵያዊውን ሳይንቲስትና በዓለም አቀፍ ደረጃ የብዝሃ-ሕይወት ተሟጋች የሆኑትን ሎሬት ዶ/ር ተወልደ ብርሃንን የተዋወኳቸው በ2000 ዓ.ም. በባሕር ዳር ከተማ በኢትዮጵያ ጋዜጦች ማኅበር አዘጋጅነት ስለብዝሃ-ሕይወትና አካባቢ ጥበቃ በተዘጋጀ መድረክ ላይ ነበር። በዚያ መድረክ ላይ እርሳቸው የክብር እንግዳ ሆነው እኔ ደግሞ በብዝሀ-ሕይወት ዙሪያ ትምህርታዊ ገለፃ (Public Lecture) ለማድረግ በሄድኩበት ወቅት ነበር።

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በብዝሀ-ሕይወት ዕውቀት ዝናቸው የናኘውን በእድሜም ከእኔ በጣም ከሚልቁት፣ በሙያም በሥጋም አባቴ ሊሆኑ ከሚችሉት ሰው ፊት የብዝሃ-ሕይወትን

ጉዳይ አንሥቶ ገለፃ (Lecture) ለማድረግ ከፊታቸው ስቆም ከፍተኛ ፍርሃት እንደተሰማኝ አስታውሳለሁ።

ይሁንና ገለፃዬን ስጨርስ በጥሞና ሲያዳምጡ ከነበረበት ቆይታ ወጥተው በእጃቸው ወደ እርሳቸው እንድቀርብ ጠቀሱኝ። በአእምሮዬ የነበረው ሐሳብ፡

"ሁለተኛ አውቃለሁ ብለህ ከሰው ፊት ወጥተህ እንዳታቀርብ!" ሊሉኝ ነው ብዬ ተጨነኩ። ለማኝኛውም ጠጋ ብዬ እጅ ከነሳሁ በኋላ፡

"እንደምን አሉ? ደኅና ነዎት ወይ?" አልኳቸው። ለሰላምታዬ መልስ ሳይሰጡኝ እጄን ጭብጥ አድርገው ይዘው፡

"አንተ አስተማሪ መሆን ነው ያለብህ! እባክህ አስተማሪ ሁን!" አሉኝ። ገለጻዬ እንዳስደሰታቸው ስለተረዳሁ በውስጤ ከፍተኛ የመንፈስ እርካታ ተሰማኝ።

በዚህ ሁኔታ ነበር ከዶ/ር ተወልደ ብርሃን ጋር የተዋወቅኩት። የሕይወት ገጠመኝ ሆኖ እንዳለመታደል እሳቸው እንደተመኙልኝ አስተማሪ ባልሆንም በሌላ መስክ በሌላ ሥራ ተሰማርቼ ከሁለት ዓመት በኋላ እሳቸው የዓለም የእርሻና የምግብ ድርጅት (FAO) የተባለው ድርጅት በጠራው ስብሰባ ለመሳተፍ ሮም/ጣሊያን ቆይተው ወደ አዲስ አበባ ሊመለሱ እኔ ደግሞ ኔዘርላንድስ ውስጥ የምርምር ኮንፍረንስ ላይ ቆይቼ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ሮም አውሮፕላን ጣቢያ ውስጥ ተገናኘን። አላጠፉኝም ነበር። እኔም ፈጠን





ብዬ ሄጄ ሰላም አልኳቸው። አቅፈው ሳሙኝና ከዋሽንግተን አውሮፕላኑ ይመጣ ስለነበር በነበረን ሰፊ ጊዜ ብዙ ጉዳይ አንሥተን ተጨዋወትን።

ዶ/ር ተወልደ ብርሃን እጅግ ትሁት ከመሆናቸው የተነሳ ለማውራትና ማንኛውንም ጉዳይ አንስቶ ለመነጋገር አይከብዱም። የጓደኛ ያክል በቅርብ ያወራሉ። አንድ ዓይነት ሙያ ያለን ቢሆንም እርሳቸው በሙያው እጅግ ጠልቀው የገቡና ብዙ ርቀት የሄዱ ስለሆነ ለእኔ ከእርሳቸው ጋር ማውራቱ ሌላ ሰፊ የትምህርት ዓለም ውስጥ እንደመግባት ነበር። አንዱን ስናነሳ፣ አንዱን ስንጥል፣ ስለሀገራችን የተፈጥሮ ሀብት ውድመት፣ ስለደን ልማት፣ ስለብዝኀ-ሕይወት፣ ስለውኃ አካላት፣ ስለኢትዮጵያ፣ ስለ ዓለምቀፍ ሁኔታ ምን ያላነሣነው አለ?!

ብዙ ሰዓታትን በውብና ተናፋቂ ውይይት ካሳለፍን በኋላ አውሮፕላኑ ስለመጣ እንድንሳፈር ተጠየቅን። ወደ አውሮፕላኑ እርሳቸው ከፊት እኔ ከኋላ ሁነን ስንገባ አውሮፕላኑ በር ላይ ስንደርስ እሳቸው ወደ ግራ ታጥፈው ቢዝነስ ክላስ ውስጥ እንዲገቡ እኔ ደግሞ ወደ ቀኝ ያለውን መስመር ይዤ ወደ ኢኮኖሚ ክላስ እንደዬ ደረጃችን እንድንሄድ አስተናጋጇ ጠየቀችን።

ገራገሩ ዶ/ር ተወልደ ብርሃን ምንም ሳያቅማሙ አስተናጋጇን፡

"እባክሽ ያልተያዘ ቦታ ካለ እያወራኝ እንዲሄድ ቢዝነስ ክላስ ውስጥ እንዲገባ ፍቀጅልን" አሏት።

አስተናጋጇም፡

"እርግጥ ያልተያዘ ቦታ አለን። ግን ኢኮኖሚ ክላስ ውስጥ ያለን ተሳፋሪ ወደ ቢዝነስ ክላስ በምንም ምክንያት ልንወስድ አንችልም" አለች።

"ምናለበት ወንበሩ ባዶውን ከሚሄድ አብሮኝ እያወራኝ ቢሄድ" አሉ ድጋሜ እያስተዛዘኑ።

"የአየር መንገዱ ሕግ እንደዚያ አይፈቅድም። የሚሆን ነገር አይደለም" አለቻቸው ፈገግ ብላ።

ቅር እንዳላቸው ገምቼ እኔም ቀበል አደረኩና፡

"ዶ/ር እውነቷን ነው። ይሄ እኮ የትም ያለ አየር መንገድ ሕግ ነው። ምንም አይደለም አዲስ አበባ ስንደርስ እንገናኝ የለ? ይልቅ ይግቡና አረፍ ይበሉ" ብዬ ተሰናብቻቸው ወደ ኢኮኖሚ ክላስ ሄጀ ተቀመጥኩ። እርግጥ እርሳቸውም ጠፍቷቸው አልነበረም። ከፍጹም ቅንነታቸው ተገፍቶ የወጣ ሐሳብ ሆኖ እንጂ።

ጉዟችንን ጨርሰን አዲስ አበባ ስንደርስ እንደማንኛውም የፌዴራል ባለሥልጣን ባላቸው ልዩ መብት ቀድመው ወጥተው በአጭር ጊዜ ወደቤታቸው መሄድ ይችላሉ። እኔ ደግሞ በጣም ረጅሙን የፓስፖርት ቁጥጥር ሰልፍ ጨርሼ፣





ሻንጣዬን ጠብቄ እስክወጣ ድረስ ረጅም ጊዜ ይፈጃል። እንገናኛለን የሚል ግምት አልነበረኝም።

እጅግ ዘግይቼ ከኤርፖርቱ ስወጣ ከፊት ለፊት ላንድ ክሩዘር መኪና ከሾፌር ጋር ይዘው ሲጠብቁኝ አገኘኋቸው። በጣም ተሳቀቅኩ።

"እንዴ ዶ/ር! ለምን ጠበቁኝ? ለምን አልሄዱም? " አልኳቸው የምለው ጠፍቶኝ።

"እንዴ አብረን መጥተን፡ ስንት ነገር ተነጋግረን፡ እንዴት ትቼህ እሄዳለሁ? ይልቅ የምታርፍበትን ቦታ ንገረኝና የምታርፍበት ቦታ አድርሼህ ነው እኔ ወደ ቤት የምሄድ" አሉኝ።

"በፍፁም አይሆንም። እኔ ታክሲ እይዛለሁ። ታክሲ ይገኙ ዘመድ ጋ ነው የምሄደው። እርስዎ ግን እባክዎት ይሂዱ" አልኳቸው።

ሳስበው እኔ የማርፍበት ዘመዶቼ ጋ መካኒሳ ቫቲካን ኢንባሲ ወደሚባለው አልፎ በጣም ውስጥ ለውስጥ ብዙ የሚያስኬድ መንገዱ የማይመች ሰፈር ስለነበረ እኒህን የተከበሩ ሰው ይገኙ በዛ ሰፈር እኔን እንዲሸኙኝ መፍቀድ በራሱ ትልቅ ትዕቢት መሰለኝ። እና በፍፁም አይሆንም አልኳቸው።

እሳቸው ግን "የትም ቢሆን መጀመሪያ አንተን አድርሼህ ነው እኔ ወደ ቤቴ የምሄደው። ይሄ ምንም የሚለወጥ አይደለም።

ይልቅስ አሁን የምትሄድበትን ንገረኝ" አሉና ወደ መኪናው እንድገባ በእጃቸው ጋበዙኝ። ከዚህ በላይ መከራከር ስለማልችል፣ ትተውኝም እንደማይሄዱ ተገነዘብኩ። ብዙ እንዳይንገላቱ፣ ክብራቸውም የተነካ ስለመሰለኝ ነገሩን ለማቅለል ‹ዋቢ.ሸበሌ ሆቴል ነው የማርፍ› አልኩ።

የእርሳቸው መኖሪያ ዘነበወርቅ አካባቢ እንደሆነ ስለነገሩኝ ብዙ ሳላንገላታቸው ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ጥለውኝ ይሄዳሉ ብዬ አስቤ ነው። ከዚያ በኋላ እርሳቸው ወደ ቤታቸው ሲሄዱ እኔ በታክሲ ተሳፍሬ ወደ ጉራንጉር ሰፈሬ እሄዳለሁ ነበር እቅዴ።

በዚህም መሠረት የጀመርነውን ወሬ እየኮመኮምን ዋቢ.ሸበሌ ሆቴል ደረስን። ሆቴሉ በር ላይ ሹፌሩ ሲያቆም ቀድም ብዬ ወረድኩና፣

"ዶ/ር እግዚአብሔር ይስጥልኝ። ወደ ፊት አዲስ አበባ ስመጣ ቢሮዎ መጥቼ እንገናኛለን" ብዬ ለመሰናበት ስሞክር፣

"የለም የለም! መጀመሪያ እንግዳ መቀበያ አብረን እንሂድና ክፍል ማግኘትህን ስናረጋግጥ እንሰነባበታለን" አሉና መኪናውን ከፍተው ወረዱ። ሻንጣዬን ለመያዝ ሲዳዳቸው ቀልጠፍ ብዬ ሻንጣዬን አፈፍ አድርጌ ወደ እንግዳ መቀበያው ሄድን። ዋቢ ሸበሌ አልጋ ይዞ ለማደር ጨርሶ ፍላጎትም እቅድም አልነበረኝም። ሁኔታው ያልገመትኩት ስለነበር ተደናበርኩ። እንደምንም ተረጋግቼ እንግዳ ተቀባዩ ጋ ጠጋ ብዬ አልጋ ይኖር እንደሆን ጠየኩ። አለ ተባልኩና መታወቂያዬን ሰጥቼ፣ ፎርም ሞልቼ አልጋ መያዜን ዶክተሩ





ቆመው አረጋገጡ። የሆቴሉ አስተናጋጅ መጥቶ ሻንጣዬን እየጎተተ ወደ አሳንሰሩ ሲሄድ እኔም ተከትዬ መሄድ ግዴታዬ ሆነ። በዚህን ጊዜ ዶ/ር ተወልደ ብርሃን አቅፈው ሳሙኝና፣

"በል ደሕና ሁን! አሁን እረፍት ያስፈልግሃል። ወደ ፊት ስትመጣ ጠይቀኝ" አሉኝ። ወደ አሳንሰሩ ሁሉ ሳመራ እንደቆሙ ነበር።

በዚህ ሁኔታ እኔም ታላቁን ሰው ላለማድከም፤ እርሳቸውም የተራራ ያክል የገዘፈ ክብርና ማዕረግ ያላቸው ቢሆንም እኔን ትንሹን የሙያ አጋራቸውን የወደኩበትን ሳያረጋግጡ ላለመሄድ ስለፈለጉ በሁለታችን ይሉኝታ ያለ እቅዴ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል አደርኩ። አሁን ድረስ ሳስበው እርሳቸውን ከማንገላታ እንኳንም ዋቢ ሸበሌ ሆቴል አደርኩ እላለሁ።

# ባለቁመጠው መሀንዲስ

ባሳለፍኳቸው የሥራ ዘመናት ውስጥ ከማስተማርና የምርምር ተግባር ከማከናወን፣ የደን ባለሙያ ሆኖ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ከመሥራት አልፌ የቢዝነስ ተቋም ስመራ ጣና ፍሎራ የተባለው የመጀመሪያዬ ነበር። ጣና ፍሎራ ንብረትነቱ ጋፋት ኢንዶውመንት የሚባለው ድርጅት ሲሆን ከባሕር ዳር ከተማ አቅራቢያ ወንጀጣ በሚባል ቀበሌ 100 ሄክታር ላይ አትክልት፣ ፍራፍሬና አበባ በማልማት ለዓለም አቀፍ ገቢያ ኤክስፖርት ለማድረግ የተቋቋመ ኩባንያ ነበር። ይህን ኩባንያ በዋና ሥራ አስኪያጅነት እንድመራ ከተመደብኩ በኋላ በተለይ አዲስ የሆነውንና በአካባቢው የመጀመሪያ የተባለውን በ40

ሄክታር ላይ የሚለማ ዘመናዊ የአበባ እርሻ ማቋቋም ፈታኝ ነበር። 40 ሄክታር ሲባል እያንዳንዳቸው አንድ ሄ/ር ስፋት ያላቸው 40 ግሪን ሃውስ መገንባት ማለት ነው።

ከዚህ ጋራ ዘመናዊ የሆነ የጠብታ መስኖ (Ferit-Irrigation System)፣ የመጠጥና የንጽህና መጠበቂያ ውኃ አቅርቦት ሥርዓት፣ የበሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ ርጭት ሥርዓት፣ የአበባ ማሸጊያና የማቆያ ማቀዝቀዣ ክፍሎች፣ ባጠቃላይ የተደራጀ የእርሻ ልማት ማቋቋም ይጠይቃል።

ዓለም አቀፍ ጨረታ አውጥቶ እነዚህን ዘመናዊ ግሪን ሃውሶች፣ የጠብታ መስኖ መዋቅሮች፣ ትልቅ መጋዝን ውስጥ የሚገጠም ሪፍሪጅሬተር፣ ፓምፖች፣ ጀኔሬተሮችና ሌሎች የተለያዩ እቃዎችን 168 ባለ አርባ ጫማ ኮንቴነር ከወደብ ማማላለስና መገጣጠም ያስፈልግ ነበር።

ማጓጓዙ ፈታኝ ቢሆንም ከሁሉ በላይ ደግሞ እያንዳንዱ ግሪን ሃውስ የሚያርፍበትን መሬት በሁለት ፐርሰንት ተዳፋት ግራና ቀኝ እኩል አድርጎ ጠርጎ ማስተካከል ይጠይቅ ነበር። ይህን ለማድረግ ትልልቅ ማሽነሪዎች ያስፈልጋሉ። ድንጋይ ለማውጫ ኤክስካቬተር፣ የወጣውን ድንጋይ የሚገፋ ዶዘር፣ አፈሩን ከቦታ ቦታ የሚሞላው ሎደር፣ ስሎፑን ጠብቆ የሚቆርጥ ደግሞ ግሬደር ያስፈልጋል። ይህንን የሚመራ የቅየሳ መሐንዲስ እጅግ ወሳኝ ነበር።





ለዚሁ ቅየሳ ሥራ ሲቪል መሀንዲስ ቀጥረን ሥራውን መሥራት ጀመረ። አንድ ሁለት ግሪን ሃውስ ተሠርቶ ሲታይ የተዛነፈ ሆኖ ተገኘ። ያን መሀንዲስ አባረን ሌላ የተሻለ የተባለ ፈልገን ቀጠርን። አዲሱ መሀንዲስ ሥራውን በትክክል መሥራት የቻለ ቢሆንም ውድ ነበር። ከባሕር ዳር አስራ ሰባት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደሚገኘው የእርሻ ቦታ ጠዋት መውሰድ አለብን። ቀን ላይ ተመልሶ መጥቶ ምሳ በልቶ ይሄዳል፣ ከዚያ ማታ ደግሞ መመለስ ይኖርብናል። ስለዚህ ለእርሱ አንድ ተሽከርካሪ መመደብ፣ የሞባይል ካርድ መሙላት፣ ከደመወዙ በላይ አበልና አላዋንስ መክፈል ነበረብን።

ለእያንዳንዱ ማሽን በሰዓት የሚከፈለው ከፍተኛ ስለነበረና ሥራው ፋታ የማይሰጥና በሆነ ምክንያት ከቆመ እጅግ ውድ እና ለኪሳራ የሚዳርግ ስለሆነ ለመሀንዲሱ የምናወጣው ወጪ ብዙ አሳሳቢ አልነበርም።

በዚህ መሠረት ስምንት(8) ግሪን ሃውስ በጥሩ ሁኔታ እንደሠራን መሀንዲሱ ወደ ቢሮዬ መጣና፡

“ሌላ ቦታ በተሻለ ክፍያ ሥራ ስላገኘሁ ልሄድ ነው” አለኝ ቁርጥ ባለ ድምፅ።

“እንዴ! ምን ነካህ? ይኼ ሁሉ ማሽን አንድ ሰዓት እንኳን ቢቆም ስንት ኪሳራ እንደሚደርስ እያወቅህ እንዴት በዚህ ሰዓት ሥራ እለቃለሁ ትለኛለህ? እኔም እኮ ከአንተ የተለዩ

ሓላፊነት የለብኝም ሀገር እናለማለን ብዬ ነው እንጂ" አልኩኝ በድንጋጤ

"አይ እድሉ እንዲያመልጠኝ አልፈልግም" አለኝ ፈርጠም ብሎ።

"ሌላ ባለሙያ ፈልጌ ለማግኘት፣ ካገኘሁ በኋላም ሥራውን እንዲያውቅ ለማድረግ የሚፈጀውን ጊዜ ታውቀዋለህ ቢያንስ ወር ይፈጃል። አጠቃላይ ሥራው ከመጓተቱም በላይ እነዚህን ውል ፈርመን ያስገባናቸውን ማሽነሪዎችንስ ምን እናደርጋቸዋለን? እባክህ ሓሳብህን መቀየር አለብህ። እምቢ ካልክ ደግሞ የተወሰነ ደመወዝ ልጨምር" ስለው

"የፈለገው ብትጨምርልኝ አሁን ካገኘሁት ሊደርስ አይችልም" አለና። "ለማኝኛውም አንድ ሳምንት እሰጥሀለሁ፡ በሳምንት ውስጥ ሰው ፈልገህ እንድታገኝ" ብሎ እቅጩን ነገረኝ።

እጅግ ነበር የተከፋሁትና ተስፋ የቆረጥኩት። ‹እኔስ የግል ተቋሜ አይደል። በአካባቢው የሥራ ዕድል ለመፍጠር የተቋቋመ የልማት ድርጅት ነው። ይህን ያክል እኔስ ለምን እሰቃያለሁ› በሚል የመሀንዲሱ ጭካኔ የእኔንም የሥራ ፍላጎት ጎዳው።

ለማንኛውም እንደ ሥራ ሓላፊነቴ እውነታውን መጋፈጥ ስለነበረብኝ ከሁለት ቀናት በኋላ ‹እስኪ ሥራው የደረሰበትን ለማንኛውም አሳዬኝ› ብዬ ሥራውን ለማየት ሄድኩ። ሳይት እንደደረስን ተቆርጦ የተዘጋጁትን ስምንት ግሪን ሀውሶች፣





ወደ ፊት ሊቆረጥ የታሰበውን እና እያንዳንዱ ማሽን የሠራውን ሰዓት አሳዬኝ።

ያን ሁሉ ደረጃ በደረጃ ካሳዬኝ በኋላ እሱ ወደ ሥራው ሲሄድ እኔ አንድ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብዬ ቀረሁ። እጅግ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ነበረኝ። በዚህ መካከል አንድ ወጣት ከመሀንዲሱ ጋር ስንነጋገር ሓሳቡን እንዲቀይር ስለምነው ሁሉ ከኋላ ሆኖ ይሰማን ነበር።

ይህ ወጣት ለመሀንዲሱ የቅየሳ መሳሪያ እንዲሸከምለት፣ እንዲታዘዘው፣ ከቦታ ቦታ እንዲላላከው የቀጠርነው ልጅ ሲሆን አስረኛ ክፍል ተማሪ ሆኖ ትምህርቱን ያቋረጠ በአከባቢው የሚኖር ነበር። እጅግ ገራገር የሆነ ለእግሩ ጫማ እንኳን የሌለው ቁምጣ ለብሶ የመጣ ልጅ ስለነበረ በቀን ሠራተኛነት 40 ብር እንከፍለዋለን። ይኼ ልጅ ያሳለፍናቸውን ጊዜያት በሙሉ ከዚህ መሀንዲስ አልተለዬም ነበር። ስምንቱ ግሪን ሀውሶች ሲስተካከሉ ሁሉ አብሮ ነበር። ተክዤ መቀመጤን አየና ቀደም ብሎም ከመሀንዲሱ ጋር የተነጋገርነውን ይከታተል ስለነበር ጠጋ ብሎ እንዲህ አለኝ፡

"ጋሽ ዶ/ር ምን ሆነህ ነው እምታዝን?" አለኝ። ሁሉም ሰው ‹ዶክተር› እያለ በተደጋጋሚ ስለሚጠራኝ እዛ አካባቢ ያሉ የቀን ሠራተኞችና የአካባቢው ሰዎች ‹ዶክተር› የሚለው ስም ማዕረግ መሆኑ ቀርቶ ስሜ ይመስላቸው ነበር። ስለዚህ አክብሮ ለመጥራት ‹ጋሽ ዶክተር› ይሉኛል።

እኔም እንደተከፋሁ

“ምን እባክህ” አልኩኝና የመሀንዲሱን ስም ጠርቼ “ሥራውን ትቼ እሄዳለሁ አለኝ” ስለው

“ኸረ ጋሽ ዶክተር! የማያሳስበውን!” አለኝ።

ገራገርነቱ ገርሞኝ፡

“እንዴ! እንግዲህ እኮ ሥራው መቆሙ ነው። እሱ ከሌለ ማን ይቀይሳል? እናንተም ሥራ ልታቆሙ ነው። ይሄ እኮ ነው ያሳሰበኝ” አልኩት እንዲረዳው ብዬ። ቀጠል አደረኩና “ለነገሩ የኪሳራውን ስፋት አንተ አትረዳውም?” አልኩና ወደ ትካዜዬ ልመለስ ስል፡

“ኦሮዋ! መሬቱን ለክቶ ማስቆረጡን እንደሆነ እሱ የሚሠራውን እኮ እኔ እሠራለሁ” አለ

በየዋህነቱ ከት ብዬ ሳኩና፡

“አንተ ደግሞ ከየት አምጥተህ ነው የምትሠራው? እሱ እኮ መሀንዲስ ነው።” አልኩት

“ጋሽ ዶክተር! እችላለሁ ስልህ” አለ አሁንም።

“ዝም ብሎ መሬት የሚቆረጥ መሰለህ እንዴ? በዚያ መሣሪያ ለክቶ አውቆ ነው እኮ ችካል ቸክሎ የሚሰጣችሁ። ስታየው ቀላል መስሎህ ነው አይደል?” አልኩት። የዋህነቱ ገርሞኝ ነው እንጂ በዚያ ሰዓት ከእርሱ ጋር የማወራበት ስሜት ላይ





አልነበረኩም። እና ፊቴን ሳዞር አይቶ፡

“አይ ጋሽ ዶክተር ጅል ነህ ለካ” አለኝ።

‹ይሄ ልጅ ከችግሬ በላይ የሚቀባጥርብኝ ምን ነክቶታል› ብዬ በቁጣ ፊቴን ወደእርሱ ሳዞር አይቶ፡

“‹ጠሐይ ይበላኛል› እያለ እሱ እኮ አይሠራም። አንድ ሁለት ቀን አሳዬኝና አስተካክዬ ስሠራው ጊዜ ተዚያ በኋላ እሱ ጥላ ፈልጎ ቁጭ ነው የሚል። እኔ እኮ ነኝ የምሠራው!” አለኝ። የችግሬን ባሕር ከሁለት ሊከፍል የሙሴን በትር ይዞ የመጣ ሰው መሰለኝ።

“እውነትክን ነው?!” አልኩት

“ኸረ ጋሽ ዶ/ር ለካ ሰው አታምንም!” አለኝ።

“እውነት አንተ መሣሪያውን አንብበህ ምን እንደሚደረግ ታውቃለህ? መሬቱን ታስቆርጠዋለህ?” አልኩ በድጋሚ

“ኦሯ! እሱ እኮ አራት ነው የሠራው። ተዚያ ወዲህ ያለውን እኮ እኔ ነው የሠራሁት” አለኝ።

“እውነትክን ነው?!” አልኩት ደግሜ

“ ታላመንከኝ እ..” አለና “ተፈለክ ሾካል (ችካል) ይምጣና ሞክረኝ!” አለ።

ለማመንም ላለማመንም ተቸገርኩ። እጅግ ስሜታዊ ከመሆኔ የተነሳ መኪናዬን አስነስቼ ወደ ባሕር ዳር እየበረርኩ መጣሁ። ገበያ ሄድኩና አዲስ ቱታ፣ ባርኔጣና ከስክስ ጫማ ገዛሁ። ለዚሁ ልጅ። ከሰማይ ለወረደልኝ መሀንዲስ።

በነጋታው መሀንዲሱን እረፍት ሰጠሁኝና ተመልሼ ሄጄ፡

"በል እንግዲህ ቀጥሎ ያለውን መሬት አዘጋጅና አሳዬኝ" አልኩት። ለእርሱ ደግሞ ረዳት ተሰጠው። ችካል ተዘጋጀ።

ሁለት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አንዱን ሄክታር በቅየሳ መሣሪያው እየተመለከተ እንደሚቆረጠውና እንደሚሞላው ሁሉን አድርጎ ችካሎችን ቸክሎ ጨረሰ።

ቀጠልኩና እዚያ ያሉትን ማሽነሪ ኦፕሬተሮችን ጠራሁና ‹አሁን እርሱ በሚላችሁና በሚያሳየው መሠረት ያለምንም ማንገራገር የሚቆረጠውን ቁረጡ ሙሉ የሚላችሁን ሙሉ! አንድም ማንገራገር የለም› ብዬ ትዕዛዝ ሰጠሁ።

ከስፔናዊው ግሪን ሀውስ አቅራቢ ድርጅት ጋር ኮንትራታችን ግሪን ሀውሱን ተክሎ ማስረከብ ጭምር ስለነበረ መሬቱ ከተስተካከለ በኋላ ግሪን ሐውሱን የሚያቆሙት ሁለት ኬንያውያን ቴክኒሻኖች ናቸው። መሬቱን ማስተካከል ግን የእኛ ሥራ ነበር። እነዚህ ቴክኒሻኖች ይመጡና በራሳቸው መንገድ መሬቱ በትክክል መስተካከሉን ሲያምኑ ግሪን ሐውስ ወደ ማቆም ይቀጥላሉ። ችግር ካለበትም ለእኔ ሪፖርት ያደርጋሉ።





በማግስቱ ኬንያውያኖችን ወስጄ ማን እንደሠራው ሳልነግር፡

"ይኼ አዲስ የተዘጋጀ ነው፡ ትክክል መሆኑን ቼክ አድርጉና ተረከቡ" አልኳቸው። በራሳቸው መንገድ ደጋግመው ቼክ አደረጉና፡ ‹በትክክል ነው የተሠራው› ብለው አረጋገጡልኝ።

እውነት ለመናገር ማመን አልቻልኩም። ድንገት ተንደርድሬ ሄጄ ያንን ወጣት አቀፍኩት!!

ያንን መሀንዲስ የለመንኩትን ያክል እንዲያውም ቶሎ እንዲሄድልኝ የሳምንቱን ጊዜ አሳጥሬ በቀናት ጊዜ ውስጥ አሰናበትኩት!

ይህ ወጣት መኪና፣ አበል፣ የሞባይል ካርድ አይጠይቅም። የሚጠይቀው በቀን 40 ብር ብቻ እንደ ቀን ሠራተኛ ነበር። ከተወሰኑ የሥራ ቀናት በኋላ ሄጄ አገኘሁትና ምን እንዳደርግለት እንደሚፈልግ ጠየኩት።

"አይ... ጋሽ ዶክተር እንዲያው..." አለና ትንሽ ሲያቅማማ

"ምንድን ነው? ንገረኝ አትፍራ!" አልኩት። የፈለገውን አድርግ ቢለኝ ለማድረግ ዝግጁ ነበርኩ። ‹ብቻ እርሱ ደግሞ ልሂድ ነው እንዳይለኝ እንጂ› እያልኩ ስጨነቅ።

"እንዲያው ይሄ ያመጣህልኝ ቱታና ጫማ አልተመቸኝም፡ እና በቁምጣና በባዶ እግሬ ብሠራ ይሻለኛል ነበር" አለኝ

ከት ብዬ ሳኩና "አይቻልም!" አልኩት። "የማን መሀንዲስ ባበዶ እግሩ ይሄዳል!"

ለማንኛውም እርሱ ባይጠይቀኝም የቀን አበሉን ወደ 100 ብር ማሳደጌን ስነግረው ትልቅ ደስታ ሆነለት። የሚገርመው 40ውን ሄክታር ግሪን ሃውስ፣ ፓክ ሃውስ እና ሌሎች ግንባታዎችንም በሚያስደንቅ ችሎታ (Precesion) ሠርቶ አጠናቀቀ። እጅግ ውጤታማ ነበር።

ኩባንያው የግንባታ ሥራውን አጠናቆ አበባ ተክሎ ወደ ውጭ ኤክስፖርት ማድረግ ሲጀምር ይሔን የክፉ ቀን ጉብል መሀንዲስ ሥራው ስለተጠናቀቀ ተራ የቀን ሠራተኛ ሆኖ እንዲቀመጥ ወይም እንዲሰናበት አልፈለኩም። ለመሀንዲሱ እንከፍለው የነበረውን ገንዘብ አስልቼ ያ ገንዘብ መሀንዲሱ ቢኖር ኖሮ ልናወጣው የሚገባው ነገር ግን በዚህ ወጣት ምክንያት ያዳነው ስለሆነ የኩባንያው ቦርድ በፈቀደልኝ መሠረት ያን ወጣት ሙሉ ወጭውን ችለን መደበኛ የቅየሳ (ሰርቬይንግ) ትምህርት እዲማር ኮሌጅ አስገባሁት። ከሁለት ዓመት በኋላ ተመርቆ ዲፕሎማ ይዞ ከቢሮዬ መጥቶ ተገናኘን።

ይህን ወጣት ባሰብኩ ቁጥር በሀገራችን የስንቱን ብሩህ አዕምሮ፣ የስንቱን ውበት፣ የስንቱን መልካም አስተሳሰብ ድህነት ጨፍልቆት እንደቀረ እያስታወስኩ ልቤ በሐዘን ይኮማተራል።





ይህ ወጣት ምንም ዓይነት ስልጠና ሳይሰጠው ከመሀንዲስ ጋር ስለዋለ ብቻ በልበ ብርሃንነት መሀንዲሱን አክሎ፣ መሀንዲሱን መስሎ ውስብስብ የተባለውን ሥራ ማጠናቀቁ ምን ያክል የአዕምሮ ብርሃን የተሰጠው እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ብዙዎች በዚህ ሁኔታ ገጠሬ ሆነው፣ እረኛ ሆነው፣ ጎዳና ተዳዳሪ ሆነው ባክነው እንደቀሩ መገመት ይቻላል። ይህን ማሰብ ልብ ይሰብራል። ለማንኛውም ልበብርሃኑ የወንጀጣው መሀንዲስ አሁን ማረጋገጫ ያለው ባለ ዲፕሎማ መሀንዲስ ሆኗል።

# ሙሉ ዶሮ (Full Chicken)

የማስተርስ ትምህርቴን ለመማር ወደ ወንዶገነት የደን ኮሌጅ ስገባ ኮሌጁ ከስዊድን ግብርና ዩኒቨርሲቲ ጋር ባለው ስምምነት መሠረት ግማሹ ትምህርት ወንዶገነት፤ ግማሹ ትምህርት ስዊድን ሀገር ይሰጥ ነበር። ፕሮግራሙን የሚያስተባብሩት ስዊድናውያን ሲሆኑ የስዊድን ግብርና ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የነበረችው በ60ዎቹ ዕድሜ ክልል ውስጥ የምትገመተው ዶ/ር ፒያ ባርክላንድ ይህንን ፕሮግራም ለማስተባበር ወንዶገነት መጥታ ነበር።

በፕሮግራሙ መሠረት በሀገር ውስጥ የተወሰነ የቀለም ትምህርት ከተማርን በኋላ ወደ ስዊድን ሀገር ሄደን ተጨማሪ ትምህርት ከመውሰዳችን በፊት የመስክ ልምድ ለመቅሰም ወደ ኬንያ መጓዝ ነበረብን። ብዛታችን 16 ስንሆን ከመካከላችን ውስጥ አንደኛዋ ሴት ስትሆን ሌሎቻችን ወንዶች ነበርን። ከአዲስ አበባ ተነሥተን ናይሮቢ እንደደረስን ለእያንዳንዳችን በቀን የሚያስፈልገን አበል ተቆጥሮ በዶላር ተሰጠን።

እንደሚታወቀው ብዙ ኢትዮጵያውያን ወደ ውጭ ሀገር ስንሄድ በተለይ ለትምህርትም፣ ለስብሰባም፣ ለሥራም ለአጭር ጊዜ ስንጓዝ ከሁሉ በፊት ቀድሞ የሚታሰበን ዶላር ቆጥቦና አተራርፎ ወደ ሀገር ቤት ኤሌክትሮኒክስ ዕቃ እንዲያም ሲል መኪና አለበለዚያም አጠራቅሞ መጥቶ ቤት መሥራት ወይም አንድ ቋም ነገር ማድረግ ነው። ቁጠባው መጠን ያለፈ ወደ ስስት የተጠጋ ይመስላል። በሀገር ውስጥ የምናገኘውን ብር በረባ ባረባው የምናባክነውን ያክል ዶላር ሲሆን ለምን እንደሚያንገበግበን ሁልጊዜ ይገርመኛል። የምናገኘው ዶላር ይብዛም ይነስም መቆጠብ እንዳለብን በአዕምሯችን ውስጥ ሳይታወቀን የታተመ ይመስላል።

እናም ኬንያ ከገባንበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወርን አንድ ሁለት ሦስት ቀናት እንዳሳለፍን የፕሮግራማችን አስተባባሪ ዶ/ር ፒያ አንድ ነገር አስተዋለች። አብዛኛው ሰው የምሳ ሰዓትና የራት ሰዓት ጠብቆ እንደማይመገብ ነገር ግን ቁርስ ከአልጋው ጋር ስለሚታሰብ ሁሉም ቁርስ ላይ እንደሚረባረብ፣ እንዲሁም





ለገለጻ በምንሄድባቸው ተቋማት ገለጻ ሲኖር በዚህ መካከል የሚቀርቡ ኩኪሶችን ደጋና አድርጎ ቸርፍሶ ዋናውን የምሳ ሰዓት ማሳለፍና እርሷ ባታውቀውም በእኛ በኩል ገንዘብ የመቆጠብ ስልት ነበር። ሁለት ሦስት ቀን ካየችን በኋላ በቂ ምግብ አለመብላታችን በጣም ያሳስባት ጀመር። እንዲያውም አልፎ አልፎ የግድ ምሳ እንድንበላ ሲታዘዝ በኬንያዊያን የምግብ አቀራረብ ሩብ ዶሮ (Quarter Chicken) የሚባለውን ወይም የአንድ ዶሮ አንድ አራተኛ በሁለት ቀን አንድ ቀን እያዘዘ ሰው ይበላል። ዶ/ር ፒያ በተለየ ሁኔታ ታቀርበኝ ነበር። ለምን እንደሆነ ምክንያቱን የምታውቀው እርሷ ብቻ ናት። ብዙ ጊዜ የሚሰማትን ቅሬታም ሆነ ማንኛውንም ነገር ጠርታ ትነግረኛለች። ትዝብቷንም ቅሬታዋንም የምትነግረው ካሉት ውስጥ ለእኔ ነበር። ይህን የተወሰኑ ጓደኞቼም የሚያውቁ ይመስለኛል።

ከዕለታት አንድ ቀን፡

"ለምንድን ነው በቂ ምግብ የማትበሉት? በቂ ምግብ የምትበሉ አልመሰለኝም። ስለዚህ አበል መስጠት ላቆም ነው። ምክንያቱም በርሃብ ብትታመሙ የምጠየቀው እኔ ነኝ። ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ምግብ ታዛላችሁ እኔ እከፍላለሁ እንጂ አበል አልሰጥም" አለች።

እኔም ያን ያክል ሊያሳስባት እንደማይገባና ዝም ብላ አበሉን ብትከፍል እንደሚሻል ብነግራትም አልተቀበለችኝም። እኔንም የችግሩ አካል አድርጋ ቆጥራኝ ይሆናል። በሚቀጥለው ቀን

እንዳሰበችው ዶላሩን ለእኛ መክፈሉን አስቀርታ ምግብ አዘን እንድንበላ እርሷ ለምግብ ቤቶች እንደምትከፍል ተናገረች። በዚህ ውሳኔዋ ብዙዎቹ ጓደኞቼ አጉረመረሙ።

"ምናገባት እርሷ! ከፈለግን እንበላለን፣ ካልፈለግን ብንተዎውስ? ማነው እርሷን ተቆጣጣሪ ያደረጋት?" እየተባለ ሁሉም ሰው እንደ አይሁድ አጉረመረመ። ለማንኛውም ዶላሩ በእርሷ እጅ ስለነበረ ምንም ማድረግ አልተቻለም።

በጠዋት ተነሥተን እንደ ተለመደው ትምህርታዊ ጉብኝት ስናደረግ ዋልንና ስሙን ለጊዜው በውል የማላስታውሰው (ናኩሩ ይመስለኛል) የኬንያ ከተማ ስንደርስ ምሳ ብሉ ተብልን ከመኪና ወርደን ወደ አንድ ምግብ ቤት ገባን። ዶ/ር ፒያ በአዲሱ ፖሊሲዋ መሠረት ከቀረበው ሜኑ (የምግብ ዝርዝር) ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት መርጠን ማዘዝ እንደምንችልና እርሷ የሁሉንም ሂሳብ እንደምትከፍል ተናገረች።

ምግብ ቤት ውሰጥ ገብተን ወንበር ይዘን እንደተቀመጥን ስልክ ለማናገር ይመስለኛል እርሷ ወደ ውጭ እንደወጣች ከነበርነው 16 ተማሪዎች ውስጥ አንድ ሦስት ወይም አራት ይሉኝታ የሚያጠቃን ተማሪዎች ስንቀር ሌሎቹ ለወትሮው ሁሉም ሩብ ዶሮ ጥብስ (Quarter Chicken) ያዝ የነበረው ሁሉ ሙሉ ዶሮ ጥብስ (Full Chicken) አዘዙ። ነገሩ ለማብሸቅ ይመስላል። የኬንያ ዶሮ ደግሞ እጅግ ግዙፍ በመሆኑ እንኳን ሙሉ ዶሮ ይቅርና ግማሹ እራሱ በእኛ አቅም የሚጋመስ አይደለም። አንድ ረጅም ጠረንጴዛ ላይ ዙሪያውን ተደርድረን ተቀምጠን





የተወሰነው እንደተለመደው ሩብ (Quarter) 12ቱ ተማሪዎች ግን ሙሉ ዶሮ (Full Chicken) ቀርቦላቸው ጠረንጴዛው በሙሉ ሞልቶ የሆነ ተኣምራዊ ትዕይንት የሚመስል ታዬ።

በዚህ መኻል ዶ/ር ፒያ ረጅም የስልክ ንግግሯን ጨርሳ ተመልሳ ስትመጣ ጠረንጴዛው በሙሉ ቋጥኝ በሚያካክሉ የተጠበሱ የዶሮ ሥጋዎች ተሞልቷል። ያየችውን ለማመን አልቻለችም። ነጭ ፊቷ ድልህ መሰለ። እንደተለመደው ጠራችኝ።

ሁሉም "እ... ወዳጅህ የእየጠራችህ ነው ሂድ" አሉኝ ዶሯቸውን እየጋጡ። እኔም መጋጤን አቋርጬ ወደ እርሷ ስሄድ ወደ ውጭ አወጣችኝና

"Almayw... this is not fair!... not fair...

when you pay, quarter chicken,

when I pay, full chicken!!

ዓለሚያው ፍትሃዊ አይደለም...አይደለም...

እናንተ ስትከፍሉ ሩብ ዶሮ

እኔ ስከፍል ሙሉ ዶሮ " እንደማለት ነው።

ብስጭቷ እስካሁን ከዓይኔ ላይ አይጠፋም። ተመልሼ መበሳጨቷን ነገርኳቸው። መበሳጨቷን ሲሰሙ ሁሉም ተደሰቱ። በዕድሜ ከመካከላችን በጣም ሽምገል ያለው

ጓደኛችን፣

"እንግዲህ ምን ይደረጋል። መቼስ አይመለስ። ባይሆን ለወደፊቱ ንገራት! ዝምብላ ዶላሩን ትስጠን!" አለና ሥጋውን መንጨቱን ቀጠለ።

ድሆች መሆናችን እውነት ቢሆንም ወደ ውጭ አገር ስንሄድ ግን አዕምሯችን ውስጥ በፈጠርነው ሥነ-ልቦና ድህነታችንን በእጅጉ እናገዝፈዋለን!





# <እኔ ብሞትም ሰርዶ ይብቀል>

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2012 እኔና አሜሪካዊዋ ተባባሪዬ ዶ/ር ማርጋሬት ሎማን ናሽናል ጅኦግራፊ ከሚባለው ሶሳይቲ የሁለት ዓመት የምርምር ፈንድ አግኝተን ነበር።

ያገኘነው ፈንድ ሰፋ ያለ ምርምር የሚያሠራ ጠቀም ያለ ስለነበር ይህንን እድል በማግኘቴ እጅግ ተደሰትኩ። በምርምር ከማገኘው ውጤት ይልቅ በዚህ ሥራ ሂደት ውስጥ በውሎ አበልና ጉዞ ሰበብ በርከት ያለ ገንዘብ አገኛለሁ ብዬ በማሰቤ ነበር። ይሁን እንጅ ዶ/ር ማርጋሬት ገንዘቡ እንደተፈቀደልን ምን ማድረግ እንዳለብን እቅድ እንድናወጣ ተገናኝተን ስንነጋገር፣

"ይህ ትንሽ አሣ ነው። ትንሽ አሣን ደግሞ ከመብላት ይልቅ የትልቅ አሣ ማጥመጃ ማድረግ በጣም የተሻለ ነው" የሚል ሐሣብ አመጣች። በአእምሮዬ የነበረውን እንደተረዳች ሁሉ!

ምን ማለቷ ነው?

"የዚህን ፕሮጀክት ጥናት እኔና አንተ ብቻ ከምንሠራው ይልቅ ሌሎች ባለሙያዎችን መጋበዝ ይኖርብናል" ነው።

የምርምር ፕሮጀክቱ በተመረጡ የኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት ተጠብቀው በኖሩ ደኖች ውስጥ ያለውን የብዝሀ ሕይወት ዓይነትና መጠን እንዲሁም ያሉበትን ሁኔታ ማጥናት ነበር።

እኔ የደን ሣይንስና ሥነ ምህዳር ባለሙያ ስሆን እርሷ ደግሞ የጥቃቅን ነፍሳት (Entomologist) እና ካኖፒ ባይዖሎጂስት/ Canopy Biologist (በዛፎች አናትና የደኖች የላይኛው ክፍል ላይ ስላለ ሕይዎት የሚያጠና ሙያ) ስለሆነች የማንሸፍነው የጥናት ዘርፍ ስለነበረ ነው።

"...እና ሰፋ ያለ ጥናት ለማድረግ ሌሎች አሉ የሚባሉ ተመራማሪዎችን ጋብዘን ሙሉ ወጪቸውን ችለን ብናመጣ የጥናት ውጤታችን ትልቅ ይሆናል። በዚህም ዓለም አቀፍ እውቅና እናገኛለን። ያን ጊዜ ወደ ትልቁ አሣ መቅረብ እንችላለን" አለች





እንደ እውነቱ ከሆነ በወቅቱ ባለኝ ገንዘብ ቶሎ የማግኘት ፍላጐት እኛ ብቻ ብንሠራውና ትንሽ ብናተራርፍ የተመኘሁ ቢሆንም ሐሳቧ እንዲህ በቀላሉ የሚጣል አልነበረም። በዚህ መሠረት እርሷ የምታውቃቸውን ከእኛ ጋር መስከ መጥተው ጥናት ሊያደርጉ የሚችሉ በቂ ልምድና እውቀት ያላቸውን ሰዎች ማፈላለግ ጀመረች።

በአጭር ጊዜ ውስጥ ከአውስትራልያ፣ ኦስትሪያ፣ እንግሊዝ፣ ካናዳ እና አሜሪካ ውስጥ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚያስተምሩ አስራ ሁለት አንጋፋ ፕሮፌሰሮችን፣ ዶክተሮችንና ተመራማሪዎችን ለማሰባሰብ ቻለች።

እነዚህ ተመራማሪዎች ከእኛ ጋር መጥተው ኢትዮጵያ ውስጥ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ቅሪት የተፈጥሮ ደኖች በሚገኙባቸው አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ደኖች ላይ ሰፋ ያለ ምርምር ማድረግ ቻልን።

በዚህ ምርምር ውስጥ ግማሾቹ የእፀዋት፣ የአዕዋፍ፣ የነፍሳት፣ የደረት ተሣቢ እንስሳት፣ የአፈር ደቂቀ ሕዋስያን፣ ብቻ በየዓይነቱ የነበሩ ምሁራን ሲሆኑ ከእነዚህ ጋር መሥራትና መተዋወቅ ብዙ ልምድና እውቀት ያገኘሁበት ስለሆነ ኋላ ላይ ሳስበው ተደስቻለሁ።

በዚህ አጋጣሚ በዚህ ምርምር ለመሳተፍ መጥተው ከነበሩት መካከል ስለ ሁለት አስደናቂ ሰዎች ጥቂት ላወራችሁ ፈለኩ።

አንደኛው ዶ/ር ፊል የሚባል ሲሆን በሙያው የሥነ-ሕይወት ባለሙያ (ባዮሎጅስት) እና የኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ እውቀትን ደራርቦ የያዘ ሊቅ የሚባል ሰው ነው። ይህ ሰው በእኛ ፕሮጀክት እንዲካተት ጥያቄ ስናቀርብለት በደስታ ነበር የተቀበለው። ፈቃደኝነቱን ከገለፀልን በኋላ የትኬትና ሌሎች የሎጅስቲክስ ሥራዎችን ማዘጋጀትና ማመቻቸት የእኔ ድርሻ ስለነበረ ‹እንዴት፣ መቼ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት እንደሚችል› ጠየኩት።

ሁሉም ከአሜሪካ ተነሥተው የሚመጡት ከአሜሪካ (ዋሽንግተን) - ፍራንክፈርት - አዲስ አበባ - ባሕር ዳር የሚመጡ ስለነበረ በዚህ መንገድ ትኬት ለማመቻቸት ይመቸው እንደሆነ ጠየኩት። እርሱ ግን ቀጥታ ከአሜሪካ ወደ ፍራንክፈርት ሣይሆን ከጓቲማላ ፍራንክፈርት ድረስ በራሱ እንደሚመጣ እኔ ግን ከፍራንክፈርት -አዲስ አበባ - ባሕር ዳር መመለሻውን ደግሞ ከባሕር ዳር - አዲስ አበባ - ፍራንክፈርት - አሜሪካ (ዋሽንግተን) እንዳደርግለት ተስማማን።

በዚህ መሠረት ሁሉም ተመራማሪዎች በወርሀ ነሀሴ በአንድ ቀን ባሕር ዳር ከተማ ደረሱ። ዶክተር ፊልም በሰዓታት ልዩነት ባሕር ዳር ገባ። እኔና ዶ/ር ማርጋሬትም ጊዮን በሚባለው ሆቴል ውስጥ ‹የእንኳን ደኅና መጣችሁ› ራት አዘጋጅተን እግረ መንገዱንም ስለቆይታቸው መሠረታዊ መመሪያዎችንና ዕቅዶችን ገለጻ አደረግን።





ዶ/ር ፊል ነጭ ስስ ቲሸርት ለብሶ ሲታይ ከፍተኛ ድካምና መጎሳቆል ከገጽታው ላይ ይነበብ ነበር። በነገራችን ላይ ከእኔ ጋር በአካል ስንገናኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። በተደጋጋሚ ሰውነቱን ከላይ እስከ ታች ያካል። ማከኩን በተደጋጋሚ ባየውም ለጊዜው ይሄን ያህል አሣሣቢ ነው ብዬ ስላልወሰድኩት ቀለል አድርጌ ተውኩት።

በነጋታው በጠዋት ወደ ደብረ ታቦር ከተማ ተጉዘን እዛ ከሚገኝ ‹ሕብረት ሆቴል› ከሚባል አልቤርጎ ከያዝን በኋላ የእለቱን ሥራችንን ወደ አንደኛው ጥንታዊ ገዳም ሄደን ጀመርን። ሁሉም በየፊናው በተሰጠው የሥራ መስክ ሳይንሳዊ የናሙና አወሳሰድን ተከትሎ ፍተሻውን ጀመረ።

አንዱ ድንጋይ እየፈነቀለ በደረቱ የሚሣብ እንስሳ ይፈልጋል፣ ሌላው ጉንዳንና ሌሎች ነፍሳትን ያጠምዳል፣ የእፅዋት ርጋፊና የአፈር ውስጥ ንጥረ ነገር (Nutrient) ይመረምራል፣ እፅዋትን ይለያል፣ ከእፅዋት ላይ ያለውን የእንጨት ሽበት (Moses and Ferns) የምንለውን ይሰበስባል። ሥራው ባሰብነው መልክ እየሄደ ስለነበረ እጅግ አስደሳች ነበር። ቀኑን ሙሉ ስንደክም ውለን ማታ ደግሞ ቀን የሰበሰብነውን ናሙና በያዝናቸው የመስክ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች የበለጠ እያጠራን ወደ ሚቀጥለው መረጃ ደረጃ እናሳድጋለን። ያን ቀን በጣም ደክሞኝ ስለነበረ በጊዜ ተኛሁ። ራት የበላሁ እንኳ አይመስለኝም።

በሚቀጥለውም ቀን ሥራው ቀጠለ። ለእኔ የተሰጠኝ የሥራ ዘርፍ ማለትም ዕጽዋትን በዓይነትና በመጠን እየለዩ መመዝገብ ስለነበረ ከቦታ ቦታ አብራኝ ከምትሠራው የፒኤችዲ ተማሪ ጋር ስንቀሳቀስ እግረ መንገዴን ሁሉንም አያለሁ። ዶ/ር ፊልን ባየሁት ቁጥር ማከኩን አላቆመም ነበር። እንዳውም የተወሰነ ሰዓት ላይ ቲሸርቱን አውልቆ በጣም ሲያክ አየሁት።

አሁን ጉዳዩ እያሳሰበኝ መጥቷል። ሁሉም ተመራማሪዎች ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሉ ድረስ የመጀመያው ግንባር ቀደም ሓላፊነት የእኔ ነበር። በተለይም ይሄ ሰውዬ እመጣለሁ ካለበት ጊዜ ጀምሮ ከአሜሪካ ኤምባሲ በተደጋጋሚ እየደወሉ የምንሠራበት አካባቢ ሰላም መሆኑን፣ ከሱዳንና ከኤርትራ ድንበር ምን ያክል ሩቅ እንደሆነ ደጋግመው ጠይቀውኝ ስለነበር ጉዳዩን በቀላሉ ልተወው አልቻልኩም።

እንደዚሁ በግማሽ ጭንቀት በግማሽ ሥራ ላይ ውዬ ወደ ሆቴላችን ተመልሰን ማታ ራት ቀርቦ ስንበላ አሁንም ማከኩን አላቆመም ነበር። ‹ይሄ ሰው ወይ የምግብ ወይ የአካባቢ አለርጅ ገጥሞታል ማለት ነው። እናም ለሕይወቱ የበለጠ ሊያሰጋው ስለሚችል ሕክምና ማግኘት አለበት፤ የከፋ ነገርም ከሆነ መመለስ ይኖርበታል› አልኩና ልጠይቀው ወሰንኩ።

“ምን ሆነህ ነው የምታከው? በተደጋጋሚ እያየሁህ ነው፡ ችግር አለ እንዴ?” ብዬ ጠየኩት።

“ምንም ችግር የለም” አለኝ ፈገግ ብሎ።





“እንዴ ችግርማ ገጥሞሃል! ትላንትም እያየሁህ ነበር፡ ዛሬም ቀኑን ሙሉ ስታክ ነው የዋልከው። ከፍተኛ ስቃይ ውስጥ ያለህ ይመስላል እና የሕክምና እርዳታ ማግኘት ይኖርብሀ ይሆናል” አልኩት

“በፍፁም! ምንም የሚያሳስብ ነገር የለም” አለና ነገሩን አቃሎ ለማለፍ ሞከረ

“ምናልባት ለሆነ ነገር አለርጅክ ልትሆን ትችላለህ” አልኩ አሁንም።

“ባክህ አትጨነቅ። ጤናዬ ደኅና ነው አለርጅም የለኝም” አለኝ ተረጋግቶ። በስቃዩም መሃል ቢሆን በጣም ሳቂታና ተጫዋች ነው። እኔ ግን በቀላሉ ልለቀው አልቻልኩም።

“ይቅርታ አድርግልኝና ዶክተር! ላንተ ላይታወቅህ ይችላል ግን በጣም ነው የምታከው። የደኅንነታችሁ ጉዳይ ሓላፊነቱ የእኔ እንደሆነ ሳትረዳ አትቀርም።” ስለው

“ይህን ያክል የሚያስጨንቅህ ከሆነ ጉዳዩን ልንገርህ” አለኝና ታሪኩን ሲነግረኝ አፌን ከፍቼ ቀረሁ።

ላቲን አሜሪካ ውስጥ ጓቲማላ ከምትባል ሀገር ‹ቦት ፍላይ (Botfly) የሚባል አደገኛና አስገራሚ የዝንብ ዝርያ አለ። ይህ የዝንብ ዝርያ ወንዱና ሴቷ በሕይወት የሚኖሩት ለአስራ ሁለት ቀናት ብቻ ነው። አይመገቡም አይጠጡም። በዚህ ጊዜያቸው ውስጥ የመብላት፣ የመጠጣትና የመኖር ተልዕኮ የላቸውም። የአስራ ሁለት ቀን እድሜ ተልኳቸው

ወንድና ሴቷ ተራክቦ ፈጽመው እንቁላል መጣል ብቻ ነው። ሴቷ ዝንብ በተለይ የወባ ትንኞችን ስታገኝ ክንፋቸው ሥር እንቁላሏን ትጥላለች (ሰውም እንስሳትም ካጋጠማት ቆዳና ጸጉር ላይ ልትጥል ትችላለች)። የወባ ትንኟ ሰው ስትነክስና ደም ስትመጥ የደሙ ሙቀት እንቁላሉ በቅጽበት እንዲፈለፈል ያነሳሳዋል። የተፈለፈለውም ትል (Maggot/Larva) ይሆንና ወደ ሰውየው ገላ ቆዳውን በስቶ ይገባል። ትሉ የሰውዬውን ሥጋ እየበላ እስከ 30 ቀናት ከቆየ በኋላ ወደ ኩብኩባ (Pupa) ተቀይሮ በራሱ ጊዜ ከሰውዬው ገላ ወጥቶ አፈር ላይ ሲያርፍ ወደ ዝንብነት ይቀየራል። ዝንቡ እንደገና በ12 ቀናት ዕድሜው/ዕድሜዋ ተራክቦ አድርጎ እንቁላል በማስጣል ወይም በመጣል ያሳልፋል/ታሳልፋለች (አንድ ዝንብ እስከ 400 እንቁላል ልትጥል ትችላለች)።

ትል(Larva) በነፍሳት የሕይወት ኡደት ውስጥ የመብል ጊዜ (Feeding Stage) የሚባለው ስለሆነ በተለይም የዚህ ዝንብ ዝርያ ምግብ የሚበሉት በዚህ ዘመናቸው ስለሆነ በከፍተኛ ሁኔታ ቆዳውን በስቶ የገባውን ሰው ሥጋ እየበላ ወደ ሚቀጥለው የእድገት ደረጃ ይሸጋገራል። ትሉ ቀንድ መሳይ እሾህ በየደረጃው ስላለው የተሸካሚውን ሰው ሥጋውን ከመብላቱ በላይ የእሾሁ ውጊያ ለተሸካሚው ሰው እጅግ ስቃይን የሚያስከትል ነው። ተሳስቶ እንኳ ትሉን በመጫን ካፈረጠ ከውስጡ የሚወጣው መርዝ ከስቃዩ አልፎ ከፍተኛ መመረዝን ወይም ኢንፌክሽን በመፍጠር እስከ ሞት ድረስ የሚያደርስ በቁም ገሃነም የሚከት የዝንብ ዝርያ ነው። በጓቲማላ ገጠራማ





አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በዚህ የዝንብ ዝርያ እነርሱም የቤት እንሰሳዎቻቸውም የቁም ስቅል ለዘመናት ሲያዩ ኖረዋል።

ዶ/ር ፊል በተደጋጋሚ ለባዮሎጅ ምርምር ጓቲማላ በሄደበት ጊዜ ይህ ችግር መኖሩን በቅርብ ለመረዳት ችሏል። ስለዚህ መከላከያ ወይም ማርከሻ ወይም ማከሚያ የሚሆን መድኃኒት ለመቀመም ይነሳሳል። ይህንን ምርመር ለማድረግ ደግሞ የተደራጀና የዘመነ ላቦራቶሪ ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ ጓቲማላ ሳይሆን አሜሪካ እርሱ የሚሠራበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ እንደሆነ ገብቶታል።

ለምርመሩ ደግሞ በሕይዎት ያሉ ወንድና ሴት ዝንቦች ያስፈልጉታል። ስለዚህ ለምርምር እንዲሆኑት በርከት ያሉ ወንድና ሴት ዝንቦችን ሰብስቦ በጥንቃቄ ሳይሞቱበት ይዞ ወደ አሜሪካ ለመሄድ ይዘጋጃል። በአጋጣሚ ኤርፖርት ላይ በፍተሻ ይያዛል።

እንደሚታወቀው በዓለም አቀፍ የብዝሀ ሕይወት ቃል ኪዳን ወይም ባዮሎጅካል ኮንቬንሽን መሠረት በሕይወት ያለ እንስሳ ወይም ሊራባ የሚችል የእንስሳ ዘረመል፣ ሊበቅል የሚችል የእፅዋት ዘር፣ ተተክሎ ሊያቆጠቁጥ የሚችል የእፅዋት ዝንጣፊ፣ ደቂቀ-ሕይወት ያለው ነገር የተሸከመ አፈር ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር በልዩ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ማጓጓዝ የተከለከለ ነው። በዚህ ምክንያት ዝንቦቹን ማውጣት ስላልቻለ እጅግ አዝኖ ወደ አገሩ ወደ አሜሪካ ይመለሳል።

አሜሪካ ከገባ በኋላ ግን ጉዳዩ እረፍት ይነሣዋል። ምክንያቱም ትልቅ የምርምር ሥራ የሚጠይቅ፣ ትልቅ ግኝት የሚሆን፣ ግኝቱ ቢሳካ ደግሞ ለሰው ልጆች ስቃይ ማጥፊያና ለአገር ኢኮኖሚም አስተዋፅኦ የሚያደርግ በመሆኑ ነው። እናም ተመልሶ ጓቲማላ በመሄድ ዝንቦቹን ለማምጣት ብቸኛውን ዘዴ በአዕምሮው እንሰላስሎ ውሳኔ ላይ ይደርሳል።

እንግዲህ ወደ ኢትዮጵያ ወደ እኛ ፕሮጀክት ከመምጣቱ በፊት ጓቲማላ የሄደበት ምክንያት ቀደም ብሎ ያሰበውን ዘዴ ለመተግበር ነበር። ዕቅዱ እንዲህ ነው፡

ጓቲማላ ይሄድና አደገኛዎቹ ዝንቦች በብዛት ከሚገኙበት ገጠራማ አካባቢ እንደ ማንኛውም ጓቲማላዊ የገጠር ቤት ወስጥ ይተኛና በሴቷ ዝንብ ወይም እንቁላሉን በተሸከመች የወባ ትንኝ ይነደፋል። ሴቷ ዝንብ ካገኘችው ወይም ወባ ትንኝ ከነከሰችው እንቁላሉ ተፈልፍሎ ትሉ ከሰውነቱ ውስጥ ገባ ማለት ነው። ትሉ ሥጋ ስላገኘ የተለያዩ እድገቶችን በ30 ቀናት ውስጥ አልፎ ኩብኩባ ሆኖ መጨረሻ ሕይወት ያለው ለምርምር የሚበቃ ዝንብ ማግኘት ይችላል ማለት ነው። ይህን ሲያቅድ ቢያንስ ለ30 ቀናት ምድራዊ ሲኦል ውስጥ ሥጋውን/አካሉን እንደሚያቀይ አምኖበት ነበር።

በዚህ መሠረት ጓቲማላ በድሆች ቤት ተኝቶ በትክክል መነደፉንና ትሉ በሰውነቱ መግባቱን ሲያረጋግጥ ለሌላ ምርምር ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ይመጣል። ለዚህ ደግሞ ትሉ የ30 ቀናት እድሜ ስላለው በቂ ጊዜ ይሰጠዋል። ምክንያቱም





ከእኛ ጋር የሚቆየው ለአስራ አምስት ቀናት ብቻ ስለነበረ ነው። ከእኛ ጋር የነበረውን ጊዜ ጨርሶ ሲመለስ ትሉ ወደ ኩብኩባ ይቀየርና ከቀናት በኋላ ከሰውነቱ ቆዳውን ቀዶ ይወጣል። በእነዚያ የመፈልፈያ ቀናት ዶ/ር ፊል ላቦራቶሪው ውስጥ ሆኖ ይጠባበቃል። በመጨረሻ ቆዳውን በስቶ የወጣው ኩብኩባ ዝንብ ሆኖ ይፈለፈላል ማለት ነው።

በዚህ መንገድ የተከለከለውን ዝንብ በምሥጢራዊ ሕይወት-ኡደት ወደ ሀገሩ ማስገባት ስለፈለገ እግረ መንገዱን ደግሞ በሌላ የምርምር አጀንዳ ከእኛ ጋር ለመሣተፍ ፍላጐቱ ጥልቅ ስለነበር ወደ ኢትዮጵያ መጣ። ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ሰዓት ትሉ አስፈሪውን የእድገት ጊዜውን የጀመረበት ነበር። እናም የሚያከው በየቦታው ሰውነቱ ውስጥ የገቡት ትሎች ያለእረፍት ሥጋውን እየበሉት ስለነበር ነው!!

ይሄን ድርጊቱን ሲነግረኝ ለማመንም ለመስማትም እጅግ ዘገነነኝ። ቲሸርቱን አውልቆ ሲያሳየኝ ጀርባው፣ በጎን በኩል ሆዱ፣ የእጁ ጡንቻ በርካታ ስፍራ ላይ ተበሳስቶ ትሎቹ በቁስሉ ጫፍ አየር ለመተንፈስ ብቅ ሲሉ ይታያሉ።

ከናቲራው ስስ የሆነበት ምክንያት አከስጅን እንዳያጥራቸው እንደፈለጉት አየር እንዲያገኙ አስቦ እንዳደረገው ያወለቀውን ከናቴራ እየለበሰ ነገረኝ። እነርሱ ሥጋውን እየበሉ ቂም ስቅሉን ያሳዩታል እርሱ ግን እንዳይሞቱበት ደግሞ ይጨነቅላቸው ነበር።

በጣም ከመደነቄ የተነሣ፣

"ለምን ብለህ ነው? ለማን ብለህ ነው? እንዲህ በትል የምትበላውና የምትሰቃየው?" አልኩት በተለመደው የእኛ አስተያየት!

ትከሻዬን መታ መታ አደረገና፣

"ይሄ ለሙያዬ የሚከፈል ዋጋ ነው! አንድ ቀን ይሄን ዋጋ ኅቲማላ ትከፍለኛለች!" አለ።

ብዙ ሙያቸውን የሚወዱ ሰዎች እንዳሉ ባውቅም ሰው በቁሙ ለሳይንስ ብሎ በትል ሲበላ ሳይ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው። እርግጥ በኢትዮጵያ ገዳማትና ጥንታውያን አድባራት በተዘዋወርኩባቸው መልካም ጊዜያቶች ውስጥ በገድላት ላይ አንዳንድ መናንያን በተደጋጋሚ ለጸሎት በመቆማቸው የተነሣ ሰውነታቸው ስለሚቆስል ይተላል። ተልቶ ትሉ ከሰውነታቸው ወጥቶ ሲሄድ ‹ይህ ላንተ የተፈቀደልህ ነው› ብለው ትሉን መልሰው ወደ ሰውነታቸው ያስገቡ ነበር የሚል አንብቤ ነበር። በተለይ በታላቁ ደብር በአቡነ አሮን ገዳም እንደዚህ ዓይነት ትልቅ አባት እንደነበሩ ተረድቼ ተደንቄ ነበር። በምናኔው ዓለም እንዲህ ያለ ነገር እንዳለ ቀደም ብዬ የማውቅ ቢሆንም ዘመናዊና ቅንጡ በምትባለው አሜሪካ ውስጥ ለሣይንስ ሲባል ራሱን እንደ መናኞች ለትል አሣልፎ የሰጠ ሰው ይኖራል ብዬ ግን ላንዳፍታም አስቤው አላውቅም ነበር።





አሜሪካ ሲባል ብዙዎቻችን የምናውቀው በቀይ ምንጣፍ የሚመላለሱ ፊታቸውን በቀለምና በፓውደር የተቀባቡ ሞልቃቃ የፊልም ተዋንያንና ዘፋኞችን ብቻ ይመስለናል። ቁራጭ ጨርቅ ለብሰው እርቃናቸውን በቴሌቪዥን የሚታዩትና ‹ተጋቡ ተፋቱ› የሚባልላቸው ብቻ ይመስሉናል አሜሪካውያን! እንደነዚህ አይነቶቹ አሜሪካ ቀሪውን ዓለም የምታደነዝዝባቸው ሞረፌን ናቸው!

አሜሪካን ግን አሜሪካ የሚያሰኟት ብልጭልጮቹ አይደሉም። በተዘጋ በር ውስጥ በትልቅ ፋብሪካ የብረት አረር የሚያነዳቸው፣ በእያንዳንዱ ላብራቶሪ ውስጥ ኬሚካል የሚያቃጥላቸው፣ በየጫካው በትል የሚበሉና ከአውሬ ጋር የሚታገሉ፣ ከምድር ወለል በታች መስኮት በሌለው ቢሮ ውስጥ 18 ሰዓት የሚሠሩ ሳይንቲስቶች፣ መሀንዲሶች፣ ባለሙያዎች አገር ናት አሜሪካ!

በየቀኑ የምትነግረንና የምታሣየን ብልጭልጮቹን እንጅ እንደዚህ ለሙያ የተሰጡትን የአገር ዋልታና ምሰሶ የሆኑትን ሣይንቲስቶች ተጋድሎና ምግባራቸውን ነግራን አታውቅም አሜሪካ!!

እጅግ ከመደነቄ የተነሣ ከተቀመጥኩበት ለደቂቃዎች ፈዝዠ ቀረሁ። የራሴን፣ ለሙያዬ ያለኝን ቀናነት፣ ለሙያዬ የምሰጠውን ክብር እና ለአገሬ የምከፍለውን መስዋዕትነት በአጠቃላይ ለሰው ልጅ ሕልውና የማደርገውን መናኛ አስተዋጽኦ ሳስብ ከዚህ ሣይንቲስት ጋራ አብሬ በአንድ

መስከ መሰለፌ በአንድ በኩል ትልቅ እድልና ክብር ቢሆንም በሌላ ግን ሀፍረት ነበር።

ሁለተኛው አስደናቂው ሰው ፕሮፌሰር ሀሮልድ ይባላሉ። በወቅቱ እኛ ጋ ሲመጡ ጡረታ ወጥተው በትልልቅ ምርምር አልፎ አልፎ ሰዎችን በማማከር ካልሆነ በስተቀር በዕረፍት ያሉ የ80 ዓመት አዛውንት ነበሩ። ፕሮፌሰር ሀሮልድ የእኔ ተባባሪ ዶ/ር ማርጋሬት ሎማን የድህረ ምረቃ ፕሮፌሰር የነበሩ ሲሆን ይሄንን ታሪክ የነገረችኝ እርሷ ናት። ከእርሳቸውም አረጋግጫለሁ።

አውስትራሊያ በባሕርና በባሕር ዳርቻ ውስጥ የሚኖር መርዛማ የእባብ ዝርያ አለ። በነገራችን ላይ ፕሮፌሰር ሀሮልድ በሙያቸው የደረት ተሣቢ እንስሳት ተመራማሪ (Herpithologist) ሲሆኑ እኛም ጋ ያመጣናቸው በገዳማትና በአድባራት ዙሪያ ባሉ ደኖች ውስጥ የሚኖሩ የእባብ የእንሽላሊትና ሌሎች በደረት ተሣቢ ዝርያዎችን እንዲለዩና እንዲያጠኑልን ነበር። እነዚህ በደረት ታሳቢ እንስሳት ደመ-ቀዝቃዛ በመሆናቸው በስርዓተ-ምህዳር የምግብ ሰንሰለትና ሀይል ፍሰት ውስጥ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው ነው።

ፕሮፌሰር ሀሮልድ ከዕለታት በአንዱ ቀን የድህረ ምረቃ ተማሪዎቻቸውን ይዘው በዚህ መርዛማ እባብ ዙሪያ ገለጻ ለማድረግ ወደ አውስትራሊያ ጠረፍ ተጓዙ። ሰው የሌለበት እጅግ ሩቅ ጠረፋማ ቦታ ሲደርሱ ባሕር ውስጥ ጠልቀው በመግባት አድነው ይሄንን መርዛማ እባብ ይዘው ይወጣሉ።





ዓላማቸው የእባቡን የውጭ ገፅታ (Morphology)፣ የውስጥ አካላዊ መዋቅር (Anatomy) እንደዚሁ አጠቃላይ ውስጣዊ የሕይወት አመራሩን (Physiology) ለተማሪዎቻቸው ለማስጠናት ነበር።

ባላቸው የካበተ ልምድ እጅግ አደገኛ ከሚባሉት ከኮብራ እስከ ቫይፐር እባቦችን ያለ ምንም ስህተት መያዝ የሚችሉት ፕሮፌሰር ይኸንንም መርዛማ እባብ ከባሕር አውጥተው ከጭንቅላቱ ዝቅ ከአንገቱ ከፍ ብለው በእጃቸው እንቅ አድርገው ከያዙ በኋላ ለተማሪዎቻቸው ማሣየት ጀመሩ። ተማሪዎቻቸውም ማስታወሻቸውን ይዘው የፕሮፌሰራቸውን ገለጻ ማዳመጥ ቀጠሉ። ከእባቡ ደም እየቀዱ በላብራቶሪ እቃዎቻቸው እየሞሉ ሥራቸውን ለመጀመር ሲጣደፉ በምን ምክንያት እንደሆነ ሳይታወቅ ትልቅ ልምድ የነበራቸው አንጋፋው ፕሮፌሰር እባቡ ከእጃቸው ሸርተት ብሎ ነደፋቸው።

ቀደም ብሎ እንደሚታወቀው ይህ እባብ ከነደፈ መርዙ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሰውነት ጡንቻን በማሽማቀቅና በመጨረሻም እንዲዝል በማድረግ ሳንባና የመተንፈሻ ቧንቧዎች እንዲዘጉ፣ የልብ ምት እንዲቆምና የደም ስርጭት እንዲቋረጥ በማድረግ በ40 ደቂቃ ውስጥ እስከ ሞት የሚያደርስ እጅግ አደገኛ እንደሆነ ይታወቃል።

በዚህ ጠረፋማ ስፍራ አንጋፋው ፕሮፌሰር በዚህ የእባብ መርዝ መነደፍ ለተማሪዎቹ ትልቅ ዱብ እዳ ነበር። ለፕሮፌሰሩም ረጅሙ የሕይወት ጉዞ ማብቂያ ከ40 ደቂቃ በኋላ እንደነበር

የሚናገር መርዶ ነበር።

ተማሪዎቹ ተደናግጠው ሲተራመሱ ፕሮፌሰሩ ግን ተረጋግተው፡

"አብዛኛውን የሕይወት ዘመኔ በለፋሁበት ሙያ የመጨረሻውን አስቀያሚ ስህተት (Stupid Mistake) ሠርቻለሁ። ነገር ግን እንዲሁ መሞት አልፈልግም:: የሚቀረው 40 ደቂቃ ለሳይንስ እጅግ ውድ የሆነውን ስጦታ የማበረክትበት ነው። በማንኛውም የሰው ልጅ ላይ የእባብ መርዝ ስለማይሞከር አሁን የምታዩትና የምትመዘግቡት የማይገኝ የምርምር ውጤት ይሆናል። ስለዚህ መደናገጣችሁን ተውና አንዳችሁ ወደምትችሉበት ቦታ ሂዱና የሕክምና እርዳታ የሚገኝ ከሆነ ፈልጉልኝ። ሌሎቻችሁ ግን የትኛውን አካሌን መጀመሪያ እንደሚጎዳ፣ የትኛውን እንደሚያበላሽ፣ መጨረሻ እንዴት እንደሚገለኝ ምልክቶቹን ከጊዜ ጋር እያገናዘባችሁ በጥንቃቄ መዝግቡ" አሉ።

በዚህ መሠረት ተማሪዎቹ የፕሮፌሰሩን ቃል ሰምተው ግማሾቹ የልብ ምትን፣ ሌሎቹ አተነፋፈስን፣ ሌሎቹ ደግሞ በደቂቃዎች ልዩነት የደም ናሙና በመውሰድ፣ የዓይን ሽፋሽፍት በመግለጥ  የሚታይን ነገር በአጠቃላይ የእባቡ መርዝ በሰውነት የሚያደርሰውን ጉዳት  በጥንቃቄ መመዝገብ ያዙ። ይህ የማይገኝ የምርምር እድል ነበር!





ተማሪዎቻቸው ሚቼን ፕሮፌሰር አስተኝተው የመጨረሻውን ወርቃማ የቤተ ሙከራ ትምህርት እየመዘገቡ ባለበት ሰዓት ለመልካም ሰዎች መልካም ነገር አለና ሕክምና ፍለጋ የሄደው ተማሪ በአውስትራሊያ ውስጥ ‹ፍላይንግ ዶክተርስ› የሚባሉ (ብዙ ጊዜ በአውሮፕላን በመንቀሳቀስ የአንቡላንስ አገልግሎት የሚሰጡት) በአጋጣሚ በቅርብ ርቀት ስለነበሩ እነሱ አምስት ደቂቃ ሲቀር በአካባቢው አርፈው ለፕሮፌሰሩ የሕክምና እርዳታ መስጠት ቻሉ። ቀጥለውም  ወደ ሜልቦርን የሕክምና ማዕከል በማድረስ ፕሮፌሰሩን ከሞት ለማዳን ቻሉ።

ያ የምርምር ውጤት ወደፊትም ወደ ኋላም ሊመዘገብ የማይችል በመሆኑ ፕሮፌሰሩን በሙያቸው እጅግ የተከበሩ አደረጋቸው።

በሀገራችንም ይሁን በመላው ዓለም ብዙዎች ሕይዎታቸው ሳይሆን የእነርሱ ሥልጣን የሚያበቃ ከሆነ ሀገር ቢፈርስ ሕዝብ ቢሰቃይ፣ እነርሱ መምራት ያቆሙበት ተቋም እለቱን ቢናድ፣ እነርሱ የማያተርፉበት ንግድ ቢተራመስ በአጠቃላይ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል በሚሉባት ምድር ውስጥ እንደ እነ ፕሮፌሰር ሀሮልድ ያሉ ሣይንቲስቶች ራሣቸውን ለሰው ልጅ ዕውቀትና ብልጽግና  አሳልፈው የሚሰጡ መኖራቸውን ማወቅ ያጽናናል። ጨርሰን እንዳንጠላት ተስፋ እንዳንቆርጥባት ምድርን ውብ ያደርጓታል። ከራስ ወዳዶች ርካሽ ተግባርና ታሪክ  ይልቅ የበጎዎችና የጀግኖች ገድል ከፍ ብሎ ይሰማልና!!

ከእነዚህ ሁለት ሳይንቲስቶች ጋር ለአጭር ጊዜም ቢሆን ያሳለፍኩትን ጊዜ ዞር ብዬ ሳስታውስ እንደርነሱ ብቁና ለሙያዬ የተሰጠሁ ሆኜ ሀገሬን ባላኮራትም ቢያንስ ግን ተማርኩ ብዬ በትዕቢት እንዳላስቸግራት እቡይ ልቤን ሜዳ ላይ ጥለውት የሄዱ መሆኑ ይሰማኛል!!!





# ‹የተጠለው ቴፕ ሪኮርደር›

ስዊድን ለድህረ ምረቃ በተጓዝንበት ወቅት ከገጠሙኝና ከማልረሳቸው ነገሮች አንዱ ይህ ነው። ስዊድን ከመሄዳችን በፊት ከዛ አገር ሄደው ከተማሩ ሰዎች በአጠቃላይ አውሮፓ ደርሰው ከሚመጡ ሰዎች በተደጋጋሚ የሚነገርና የምንሰማው ነገር ነበር። ይኸውም ‹በዓላትን ጠብቆ ወይም በሆነ ጊዜ ሊጠቅም የሚችል ዕቃ አውጥተው ይጥላሉ› የሚል ነበር። ‹ቴሌቪዥን፣ ቴፕ፣ ፍሪጅ ሌላም ብዙ ዕቃ አውጥተው ይጥላሉ ያንን አንሥተህ ወስደህ መጠቀም ይቻላል› የሚል ነበር።

ብዙ ሰው እንኳን የሚያገለግል እቃ ቀርቶ እቃው ተጠቅልሎ የመጣበትን ማሸጊያ ካርቶንና የፀጉር ቅባት ጠርሙስ ቤት ውስጥ በክብር በሚያስቀምጥበት ድሃ ሀገር ውስጥ አድገን ይህን መስማት ተአምር ነበር።

ወደ ስዊድን የሄድነው ይህንን የመሳሰሉ የሚያማልሉ ትርክቶችን እየሰማን ነበር። ከዋና ከተማዋ ስቶኮሆልም 70 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከምትገኘው ‹ኡፕሳላ› ከተማ ውስጥ በአንድ አፓርትመንት ሕንጻ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጓደኞቼ ጋር አብረን እንኖር ነበር። ሁለት ሁለት ሆነን አንድ ክፍል ውስጥ እንኖራለን። በአንድ ረጅም ኮሪደር ግራና ቀኝ ባሉ ክፍሎች ኢትዮጵያውያንም፣ አሜሪካውያንም፣ አውሮፓውያንም እንዲሁም የሌሎች ሀገር ዜጎችም ይኖራሉ።

አንድ ቀን ዩኒቨርሲቲ ስንማር ቆይተን ስንመለስ ከአንደኛው ጓደኛችን መኖሪያ ክፍል ፊት ለፊት አንድ የሚያምር ሲዲ-ቴፕ ሪከርደር በር ላይ ቁጭ ብሏል። ከፊትም ከኋላም የነበርነው ጓደኞሞች ‹ዕቃ ይጣላል› የሚለውን ሰምተን ስለነበረ ይህን የሚያምር ግብዳ ቴፕ ሪከርደር ስናይ በደስታ ሰከርን። ወዲያው ቴፑ የተገኘበት ክፍል ፊት ለፊት ያለው ጓደኛችን ለእርሱ እንደሚገባ ሁላችንም በአንድ ድምጽ ብይን ሰጠን።

ቴፑን አንሥተን እየተንገዳገድን ጓደኛችን ቤት ይዘን ገባን። ያው ጓደኞችንም የደስ ደስ የቆርቆሮ ቢራ ከፍቶልን እንንበሸበሽ ጀመር። ትልቅ ደስታ ሆነ! እንደማስታውሰው በኢጋጣሚ አንድ ሰው የጥላሁን ገሰሰ ሲዲ ነበረውና ሲዲውን





አስገብተን በታላቅ ፌጩኸት ‹በሸንና፣ ዓለም ኮበለለች› እንል ጀመር።

መጠጡ በላይ በላዩ ወርዷል። ዳንሱም ቀልጧል። በየመኻሉ አጋጣሚው እንዴት አስደናቂ እንደሆነ፣ ያ ጓደኛችንም ምን ያክል እድለኛ እንደሆነ እያወራን ትልቅ ፌሽታ በምናደርግበት ሰዓት ድንገት በሩ በኃይል ተንኳኳ። የሙዚቃውን ድምፅ ቀንሰን አስታውሳለሁ እኔ ሄጄ ስከፍተው የሰማይ ስባሪ የሚያክለው አሜሪካዊው ጎረቤታችን ነው። ከዚህ በፊት እናውቀዋለን። ከጓደኛችን ክፍል ፊት ለፊት ካለው ክፍል ውስጥ የሚኖር ነጭ አሜሪካዊ ነው።

ቴፕ ሪከርደሩን ሲያየው ድንገት በምድር ላይ ያለውን የስድብ ዓይነት ሁሉ አወረደብን። እስከዚያች ቀን ድረስ ፈረንጅ ስድብ የሚያውቅ አይመስለኝም ነበር። ‹ምንድን ነው የሆንከው?› ለማለት ስንተባተብ ቴፑን እንደሰረቅነው ከተጨማሪ ስድብ ጋር ተናገረ። ባለንበት ደርቀን ቀረን።

ከመካከላችን ትንሽ ልብ የገዛ ሰው "እኛ ቴፑን አልሰረቅንም። መንገድ ላይ ተጥሎ አገኘነው ወደ ቤት አስገባነው" አለ።

ለካ እርሱ ክፍሉን እያፀዳ ኑሮ አገር ሰላም ብሎ ቴፑን ከኮሪደሩ ላይ አስቀምጦት ነበር። እኛ ደግሞ በሰማነው መሠረት ‹የተጣለ ቴፕ ነው› ብለን ወደ ክፍላችን ይዘን ገብተናል። ስለዚህ እኛ ‹የወደቀ እቃ አነሣን› ነው የምንለው እርሱ ደግሞ ‹ሰረቃችሁኝ› ነው የሚለው።

የሚችለውን ያክል ከሰደበን በኋላ ሁላችን በድንጋጤ ደርቀን ብንቀርም እንደምንም ተጽናንቼ ማናገር የቻልኩ እኔ ነበርኩ።

“የጣልከው ስለመሰለን ነው ያስገባነው። አሁንም ቴፕህን መውሰድ ትችላለህ። ስድብና ሌላ ነገር አያስፈልግም!” የሚል ኃይለቃል ተናገርኩ።

የቀሩትን ስድቦች ሰድቦን እያመናጨቀን ቴፑን አንሥቶ ይዞ ሄደ። የጥላሁን ሲዲም አብሮ ምርኮ ሆኖ ተወሰደ። ደፍሮ መልስልን ያለ የለም። ሁላችንም በዚያ ድንጋጤ ወደየክፍላችን ተበታተን።

ምናልባት ይህ ከሆነ ከአንድ ከሁለት ሰዓታት በኋላ ይመስለኛል ምን ሰይጣን እንዳሳሰበኝ አላውቅም ቴፑን ሰጥተነው ከነበረው ጎደኛዬ ላይ ልቀልድ ፈለኩ።

እናም ስልክ አነሣሁና ወደ ጓደኛዬ ደወልኩ። አፍንጫዬን በጣቶቼ አፍኜ ልክ የሌላ አገር ዜጋ የሚያናግር አይነት ባለው ቃና በተቻለኝ መጠን አውሮፓዊ ቅላጼ ባለው እንግሊዝኛ፡ “ይህ 505 ክፍል ነው?” አልኩት።

“አዎን” አለኝ። ድምፁ ውስጥ ድንጋጤ አለ።

“ከዋናው ሕንጻ አስተዳደር ነው የምደውለው። እንደዚህ አይነት አስነዋሪ ጠባይ በዚህ ሕንፃ ውስጥ የማንቀበለው ነው። እናንተ ክፍል ውስጥ ስርቆት ተፈፅሟል። ፖሊስ ጉዳዩን ስለደረሰበት መጥታችሁ ቃላችሁን እንድትሰጡ ስለተፈለገ አሁን በአስቸኳይ ታች እንግዳ መቀበያ (ሪሴፕሽን) ድረስ





እንድትመጣ!” ብዬ ስልኩን ዘጋሁ።

ሪሴፕሽን ማለት ህንፃውን የሚያስተዳድረው ሰው የሚቀመጠበት መግቢያው አካባቢ የመጀመሪያው ወለል ላይ ነው።

ጓደኛዬ በከፍተኛ ድንጋጤና በተቆራረጠ ድምጽ “እሺ… እሺ…” ሲል ይሰማኛል።

‹ሠራሁለት፣ አስደነገጥኩት!› ብዬ ስልኩን ዘግቼ ቁጭ አልኩ። ከአንድ 30 ደቂቃ እንደቆየሁ ግን የሆነ ነገር ዘገነነኝ። ‹እንዴ ምንድን ነው ያደረኩት?› አልኩና ተነሥቼ ወደ ጓደኛዬ ክፍል ሄጄ ሳንኳኳ ወዲያው አልከፈተልኝም። በኃይል ሳንኳኳ መጥቶ ከፍቶልኝ ወደ ውስጥ ስገባ ሻንጣ እያዘጋጀ ነው።

“እንዴ ምንድን ነው?” አልኩት

“ኧረ ተወኝ እባክ! እማራለሁ ብዬ መጥቼ ልዋረድ! በሀገሬ የወደቀ ቁልፍ አንስቼ የማላውቅ ሰው አውሮፓ መጥቼ በስርቆት ልጠርጠር?!” ቀጠለ

“እዚህ ቀዝቃዛ በረዶ ሀገር ታስሬ ልቀር ነው? ትምህርት ነው አይደል የሚቀረው ይቀራል! አሁኑኑ ወደ ስቶኮሆልም ልሄድ ነው” አለኝ።

“ምንድን ነው እስኪ ተረጋግተህ ንገረኝ” አልኩት

“ጊዜ የለም። ታች ፖሊስ እየጠበቀኝ ነው። በቅድሙ ቴፕ መጥተህ ማብራሪያ ስጥ ነው የሚሉኝ። ምንም የምሰጠው ማብራሪያ የለኝም። ስለዚህ ወስደው ነው የሚያስሩኝ” አለ

“እና ምን ልታደረግ ነው?” አልኩት

“አሁን በባቡር ተሳፍሬ ዛሬ ማታ ስቶክሆልም እገባለሁ። ኢትዮጵያ ኢምባሲ የሚሠራ ዘመድ አለኝ፡ ነገ በአውሮፕላን አሳፍሮ ወደ ሀገሬ ይልከኛል” አለ።

እንደ ቀልድ የሠራሁት መራራ ስህተት የታወቀኝ ወዲያው ነበር።

“እረ እባክህ እኔ ነኝ የደወልኩ ተረጋጋ” ስለው ማመን አልቻለም።

“እንዴ! ያልኩህ እንዲህ አይደለም?” ብዬ አፍጫዬን በእጄ አፍኜ ያልኩትን ደገምኩለት። እኔ መሆኔን ሲያረጋግጥ ድንገት ዘሎ መጥቶ በደስታ ተጠመጠመብኝ። ደስታው ወደር አልነበረውም።

ትንሽ ዘግይቼ ቢሆን ኖሮ ይሄ ጓደኛዬ ሻንጣውን ይዞ በባቡር ተሳፍሮ ስቶክሆልም ይገባ ነበር። እኔም ምን እንደሆነ ሳላውቅ በማግስቱ ወደ ሀገሩ ይመለሳል። በዚህ በማይረባ ቀልድ ከትምህርቱ ላሰናክለው እችል ነበር። ስለምዕራቡ ዓለም የምንሰማው ሁሉ ወደ ትንግርት የቀረበ ነው። ጨለማውን ብርሃን፣ ሸካራውን ለስላሳ፣ እሾኩን ጽጌረዳ አድርገን የተጋነነ ምስል በመያዛችን ልክ እንደኛ ቀሽም የሆነ ስህተት ላይ





ብዙዎች የወደቁ ይመስለኛል። ስንቱ በዚህ በተጋነነ ትንግርት ተታሎ ከሀገሩና ከባህሉ ተለይቶ ይሆን!

ይህ ጓደኛዬ በአሁኑ ሰዓት አንጋፋ ተመራማሪና ፕሮፌሰር ለመሆን በቅቷል። ይህንን አሁንም ድረስ ባሰብኩት ጊዜ ሁሉ እጅግ በጣም ይዘገንነኛል። የማይረባ ቀልድ ቀለድኩ ብዬ ብጃጃልም ቀድሜ በመሄዴ ግን ከትልቅ ጥፋትና ከሕሊና ፀፀት መዳን ቻልኩ!

# ተስፋ አስቆራጩ መምህሩ

ከዓለማያ ግብርና ዩኒቨርሲቲ በደን ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪዬን የጨረስኩት በጥሩ ውጤት ነበር ። ጥሩ ውጤት ሲባል በማዕረግ የሚባለው ደረጃ ውስጥ ይካተታል። በወቅቱ በማዕረግ የሚመረቁ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲው ውስጥ መምህር (ሌክቸረር) ሆነው የመቀረት ወይም በሌላ የምርምር ተቋማት ውስጥ ቅድሚያ አግኝተው ይቀጠሩና በጣም ባጭር ጊዜ ውስጥ የድህረ ምረቃ (የማስተርስና የፒ ኤች ዲ ዲግሪ) ትምህርት የመማር ዕድላቸው የሰፋ ነበር።

ከመጨረሴ በፊት በተለይ 4ኛ ዓመት እያለሁ የነበረኝ አጠቃላይ ውጤት ሲታይ ዩኒቨርሲቲው ውስጥ መምህር ሆኜ የመቅረት አጋጣሚዬ ከሞላ ጎደል የተረጋገጠ ይመስል ነበር። ያም ባይሆን ውጭ ወጥቼ በጣም ባጭር ጊዜ የድህረ ምረቃ ትምህርቴን እከታተላለሁ የሚል ተስፋ ነበረኝ። መምህሮቼም ሁሉ እንደዛ ዓይነት ተስፋ ነበራቸው።

ይሁንና የታሰበው ቀርቶ ያልታሰበው ሆነና ከአንድ ግለሰብ ጋር በተፈጠረ አለመግባባት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሳልቀጠር ቀረሁ። እንዲያውም የባሰ አለና እኔ በተመረቅኩበት ወቅት የመንግሥት ለውጥ ስለነበረ ከውጭም የሚቀጥረኝ አጥቼ ለአንድ ዓመት ያለሥራ ተጉላላሁ። ከአንድ ዓመት በኋላ ሥራ ይገኝ ገጠር ገባሁ።

የድህረ ምረቃ ትምህርት የመማር ተስፋዬም ከዕለት ወደ ዕለት እየተመናመነ ሄደ። ሁለት ዓመት አለፈ፣ አራት ዓመት ሆነ፣ ስድስት ዓመት ሞላኝ። በዚህ መኻል ለሥራ ጉዳይ ወደ ሐዋሳ ሄድኩኝ። በወቅቱ አብረውኝ ከተመረቁ ጓደኞቼ ውስጥ የተወሰኑት ወንዶገነት የደን ኮሌጅ ውስጥ ሌክቸረር ሆነው ግማሾቹ ማስተርሳቸውን ሠርተው ሌሎቹ ፒ ኤች ዲ ጀምረው ስለነበረ ‹ለምን እግረ መንገዴን ጎራ ብዬ ሰላም ብያቸው አልሄድም› አልኩና ወደ ወንዶገነት ደን ኮሌጅ አመራሁ።





ጓደኞቼን አግኝቼ በስኬታቸው ‹እንኳን ደስ አላችሁ› ብዬ እውነት ለመናገር በውስጤም ቅናት መሳይ እያብሰለሰለኝ ካፍቴሪያቸው ውስጥ ቁጭ ብዬ እያወራን እያለን የቀድሞው መምህሬ የነበረ (ዓለማያ ዩኒቨርሲቲ ማለት ነው) በወቅቱ በኮሌጁ ውስጥ ትልቅ ባለሥልጣን የሆነ ሰው መጣና ተገናኘን።

አልረሳኝም! ‹እንዴ! ደኅና ነህ ወይ? እንደምን አለህ? ሰላም ነህ ወይ?› የሚል ሞቅ ያለ ሰላምታ አዥጎደጎደልኝና፡

-ለመሆኑ ማስተርስህን ተማርክ?" አለኝ። ቀጠለና መልሴን ሳይጠብቅ "መቼም ተምረህ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡ አንተን እንደዚያ ነው የምጠብቅህ!" አለኝ።

-እረ አልተማርኩም" አልኩት ውስጤ እየተኮማተረ። እድሉን አጥቼ አልሳካልህ ብሎኝ እንጂ የመማር ጉጉቴ ከፍተኛ ስለነበረ ንግግሩ የውስጥ ስቃዬን አባባሰው።

-ምንም አይደለም ገና ወጣት ነህ አሁንም ትደርሳለህ። ብቻ አንድ ነገር የምመክርህ ግን..." ሲል የትምህርት እድል የማገኝበትን አቅጣጫ ሊያመለክተኝ ይሆናል አልኩና ሰፍ ብዬ ስጠብቅ፡

-መማር ከፈለክ እንዳታገባ!" አለኝ ፈርጠም ብሎ።

የሚገርመው በወቅቱ አግብቼ ነበር። እየተቅለሰለስኩ፡

-እረ አግብቻለሁ" አልኩት።

-ዋው!" አለና ትንሽ ቆይቶ "ኦኬ ግዴለም። ማግባትህ ምንም

አደለም። ብቻ ልጅ እንዳትወልድ፡ ልጅ ከወለድክ ምንም ተስፋ የለህም!” አለኝ። በወቅቱ ልጅም ወልጄ ነበር። እናም የመማር ተስፋዬን በር አንድ በአንድ እየዘጋብኝ እንደሆነ ቢሰማኝም፡

“ዶክተር ልጅም እኮ ወልጃለሁ” አልኩት። ብሽቅ አለና፡

“ምንድን ነው አንተ ይህን ያክል ያጣደፈህ! በጣም ያሳዝናል! ለትምህርትህ ቅድሚያ አትሰጥም እንዴ!” አለኝ። ሕይወት በእቅድ ብቻ የምትመራ ሳይሆን አንዳንዴ በዕድልም የምትሆን ነበረችና ልቤ በሐዘን እንደተወጋ አንገቴን ደፋሁ። እርሱ ግን ቀጠለ፡

“ኦኬ አንድ ልጅ ምንም አይደለም! ባለቤትህም ቢሆን ልታሳድገው ትችላለች። ብቻ ግን ድጋሜ ሌላ ልጅ የሚባል እንዳትወልድ” አለኝ። የሚገርመው ከዚህ መምህሬ አስተሳሰብና ፍልስፍና በተቃራኒ አቅጣጫ ተጉዤ ነበርና እኔና ባለቤቴ ሁለተኛ ልጃችን ከተወለደ ሁለት ወራት ተቆጥረው ነበር።

ከመምህሬ አነጋገር የተነሣ ሕይዎቴን በትክክለኛ መንገድ በደንብ ሳላስብ የመራሁት መሰለኝና በራሴ ተናደድኩ። ፈጣሪንም ወደ ማማረር ገባሁ። የመማር ዕደሌ እየተመናመነ፣ በላዬ ላይም ተስፋ የመቁረጥ ትልቅ ቋጥኝ እየተጫነኝ እንደሆነ ተሰማኝ። ቆይቼ፡





-እውነቱን ልንገርህ ዶክተር! ሁለተኛ ልጅም ወልጃለሁ” አልኩት።

ካፍቴሪያው ውስጥ የትምህርት ቤት የቀድሞ ጓደኞቼ ሌላ ብዙ ስታፍም ሞልቷል። ሁሉም ባለተስፋ ነው። ግማሹ ድህረ ምረቃ ትምህርት ላይ ያለ እና ሌላውም አውሮፓና አሜሪካ ለመማር እርግጠኛ የሆነ ነው። እንግዲህ በዚህ መኻል ነበር እኔ ተስፋ ቢስ ሆኜ የቀረብኩት ማለት ይቻላል። ልክ ‹ሁለተኛ ልጅ ወልጃለሁ› ስል፡

-አይ አንተ በቃ ዋጋ የለህም! ሕይወትህን በአግባቡ የማትመራ ሰው ነህ! በጣም አዝናለሁ እኔ እኮ ተስፋ ያለህ መስሎኝ ነው!” አለኝና “በል ለማንኛውም ደኅና ሁን...ምናምን” ብሎ ሌሎቹን ሰላም ብሎ ሄደ። ስሜቴን የሚቀጥለው ስንኝ የሚገልጸው ይመስለኛል።

"አርዳ ጥላኝ ሄደች ዘልዝላ ዘልዝላ

እንግዲህ ተነሥቶ ሰው አይሆንም ብላ"

እውነት ለመናገር ያን ጊዜ በጣም የጠለቀ ጉድጓድ ውስጥ የከተተኝ መሰለኝና ሁሉ ነገር ሲጨልምብኝ ታወቀኝ። እውነትም በሕይወቴ ልክ ያልሆነና የተቻኮለ ውሳኔ ያሳለፍኩና መንገዴም የተሳሳት መስሎ ተሰማኝ። ወደ ጋብቻ ስገባ የተነሳሁበትን የፈጣሪ ትዕዛዝና መርህ በአእምሮዬ ተፈታተንኩት።

ምንም ያልተሰማኝና ዘና ያልኩ መሰልኩና ጓደኞቼን ተሰናብቼ በውስጤ ግን ቅስሜ ተሰብሮ ተስፋዬ ተሟጦ ወደ ሐዋሳ ተመለስኩ። ጓደኞቼንና የቀድሞ መምህራኖቼን ሳገኛቸው ትምህርቴን የምቀጥልበትን ዕድልና ተስፋ ያሳዩኛል ስል ጭራሽ የሚያስከፋ ስሜት ደፉብኝ። ወደ ሐዋሳ ይህን እያብሰለሰልኩ ስሄድ ግን የሆነ እልህ መጣብኝ። አንድ ገጣሚ ያለው ታወሰኝ፡

"ያመኝ የነበረው አያመኝም ተውኩት

ያስታማሚው ነገር ሲቸግር አየሁት"

እልህ ከፍ ወዳለ ጥረትና ትጋት ገፉኝ። የሚገርመው ይህን በተነጋገርን በ6ኛ ወሩ የማስተርስ ትምህርት እድል አገኘሁ። የማስተርስ ትምህርቴን ባጠናቀቅሁ በአጭር ጊዜ ውስጥ ደግሞ የዶክትራል ዲግሪዬን በጣም ጥሩ በሚባል ፕሮጀክት ለማጠናቀቅ ቻልኩ! የሰውና የፈጣሪ እቅድና መንገድ የተለያዩ ነው። ከሰው ይልቅ ፈጣሪ ያሰበው ደግሞ እጅግ ውብና የተሻለ ነው!

ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው በሕይወቴ ውስጥ መልካም ነገሮች ወይም ስኬት ብዬ ከማስባቸው ውስጥ ማስተርስ ዲግሪዬ ወይም ዶክትሬት ዲግሪዬ አይደለም። ልጆቼ፣ ትዳሬ፣ ቤቴ ናቸው! በሕይወቴ ትልቁ ቁም ነገር፣ ትልቁ ስኬቴ እነርሱ ናቸው! እናም አሁን ሆኜ ሳስበው የተጓዝኩበት የሕይወቴ አቅጣጫ ትክክል ነበር። አካሔዴም በእኔ ምኞትና መምህሬ





ባሰበልኝ ሳይሆን ፈጣሪ በመረጠልኝ ስለነበር በጎ መሆኑን የኋላ ኋላ ተገንዝቤያለሁ።

እናም በሰዎች ዘንድ ተስፋ የሌለን ብንመስልም እንኳን ዋናው ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ተስፋችን ነው። ሕይዎት ጠመዝማዛም ብትሆን ውብና ተስፋን የተሞላች ናት! በዚህ ዓለም ሁሉ ነገር አበቃ፣ አከተመ ባልንበት ጊዜ የሚቀጥል የተሻለ እድል፣ የምናውቀውና የተለመደው በር የተከረቸመ ቢመስልም ወለል ብሎ የሚከፈት ሌላ በር፣ ዙሪያችን ጭው ያለ በርሃ ቢሆንም የለመለመ መስክ የሆነ ስፍራ ላይ እንዳለ ተምሬያለሁ። ዕድል ፊቷን ያዞረችብን በመሰለን ጊዜ እንኳ ቢሆን አብዝቶ በትጋት መጓዝ እንጂ ተስፋ መቁረጥ አይገባም። ትጋት የተስፋ ልጅ ናት። ተስፋ ደግሞ በእኛና በፈጣሪ መካከል የእምነት ድልድይ ስለመኖሩ ማረጋገጫ ነውና!

‹ዛፍ ቢቆረጥ ደግሞ ያቆጠቁጥ ዘንድ፡ ቅርንጫፉም እንዳያልቅ ተስፋ አለው› እንዲል መጽሐፍ።

# ቢዝነስ ክላስ

በብዙ ጉዳዮች አጋጣሚ ዓለም ዓቀፍ ጉዞዎችን አደርጋለሁ። ረጃጅም የሚባሉ የአውሮፕላን ጉዞዎችን አድርጌ አውቃለሁ። ግብዣ ሲደርሰኝም ሆነ በራሴ እቅድ ስጓዝ ሙሉ ለሙሉ ማለት ይቻላል የምጓዘው ኢኮኖሚ ክላስ በሚባለው የአውሮፕላን መሳፈሪያ ደረጃ ነው። በአውሮፕላን ጉዞ ቢዝነስ ክላስ፣ ፈርስት ክላስ፣ ኢኮኖሚ ክላስ የሚባሉ ማዕረጎች አሉ። ቢዝነስ ክላስ መስተንግዶ ቸው፣ የመቀመጫው ስፋትና ምቾት ከፍ ያለ ቢሆንም ዋጋው እጅግ ውድና ከኢኮኖሚ ክላሱ ከሞላ ጎደል እጥፍ ሊሆን ይችላል። ምቾቱን ገብቼ ባላየውም በአንድ አውሮፕላን ውስጥ እጥፍ ከፍሎ በቢዝነስ

ክላስ መጓዝ ቅንጦት ይመስለኛል። ገንዘብ የማባክን ያክል ይሰማኛል።

ስለዚህ ብችልም ባልችልም በቢዝነስ ክላስ መጓዝን ምርጫዬ አድርጌ አላውቅም። ሁልጊዜም የምጓዘው በኢኮኖሚ ክላስ ነው። ባደረኳቸው ሁሉም ጉዞዎች በኢኮኖሚ ክላስ ስጓዝ ደስ ብሎኝ ነው። ከማደርጋቸው ጉዞዎች ውስጥ የሚያስደስተኝ ነገር ቢኖር የአውሮፕላን ውስጥ በረራ ነው። ረጅም ጉዞም ቢሆን። ቀደም ብዬ አውሮፕላን ማረፊያ እገኛለሁ። ተሳፋሩ ሲባል ቀድሜ እሰለፋለሁ። ከግርግር በፊት ተረጋግቼ መቀመጫ ወንበሬን እይዛለሁ። አውሮፕላኑ ሰማይ ላይ ሲሆን ፊልም አያለሁ፣ መጽሐፍ አነባለሁ፣ እጽፋለሁ፣ በቃ መዝናናትና ነጻነት ይሰማኛል። ወንበሩ ጠቦኝም ተማርሬም አላውቅም። በቂ ምግብ ይቀርባል። መጠጥም አስተናጋጆቹን በመጠየቅ መደጋገም ይቻላል።

በአንድ ወቅት ወደ ደቡብ አፍሪካ ጁዋንስበርግ ከተማ ለሥራ ጉዳይ ለመሄድ  ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ስደርስ ድንገት ‹ዛሬ እንኳን ለምን  በቢዝነስ ክላስ አልሄድም› አልኩኝ ለራሴ። ምን እንደነካኝ አላውቅም። ግን ዝምብሎ ሁኔታውን የማዬት፣ አዲስ ነገር የመሞከር ጠባዬ ያመነጨው መሰለኝ። ስለዚህ ቦሌ አውሮፕላን ጣቢያ ከሚገኘው ትኬት ቢሮ ጎራ አልኩና  የመሄጃውን ብቻ ከኢኮኖሚ ክላስ ወደ ቢዝነስ ክላስ አሳደኩኝ።





ተሳፈሩ ተባለና ቅድሚያ ተሰጥቶኝ ወደ ቢዝነስ ክላስ ስገባ የነበረው አቀባበል መስተንግዶው እጅግ ተለየብኝ። ኮትህን ይቀበሉህና በሥነ ሥርዓት ይሰቅሉታል። መቀመጫው ምቹና ሰፊ ብቻ ሳይሆን እንደ አልጋ ተዘርግቶ ይተኛበታል። ምግቡና መጠጡ በገፍ ይቀርባል። ‹በቃኝ› ስትል እንኳን ያግደረድሩሃል። የልዑል ያክል ይንከባከቡሃል። የአስተናጋጆች ፈገግታና ትህትና የሌለህን ማዕረግ የሌለህን ክብር የተጐናፀፍክ ያክል ይሰማሃል። በዚህ ሁኔታ በምቾት እየተንፈላሰስኩ የአራት ሰዓት ተኩል በረራ ጨርሼ ደቡብ አፍሪካ ገባሁ።

ደቡብ አፍሪካ ሥራዬን አጠናቅቄ ከሦስት ቀናት በኋላ ስመለስ ‹አይ በቃ! ቢዝነስ ክላስ የሚባለውን አየሁት አይደል! ድጋሜ በቢዝነስ ክላስ መሄድ ገንዘብ ማባከን ነው› አልኩኝና በኢኮኖሚ ክላስ ለመመለስ ወሰንኩና ትኬቴን ሳላስቀይረው ቀረሁ። ሰዓት ደረሰና አውሮፕላኑ መጥቶ ተሳፈሩ ሲባል እንደተለመደው ወደ አውሮፕላኑ ኢኮኖሚ ክላስ አመራሁ። አውሮፕላን ውስጥ ገብቼ የቢዝነስ ክላሱን ትቼ ወደ ኢኮኖሚ ክላስ ስዘልቅ ልክ የፍዬልና የበግ ጉረኖ (ማደሪያ) የገባሁ ያክል ተሰማኝ። ሰው ሻንጣውን ለማስቀመጥ ቦታ ይያዛል በሚል ይራኮታል። በቃ ትርምስ ነው። ወንበሮቹ እንዴት ጠባብ ሆኑ? ኮትክንና ጃኬትክን ጭንህ ላይ መሸከም ግዴታህ ነው። እንቅልፍህ ከመጣ እንደ በግና ፍየል በተቀመጥክበት ማሸለብ ነው። ምግብ ሲቀርብ ውስን ምርጫ ቢኖርም ለምንዱባን የሚሰጥ ምጽዋት ወይም ለገዳም መናኝ የሚሰጥ

መቁኑን መሰለኝ። መጠጥ መጨመር የሚቻል ቢሆንም አፍ አውጥተህ ጠይቀህ ነው እንጂ ‹እባክህ ጨምር› ብሎ የሚያግደረድርህ የለም። በአእምሮዬ ውስጥ ተቀርፆ የነበረው የቢዝነስ ክላስ ምስሉ ለካ እንዳለ ነው።

እንዳጋጣሚ ከጎኔ የተቀመጠችው ሴትዮ የሰማይ ሰባሪ ታክላለች። ግዙፍ አካልዋ ከመቀመጫው ተርፎ ተከሻዋና ክንድዋ የእኔን መቀመጫ ዕሩቡን ሸፍኖታል። ከእርሷ ጎን ተቀምጬ ለሚያስተያየን ሰው ሚስተር ቢን ከአሻንጉሊቱ ጋር ጎን ለጎን ተቀምጦ ሊመስለው ይችላል። እንደምንም ሰቅስቄ ተቀመጥኩ። ክንድዋን ከከፊል ትከሻዋ ጋር እንደ ባላ ደግፌ መቀመጥ ግዴታዬ ሆነ። የክንዷ ክብደት የቀረሮ ግንድ ጉማጅ የወደቀብኝ ያክል ይሰማኛል። ቢዝነስ ክላስ እኮ ወንበርህ ከጎንህ ካለው መንገደኛ መቀመጫ ጋር እንዳይገናኝ ትልቅ ድንበር አለው። ለማውራት ስትፈልግ እንኳ ተንጠራርተህ ነው። ‹ለአራት ሰዓታት በላይ ይህቺን ሴትዮ ተሸክሜ እንዴት ነው የምዘልቀው?› ብዬ ተጨነኩ። ‹እባክሽ እጅሽን ሰብስቢልኝ› ብላትም አትችልም። ሰውነቷ ከወንበርዋ ሞልቶ ስለተረፈ ምን ማድረግ ትችላለች? የትስ ትወስደዋለች? እንደ ሻንጣዋ ቀንሳ ከላይ አትሰቅለው ነገር!። ‹በቃ ትከሻዬ መውለቁ ወይም መዛባቱ ነው። እንደምንም ችዬ ሀገሬ ስገባ ወጌሻ ዘንድ መሄድ ነው› ብዬ ራሴን አሳመንኩ። ግን ለምን መቀመጫው እንደዚህ ጠበበ!





በአንዲት ቀን ያውም ለአራት ሰዓታት ቢዝነስ ክላስን በማዬቴ ለብዙ ጊዜያት ስጓዝ በብዙ አየር መንገዶች ስመላለስበት ይመቼኝ የነበረው የኢኮኖሚ ክላስ በአንድ ጊዜ ወደ ማይመች፣ በጣም እወደው የነበረው ወደሚተራመስ ተቀየረና ሥርዓት የሌለው አስቀያሚ ሆኖ ታዬኝ። ‹ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው› ሆነና ጭራሽ የሴትዮዋን የተረፈ ገላ ስሸከም ጊዜ አንገሸገሸኝ። እናም ከዚያ ወዲህ በገዛ እጄ ሲመቸኝ የነበረውን የኢኮኖሚ ክላስ ወደማይመች ቀየርኩት።

በዚህ ዓለም ከላይ ስንደርስ ታች የነበርንበት ከንቱ ይሆናል፣ የጨበጥነውን እንረግጣለን፣ ክብር የሰጠነውን እናዋርዳለን፣ ‹ከዚህ በላይ የለም› ያልነውን ተራ ነገር እናደርገዋለን! ዓለሙ እንደዚሁ ነው። ንፋስ እንደመከተል ነው፣ የሚያረካ የሚያስደስት ምንም ነገር የለም።

የምቾት ችግሩ ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ መመለስን አለመፍቀዱ፣ ወደ ላይ እንጂ ወደ ታች መውረድን አለመፈለጉ ነው። ምቾት ጥሩ ቢሆንም ከደረጃ ላለመውረድ የሚያስከትለው ትግል በራሱ ጭንቀት ፈጥሮ ቆይቶ ምቾትን መልሶ መንሳቱ አይቀርም። በምቾት ውስጥ ምቾት የለም!

አሁን ድረስ የውጭ ጉዞ ሲኖረኝ ‹በቢዝነስ ነው በኢኮኖሚ ክላስ የምሄድ?› የሚለው የሚያሳስበኝ ጉዳይ መሆኑን እኔኑ ይገርመኛል። ‹የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች› መሆኑም አይደል?!

# <ዝም ብለህ ተናገር>

ይህ ምክር ነው! ምክሩ ግን ለሥልጣን ፈላጊዎች ብቻ ነው! እውቀትና ልምድ፣ ራዕይና ግብ፣ ሞራልና ሓላፊነት የማይሰማህ ሁነህ ነገር ግን የሥልጣን ፍላጎት ካለህ የሚከተለውን ምክር አንብበህ ተግብር! ‹መፍትሄ ውዱቅ፣ መድፍነ ጽድቅ› ይባላል። አጽፈህ በጡንቻህ እሰረው ወይም ምላስህ ላይ ተነቀሰው!

ያዝ አንግዲህ!...

ባሳለፍከው ዘመንህም ይሁን በመጭው ጊዜ በተግባር ሜዳ ላይ ምን ውጤት እንዳመጣህ፣ ምን ልታስመዘግብ እደምትችል ሊመዝንህ የሚችል ማንም እንደሌለ ራስክን አሳምን።

ዋናው ነገር በትላልቅ ጉባዔና በስብሰባዎች ላይ ከማንም ቀድመህ ተናገር። ደጋግመህ ተናገር። ሲጀመርና ሲጠቃለል እንዳትረሳ ተናገር። ስምክንና አድራሻህን ሰጥተህ በታላቅ ስሜት ተናገር። ልብ በል! የምናገረው ምን ቁም ነገር አለው ብለህ ይዘቱን አትመርምር። ብቻ ማድረግ ያለብህን ሲመክርህ ልብ ብለህ ስማ!

በስብሰባው ካሉት ጉምቱ ሰዎች መካከል እና መድረኩን የሚመሩት ቱባ ባለሥልጣናት የሚናገሩትን ጭብጥና አጀንዳ በደንብ አዳምጥ።

ከዚያ እጅህን ታወጣና ዕድሉ ሲሰጥህ ‹አሁን ከመድረኩ የቀረበው እጅግ አስፈላጊ ነገር በመሆኑ ለማጠናከር ነው› ትልና ጉምቱው ወይም ቱባው ሰውዬ የተናገረውን ቁምነገር በአድራጊ (Active sentence) ተናግሮት ከሆነ በተደራጊ (Passive sentence)፣ በተደራጊ ተናግሮት ከሆነ በአድራጊ ቀይረህ በተመሳሳይ ድምፀት ተናገር።

ለምሳሌ ጉሙቱው ባለሥልጣን ‹መንግሥት ለድሃው ኅብረተሰብ ተደራሽ የሆነ አገልግሎት እየሰጠ ነው› ካለ አንተ ‹ድሃው ኅብረተሰብ የመግሥት አገልግሎት ተደራሽ እየሆነለት ነው› ትላለህ። እንዳትረሳው ቀመር ልንግርህ መድረክ ላይ "ቀበሮዋ በጉን በላችው" ከተባለ አንተ በጉ በቀበሮዋ የተበላበት ሁኔታ እንዳለ ትገልፃለህ።





ልብ በል! በይዘት አዲስ ነገር ወይም ወጣ ያለ አመጣለሁ ካልክ ከሠርክስ ገመዱ አድጦህ ወደክ ማለት ነው። ያልተባለና ያልታሰበ አትናገር! እንድትደግም እና እንድታስተጋባ እንጅ እንድትተልም አልተፈቀደልህም። የተለየና ያደገ ሐሳብ አምጥተህ መሪዎችን አትፈትን! ‹አምላክን አትፈታተነው› ተብሎ ተጽፏልና።

እናም ያልኩህን ከፈፀምክ እመነኝ በዚያ ጉባዔ ማብቂያ ምርጫ ካለ አንተ መመረጥህ እርግጥ ነው። ምርጫው የማዕከላዊ ኮሚቴ ይሁን ወይም የጠርዝ ኮሚቴ ትመረጣለህ። ሲሆን ሚኒስትር ያለዚያ ዳይሬክተር ሹመት በእጅህ ትገባለች። ሲሆን ሊቀመንበር ያለዚያ ፀሐፊነት ያንተ ናት።

የማስጠነቅቅህ ግን በጉባዔው ወይም በስብሰባው ማብቂያ ምን አይነት ምርጫ፣ ለምን ሥልጣንና ሓላፊነት እንደሆነ ቀድመህ አነፍንፍ። ያለዚያ የቀብር አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሆነህም ልትመረጥ ትችላለህ።

ለሕዝብ፣ ለድርጅት፣ ለመንግሥት ተቆርቋሪ ምሰል። ከፓርቲ ሰነድ ትንሽ ቅንጣቢ፣ ከሕገ-መንግሥቱ አንዲት አንቀፅ መጥቀስክን አትርሣ። አንተ ምን ቸግሮህ! ከፈለክ ከተባበሩት መንግሥታት ቻርተር፣ ከሰባዊ መብት ደንጋጌ፣ ከቬየናና ጄኔቫ ኮንቬንሽን ጥቀስ። የሆነ የሩቅ ምሥራቅ ወይም አፍሪካ ብትፈልግ ከአውሮፓ በግምትም ቢሆን ሀገር ጠቅሰህ ምሳሌ ስጥ። አትፍራ! ማንም ከኋላ ሂዶ የሚያረጋግጥ የለም! ብቻ አብዝተህ ተናገር። ንግግርክን አንጂ ተግባርክን የሚመዝን

ማንም የለምና አትሳቀቅ። የሆኑ አካላትን መውቀስና መኮነንክን አትርሣ። ፀረ-ሕዝብ፣ ፀረ-ሰላም፣ ጨቋኝ፣ አፋኝ መሆናቸውን በምሬት ግለፅ።

ግን ተጠንቀቅ! ከደገፍክ ልጥፍ ያልክ ጭፍን ደጋፊ ሁን! አለበለዚያ ደግሞ ጫፍ የረገጥክ ተቃዋሚ ሁን። ሚዛናዊ ለመሆን አትሞክር! ምን ማለት ነው? ጽንፈኛ ሁን ነው! ስለ ድህነት፣ ስለ ኑሮ ማሻሻያ፣ ስለ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት፣ ስለ ድንቁርናና ኋላቀርነት እንዲች ብለህ ትንፍሽ እንዳትል። ማንም አይሰማህምና! ይልቁንም የብሔር፣ የሀይማኖትና የቋንቋ ጭቆና ያለ የነበረ መሆኑን በብስጭት እያነሳህ ደስኩር። ያን ጊዜ ትኩረት ትስባለህ! ቴሌቪዥኑ፣ ራዲዮኑ፣ ጋዜጣው፣ ፌስቡኩ ከኋላህ ይራኮታል።

አንድ ጊዜ በዚህ መልክ የሰርከሱን ገመድ ተሻግረህ መንበር ላይ ከተቀመጥክ የመንበሩ /ወንበሩ/ ግርማ ሞገስ አዋቂ ያስመስልሃል። በማንኛውም ጉዳይ ማጠቃለያ ሰጭ አንተ ነህ! ካንተ ወዲያ የሚናገር የለም። አንተ ያሰርከውን የሚፈታ ማንም የለም!

ባለሙያው ወይም አዋቂ የተናገረውን ቁም ነገር ገልብጠህ መናገር ችለህ የለ? አሁን ገልብጠህ አንተ ስታቀርበው የተለየ ግርማ ሞገስ አለው። አልፎም መመሪያ ይሆናል። ይህቺ ናት የኢትዮጵያ የሥልጣን መንገድ!





ሕሊናህን አለማምደው! የድሆችን መከራ እንዳላዩ ማለፍ፣ የድሆችን ጩኸት እንዳልሰሙ መሆን፣ ሳያውቁ አዋቂ መምሰል፣ ሳይገድሉ ገሎፈሬ፣ ሳይዘሩ ማጨድን ራስክን አስተምረው። ካንተ ያነሱ እንጅ የተሻሉ ሰዎች እንዳሉ ፈፅሞ እንዳታስብ። የሞት ፈረስ መጋለብን፣ የቆሰለች ሀገርን መጋጥን ራስክን አለማምደው! የበላይህን እንጂ የበታችህን አታዳምጥ! ሲቃወሙህ አንዳንድ፣ ጥቂቶች ሲደግፉህ ደግሞ ሕዝቡ ማለትን ተማር።

መቼ እንደተወከልክ የሚጠይቅህ የለምና፥ የሆነ አካባቢ ሕዝብ ጠበቃና ተሟጋች እንደሆንክ በድፍረት ተናገር። ለጥፋትህ መሸፈኛ ካባ፣ ለክፉ ተግባርህ መሸሸጊያ ዋሻ አዘጋጅ። ወይ ከጎሣህ አሊያም ከሃይማኖትህ አለዚያም ከመንደርህ በውድቀትህ ጊዜ የምትመዘው ካርድ አዘጋጅ፤ አንተ ስትነካ የሚንጋጋ መንጋ ይኑርህ!!

መንጋ ለማግኘት ሕይወት የገፋቻቸውን፣ ኑሮ ያልሞላላቸውን፣ ተስፋ የጨለመባቸውን ወገኖች ለይተህ ያለርህራሄ በቁስላቸው እንጨት እየሰደድክ ስቃያቸውን እያባባስክ፣ የመከራቸው ምንጭ ካንተ በተፃፃሪ የቆመው መሆኑን እያመላከትክ ‹ጃዝ› ማለት ነው።

አሁን ከፈለክ አጋንንትን ሁሉ ጠርተህ የምድርን በረከት ልታጠፋ እንደምትችል፣ የሰላምና የመከራ፣ የሕይወትና የሞት ማህተም በእጅህ እንዳለ በምትችለው ሁሉ ያለይሉኝታ ግለፅ!!

ይህች ናት የዘመኑ የሥልጣንና የታዋቂነት መንገድ በመከረኛዋ ኢትዮጵያ!!

ሀገርና ሕዝብ አንተ ሙጫ ሁነህ ባታጠብቀው ኑሮ እንደ እንቧይ ካብ የሚናድ እንደ ትቢያ የሚበተን መሆኑን ያለይሉኝታ ደስኩር። የሕዝብን ታሪካዊ ቁርኝት፣ ማኅበራዊ መስተጋብር በመካድ አብሮነት የሌለው ዝርው በመሆኑ ካንተ ውጭ አብሮ የሚያኖረው እንደሌለ በየቴሌቪዥኑ መስኮቱ እየቀረብክ አስፈራራ፣ በየማኅበራዊ ሚዲያው ጻፍ አጽፍ። ‹ኢትዮጵያ ትፈርሳለች ወይስ አትፈርስም?› የሚል ክርክር ድንገት እያነሳህ ሽብር ፍጠር። ‹ሀገሪቷ ልትበታተን ትችላለች› ትልና መፍትሄው ካንተ ዘንድ ብቻ እንደሆነ ስትናገር አትፈር! መንጋህን እያንጋጋህ ታሪካዊ ዕሴቶችን በድፍረት ነቁር። ሀገርና ሕዝብ ቢረግምህም እንኳን ስልጣንና ገንዘብ ጋሻ መከታ ይሆኑሃልና አትሳቀቅ። ይሉኝታ አይኑርህ! ዓይንህን በጨው ታጥበህ ቅረብ! ደግሞስ ሆድ እንጂ ጭንቅላት ስለማይኖርህ አትጨነቅ!!

ጀግንነት ጨለማን በብርሃን፣ ድህነትን በብልፅግና፣ ግፈኛን በፍትህ ማሸነፍ ሳይሆን የከበረን በማዋረድ፣ የተቀደሰን በማርከስ፣ አንድነትን በመበተን ሆኗልና ደጋግመህ የተከበረውን ንቀፍ፣ ንፁህ ክርስቶስን በጲላጦስ አደባባይ ራቁቱን አቁመህ ክሰሰው። ለበጎ ሥራው የእሾክ አክሊል ድፋለት! እየደጋገምክ መስቀል ጫንበት! እናም በርባኑ አንተ ነጻ ወጥተህ በአደባባይ ትጎማለላለህ!





ልብ በል! የእውነት ፀሐይ ስትወጣ፣ ጨለማው ሲገፈፍ ምን ይውጠኛል ብለህ አትጨነቅ! ሆድ እንጂ ሕሊና የለህምና አንተ ሥጋ እንጂ ነፍስ የለህምና የነገን የጽድቅ ፍርድ መፍራት የለብህም!

ይህቺናት የዘመኗ ኢትዮጵያ የሀብትና የሥልጣን መንገድ፡ መፍትሄ ውዱቅ! መድፍነ ጽድቅ!

ሶበዝ

# የካሊፎርኒያው ፖበዝ

እንደ እ.ኤ.አ. 2016 በፈረንጆች የበጋ ወራት ካሊፎርኒያ ሳይንስ አካዳሚ ተጋባዥ ሳይንቲስት (Visiting Scientist) ሆኜ የመሄድ እድል ገጥሞኝ ነበር።

ካሊፎርኒያ ሳይንስ አካዳሚ በሳንፍራንሲስኮ ከተማ የሚገኝ ዓለም አቀፍ የሳይንስ አካዳሚ ነው። ይህ አካዳሚ የእንስሳት ዘረመል፣ በፎርማሊን ደርቀው የተዘጋጁ ነፍሳትና እንስሳት አካላት፣ የዕጽዋት ዘር፣ የቅጠልና የአበባ ናሙና ክምችት ባለቤት ሲሆን ልዩ ልዩ የፊዚክስ፣ የባዮሎጂ፣ የከርሰ ምድር ጥናት ውጤት ሞዴሎችንና ምስለ-ተግባር (Simulator) ያሰባሰበ የምርምርና የማስተማሪያ ማዕከል ነው። ከመሬት ወለል በታች ተቆፍሮ በተሠሩት ምሥጢራዊ እና እጅግ

ጥብቅ በሆኑ ክፍሎች ውስጥ ከመላው ዓለም የተሰበሰቡ ከ32 ሚሊዮን በላይ የደረቁ የዕፅዋትና የእንስሳት ናሙናዎች እና ህያው የእንስሳት ዘርመል በናይትሮጅን ማከማቻ በጥንቃቄ ተጠብቀዋል። አንዳንዶቹ ዝርያዎች በአሁኑ ወቅት ከምድረ ገፅ የጠፉ ጭምር ይገኙበታል። በአጠቃላይ አካዳሚው ‹የኖህ መርከብ› ነው ማለት ያስደፍራል።

እኔም የተጋበዝኩት በተለያየ ጊዜ ከኢትዮጵያና ከምሥራቅ አፍሪካ የተሰበሰቡ የዕፅዋትና የነፍሳት ዝርያዎችን ናሙና በማደራጀት ለማገዝ ነበር። በዚህ ቆይታዬ ሁሉንም በምሥጢራዊ ኮድ ተቆልፈው የሚጠበቁትን ክፍሎች የማየት ሁሉንም ናሙናዎች የመመልከት ዕድል ገጥሞኛል። አስፈሪውን የድራጎንን የደረቀ ናሙና እንዲሁም ቀለማቸው በቅጽበት የሚለዋወጥና በተለይ አሁን ታይተው ከዓይን የሚሰወሩ ፍጥረታትን የማየት አስደማሚ እውቀት አግኝቻለሁ። ‹Now you see me, now you don’t /አሁን ታየኛለህ፤ አሁን አታየኝም/› በሚባለው ክፍል ውስጥ ብርሃንና የሞሎውኪል ውህድ ቅይይርና ድብልቆሽ ተኣምር የሚባል ትዕይንት ለማየት ታድያለሁ።

በአንደኛው የሳምንቱ ቀናት ሁሌም እንደሚደረገው እንደ ተጋባዥ ሳይንቲስትነቴ በሠራኋቸው የምርምር ሥራዎች ዙሪያ ገለፃ እንዳደርግ (Public Lecture) ፕሮግራም ተያዘልኝ። ከቀኑ በስምንት ሰዓት ጀምሮ ለሁለት ሰዓታት ያክል። ይህን ፕሮግራም የምታስተናብረው ወጣት ለስምንት ሩብ ጉዳይ ላይ ኮምፒውተሬን ይዤ ከጉባዔ አዳራሽ (Lecture Hall) እንድገኝ ነገረችኝ።

በተባለው ሰዓት ደረስኩ። የሚያምር ግርማ ያለው ትልቅ አዳራሽ ነው። ከልጅቷ በስተቀር አንድ ሰው እንኳን የለም። እጅግ ተሳቀቅሁ። ኮምፒውተሩን ከ LCD ጋር አገናኝታ የድምፅ ማጉያው መሥራቱን በጥንቃቄ አረጋግጣ ዝግጁ መሆኑን ስትነግረኝ ለስምንት አስር ጉዳይ ሆነ። ማንም ሰው ዝር አላለም።

‹ብቃ ጥቁር ስለሆንኩ ንቀውኝ ነው፤ ከአፍሪካ ስለመጣሁ ርባና ቢስ ነው ብለው ትተውኝ ነው› እያልኩ አንገቴን ደፍቼ በበታችነት ስሜት ስንጨረጨር ቆይቼ ሰዓቴን ሳይ ለስምንት አምስት ደቂቃ ጉዳይ ይላል። ቀና ስል ምንም ኮሽታ ሳይሰማ፣ የወንበር ግርግር ሳይኖር አንጋፋዎቹ ሳይንቲስቶችና ቴክኒሻኖች አዳራሹ ውስጥ በጸጥታ እየገቡ ኑረል። ስምንት ሰዓት ላይ አዳራሹ ከአፍ እስከ ገደፉ ጢም ብሎ ሞልቷል። በመቅደምም በመዘግዬትም የሚባክን የደቂቃ ሽርፍራፊ የለም አሜሪካ!

ከነዚህ በምድር ቤት ውስጥ በተዘጋ ክፍል ዕድሜ ዘመናቸውን ምርምር ሲያደርጉ ከኖሩ አንጋፋ ሳይንቲስቶች ፊት ቀርቦ ሌክቸር መስጠት ሳስበው እንደገና አስፈራኝ። እንደምንም ተረጋግቼ ልክ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ገለጻዬን ጀመርኩ። በሚገርም ንቃትና ተመስጥኦ ያዳምጣሉ።

ምንም እንደማያውቅ ሰው በአንክሮ መከታተላቸውን ሳይ አድናቆቴም መገረሜም እየጨመረ ገለፃዬን ቀጠልኩ።

ከ40 ደቂቃ ገለፃ በኋላ ጥያቄና መልስ ቀጠለ። ልክ እንደ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ሁሉም እጁን እያወጣ ይጠይቅ ጀመር። እኔ ከምሰጣቸው ይልቅ እነርሱ ለዕውቀት ባላቸው የማወቅ ጉጉት ተደመምኩ። አውቄ የጨረስኩ የመሰለኝን በርካታ ጊዜያት አስታውሼ በራሴ ትዕቢት አፈርኩ።

በዚህ ሁኔታ 10 ሰዓት ላይ ፕሮግራሙ አለቀና ሁሉም እየመጡ እየጨበጡ የተለመደ የምስጋናና የማበረታቻ ቃላት እንዲሁም የአድራሻ ልውውጥ ስናደርግ ቆየን። መጨረሻ ላይ ቆሞ የነበረ አንድ አንጋፋ ሳይንቲስት ጠጋ አለና፣

“ገለፃህን ወድጀዋለሁ! በሥራህም ተደምሜያለሁ! እባክህ ፈቃድህ ቢሆን ነገ ማታ ቤቴ ራት ልጋብዝህ?” አለኝ።

ከጎኔ ቆማ የነበረችውን የመጀመሪያ ጋባዤና አብሬያት የምሠራትን ዶ/ር ኬሪን ዘወር ብዬ ሳያት፣

“ምንም የተለየ ፕሮግራም የለህም” አለችኝ። ‹ግብዣውን ተቀበል› ማለቷ ነበር። በዚህ መሠረት ከዶ/ር ኬሪ ጋር አብረን እንድንሄድ በሚቀጥለው ቀን ወደ ማታ 12 ሰዓት ተቀጣጥረን ተለያየን።

በተባለው ቀን ከዶ/ር ኬሪ ጋር ተያይዘን በሳንፍራንሲስኮ ከተማ ኮረብታማ ሥፍራ ላይ ወደሚገኘው ጋባዣችን ቤት አመራን።





ከኮረብታማ ሥፍራ ላይ የተሠራው መኖሪያ ቤት በታላቅ ግርማ ተከፍሶ ዘቅዝቆ ረግቶ የተንጣለለውን የሰላማዊ ውቅያኖስን እንዲያሳይ ተደርጎ የተሠራ ነው። ግማሹ የቤቱ ጣሪያ ከቁንጠኛ መስታዎት የተሠራ ሲሆን በምሽት ኮከቦችን እንዲያሳይ ወደ ጎን ደግሞ ሰላማዊ ውቅያኖስን እንዲያሳይ ተደርጎ የተሠራ በቃላት ለመግለፅ የሚከብድ ውበት ያለው ቤት ነው። እንዳዚህ ዓይነት ቤት በዞርኩባቸው ሀገራት አይቼ አላውቅም።

በሩ ላይ ደርሰን የመጥሪያ ደወል ስንጫን ዘመናዊው ባለግርማ በር ተከፍቶ ከጋባዣችን ጋር ፊት ለፊት ተገናኘን።

“እንኳን ደህና መጣችሁ!” ብሎ በወዳጅነት ስሜት ሁለታችንንም አቅፎ የሞቀ ሰላምታ አቀረበልንና “ስለመጣችሁ አመሰግናለሁ። እኔና ባለቤቴ በእጅጉ ክብር ይሰማናል” አለ። ቀጠለና

“Please allow me to introduce you my wife/ አባካችሁ ባለቤቴን ላስተዋውቃችሁ” አለና “Honey! our guest has arrived! Please come and meet him!” አለ ጮክ ብሎ። ( ማሬ! እንግዳችን መጥቷል ነይ እና ተዋወቂው እንደማለት ይመስላል) ።

እኔ የጠበኩት ለግላጋ አሜሪካዊት ወይዘሮ ቢሆንም ፈፅሞ ያልጠበኩት ሆነ። My wife/ ባለቤቴ የተባለችው ሴት ሳትሆን ከወደ ዳሌው የሰፋ ወንድ እየተቅለሰለሰ ብቅ አለ። አዙሮኝ ተፍገምግሜ ልወድቅ ምንም አልቀረኝም። ሚዛኔን የሳትኩ መሰለኝ። ለካ የተጋበዝኩት ግብረ ሰዶማውያን ቤት ነበር!

እንደኔ ጥብቅ ሃይማኖት ለሚከተል ሰውና ራሱን እንደ ሃይማኖተኛ የሚቆጥር ሰው በእንደዚህ ዓይነት ሥፍራ ራሱን ሲያገኝ ሊሰማው የሚችለውን መገመት አይከብድም። በዚህ ቅፅበት ሁለት ማንነቶቼ ተምታቱ። ራሴን እንደ ሃይማኖተኛና ፈጣሪን እንደሚፈራ ሰው እቆጥራለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ ራሴን የሳይንስ ሰው አድርጌ አስባለሁ። እዚህ የተገኘሁት በሳይንስ ሰውነቴ እንጂ በሃይማኖተኛነቴ አልነበረም። ምንም ይሁን ምን አክብረው በመጥራታቸው ድንጋጤዬን ሳላሳይ የታይታ ክብር ማሳዬት ይኖርብኛል። እናም ሁኔታውን ለቅጽበትም ቢሆን መቀበል የማይሻው ሀይማኖታዊው እኔነቴን አቅቤ ትንሽም ቢሆን የሞራል ኪሳራውን ሊቀበለው የሚችለውን ሳይንሳዊው እኔነቴን ለማሳዬት ሞከርኩ። እውነት ለመናገር በሕይወቴ ካጋጠሙኝ አስደንጋጭና ፈታኝ ክስተት ይሄ ዋነኛው ይሆናል።

በደመነፍስ እጄን ዘረጋሁ። ‹ሚስት› ተብዬውም እጅግ ቀፋፊ ልስላሴ ባለው እጁ ጨበጠኝና ይባስ ብሎ ሳብ አድርጎ አቀፈኝ። ጉንዳን የወረረኝ መሰለኝ። አቅፎኝ የቆያቸው ሴኮንዶች በድቅድቅ መቃብር ውስጥ ለዘላለም የተጣልኩ ያክል አስጨነቀኝ። አሰቃቂው የሰላምታው ሥነ ሥርዓት አልቆ ቤቱን መጎብኘት ያዝን። አሁን ባልየው እያስጎበኘን ‹ሚስት› ተብየው ወደ ወጥቤት ሄደ። ትንሽ ቀለል አለኝ።





ከውጭ እጅግ የሚያምረው ቤት ውስጡ ደግሞ የበለጠ ያስደምማል። ከንድፉ፣ ውበቱና ንፅህናው፣ ከዕቃ አቀማመጡ እስከ ጥራቱ በህልም እንጂ በእውን የሚታይ አይመስልም። እኔ ግን የውስጥ ስሜቴ የሚነግረኝ የፈራረሰና በሙታን አፅም የተሞላ፣ እባብና ጊንጥ የሚተራመሱበት ዋሻ እንደምጎበኝ ነበር። እንዲህ እየቀፈፈኝ ከአንድ ክፍል ወደ ሌላ ክፍል በድኔን ይዤ እጎተታለሁ። በመኻል ወይን ተቀድቶ ቀረበልን። አፈፍ አደረኩና ጭልጥ አደረኩት! በቃ ያለሁበትን መርሳት ፈለኩ! ራት መድረሱ ተነገረን።

በተንጣለለው የገበታ ክፍል ምግብ በያይነቱ ተደርድሯል። እንኳን ልበላው ላየው አስጠላኝ። ደጋግሞ የማስመለስ ስሜት ይሰማኛል። ይህንንም ለመቋቋም እስኪታዘቡኝ ድረስ ብዙ ወይን ጠጣሁ። አንድ ጐርሼ ብዙ እጠጣለሁ። ጋባገሮቹ ‹ባልና ሚስቱ› ስለሥራዬ ስለቤተሰቤ ደጋግመው እየጠየቁ ዘና ለማድረግ ይጥራሉ። በእውነቱ በጣም ትሑቶች ናቸው። እኔ ግን ባናገሩኝ ቁጥር ውስጤ ይተራመሳል።

ዶ/ር ኬሪ ደግሞ እንደ ደኅና ነገር "ከተጋባችሁ ስንት ጊዜ ሆናችሁ ምናምን" እያለች ትጠይቃለች። ባልዬውም ሚስቱን እያሽኮረመመ ይመልሳል። ‹ሚስት› ተብየውም ባልዬውን እየተቅለሰለሰ እየተመለከተ ይመልሳል። ነገረ-ሥራቸውን ሳይ የበለጠ ሁሉ ነገር አቅለሸለሸኝ። ከንግግራቸው እጅግ የገረመኝ ነገር ቢኖር ጋባዤ የሦስት ልጆቹ እናት የነበረችውን ወይዘሮ ፈትቶ ነው ይህንን ‹እንትን..› ያገባው። ኧረ ወዲያልኝ!

የጭንቅ ሁለት ሰዓታት አልፈው አመስግነን ስንለያይ ውጭ ድረስ ተከትለው ሁለቱም አቅፈው ስመው ተሰናበቱኝ። ያሳዩኝን ፍቅርና አክብሮት ልክደው የምችለው ነገር ግን አልነበርም።

መኪና ውስጥ ስንገባ ዶ/ር ኬሪ መቸገሬን ተረድታው ኑሮ፡

"በጣም ይቅርታ! ያልነገርኩህ በዚህ ደረጃ ትቸገራለህ ብዬ ስላላሰብኩ ነው" አለችኝ።

እኔም አምርሬ መከፋቴን ነገርኳት።

ዶ/ር ኬሪም መልሳ፡

"ያን ያክል ግን መጨነቅ አልነበረብህም። የራሳቸው ጉዳይ ነው" አለችኝ።

መልስ አልሰጠኋትም። ከራሴ ጋር ሙግት ላይ ነበርኩ፡

*"እኔን ያስጨነቀኝ የእነርሱ እንደዚያ መሆን አይደለም። እነርሱ የሆኑትን መሆን መብታቸው ቢሆንም እኔም የሆንኩትን መሆን መብቴ ነው። እነርሱን የመናቅ መብት ባይኖረኝም እኔም ጉዳዩን የመጥላት መብት አለኝ። እነርሱን በማየቴ በእኔ ላይ የደረሰው የሞራል ጫናስ? በሕሊናዬ ተከብሮ የኖረው እሴት እንዲገረሰስ ጫና ሲደረግብኝስ?"*

ዶ/ር ኬሪ ካረፍኩበት አፓርትመንት አድርሳኝ ዘወር እንዳለች ትውከት ያጣድፈኝ ጀመር። ጨጓራዬ ተገልብጦ የወጣ እስኪመስለኝ ድረስ ተናጥኩኝ። ገላዬን በሙቅ ውሃና





በሻምፖ በቡርሽ እየፈተኩ ታጠብኩ። ይህን ያክል ስሜቴ መናወጡ በእጅጉ ገረመኝ።

ምን ብናውቅ፣ የፈለግነውን ያክል መስተጋብራችን ቢሠፋ፣ የሰው መብት አክባሪዎች ብንሆንም የተሠራንባቸው የማኅበረሰብ ዕሴቶቻችን በቀላሉ አውጥተን የምንጥላቸው አለመሆኑ የገባኝ ያኔ ነው። የዕሴቶቹ ጥንካሬ የሚገባን ለመናድ ሲሞከሩ ነው።

ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩ በኋላ ይህን ስህተቴን ለንስሐ አባቴ ለመንገር ፈራሁ። በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተጽፎ የሚያውቁትን የኃጢያት ድርጊት በሐዲስ ኪዳን ‹እኔ በዓይኔ በብረቱ አየሁ፤ ከቤታቸውም ተጋበዝኩ› ብዬ ሕሊናቸውን ላለማቆሸሽ ብዙ ጣርኩ። በኔ ይብቃ ብዬ! ይሁን እንጂ መሬትና የንስሓ አባት የማይችለው የለምና ለመናዘዝ ደፈርኩ።

# የአስካሪስ ሕይወት

ጣሊያን ኢትዮጵያን ቅኝ ተገዢ ለማድረግ ወረራ አድርጋ በአምባላጌ፣ በመቀሌና በመጨረሻም አድዋ ላይ የእብሪት ወታደራዊ ዘመቻ ስትከፍት ጣሊያኖች በጦርነቱ ከራሳቸው ዜጋ በተጨማሪ በርካታ የሰሜን አፍሪካ፣ ህንድና ጥቂት ኤርትራውያንን በገንዘብ በመግዛት ግንባር ቀደም የጦር ተሰላፊ አድርገዋቸው ነበር። ስማቸውንም ‹አስካሪስ› ይሏቸዋል። በጦርነቱ ወቅት የገንዘብ ደመወዝ የሚሰጣቸው ሲሆን በሚሰጣቸው ገንዘብ ከሚዘምቱበት አካባቢ እህልና ሌላም ነገር እየገዙ መጠቀም ይኖርባቸዋል እንጅ ሬሽን አይሰጣቸውም። ብዙዎች ሚስትና ልጆቻቸውን አስከትለው የሚዘምቱ አገር የለሽ ከንቱዎች ናቸው። ጣሊያኖች በጦርነት

ወቅት ከፊት የሚያሰልፏቸው እነርሱን ሲሆን የጦርነቱ ስልት ማሟሻ፣ ኃይል መፈተሻና አደጋ ጠራጊ አድርገዋቸው ነበር።

ከጣልያን መኮንኖችና ወታደሮች በቀለሙ የሚለይ ዩኒፎርም የሚለብሱ ሲሆን ደረጃውም ከጣሊያኖቹ የወረደ ነበር። ይህ የቀለም ልዩነት በጦርነቱ ጊዜ ተለይተው እንዲታወቁ ለኢትዮጵያውያኑ ተዋጊዎች እረድቷቸዋል። ቁልፍ ቦታ ካልያዙ በስተቀር የኢትዮጵያውኑ ዒላማ ያነጣጠረው ጣሊያኖቹ ላይ ነበርና። ‹እረኛውን በለው ከብቶቹ ይበተናሉና› የሚል ስልት ይመስላል። የኢትዮጵያውያኑ የሞራል ልዕልና ጣሊኖችን እጅግ የሚያበሽቅ ከመሆኑም በላይ ሆድገቦቹ አስካሪሶች ቶሎ እንዲያፈገፍጉ የሚያደፋፍር ስለነበር የጦርነቱ አንድ ትልቅ ስልት እንደነበር ይገመታል።

አሳዛኙ ነገር በጦርነቱ ድል ቢገኝ አስካሪሶቹ የድሉ ባለቤትም አይሆኑም። ድሉ የጣሊያንና የጣሊያናውያን ብቻ ይሆናል። እነርሱ በገንዘብ የተገዙ እንደ ጠበንጃው፣ መድፉ፣ ጥይቱ ወይም ዕቃ ከሚያጓጉዙት አጋሰሶች እንደ አንዱ ናቸው። በጦርነቱ ወቅት ቢሞቱ ለሀገር ነፃነት፣ ለወገን ክብር፣ ለራስ ማንነት የከፈሉት ዋጋ ባለመሆኑ የሰማዕትነት ክብር የላቸውም። የሞቱት ለሆዳቸው ነውና ሆድ ደግሞ ከአፈር ተሠርቶ ወደ አፈር ሊመለስ የሚገባው ትቢያ ነውና ታሪክ ብሎ ነገር የለም ።





ሬይሞንድ ዮናስ የተባለ የታሪክ ፀሐፊ ስለ አድዋ ድል በጻፈበት መጽሐፉ (The Battle of Adwa) የመጀመሪያውን የአድዋ አካባቢ ጦርነት ሲዘግብ ‹ይህ ጦርነት የኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ የሚወስን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካን ዕጣ ፈንታ ጭምር ነበር› ካለ በኋላ ‹በዚህ ግንባር በአፍሪካውያን የሚመሩ አፍሪካውያንና በጣሊያን የሚመሩ አፍሪካውያን የተፋለሙበት ነበር› ይላል።

ድሉ በአፍሪካውያን ለተመሩት አፍሪካውያን ማለትም ኢትዮጵያውያን ሲሆን በሕይወት የተረፉትም የድሉ ባለቤት የሞቱት ደግሞ የድሉ ሰማዕታት ሆነው ዘላለም ይዘከራሉ። የኢትዮጵያውን ዘማቾች ልጆች የአባቶቻቸውን የጀግንነት ታሪክና የነፃነት ተጋድሎ በኩራት ይናገራሉ። የአስከሪሶች ልጆች ግን ስለሞቱትም ሆነ ስለተረፉት አባቶቻቸው ምን ብለው ያወራሉ? በጦርነቱ አካሉን ያጣውና ቁስለኛው አስከሪስስ ቆም ብሎ ሲያስብ ምን ይሰማው ይሆን?

“አሁን የኔ አሟሟት አሟሟት ነወይ

ክብርና ነፃነት አንድ ቀን ሳላይ”

ከማለት በስተቀር!

ከአደዋ ጦርነት በኋላ ዘግይቶ እ.ኢ.አ በ1949 ዓ.ም. በተፈረመውና የጦር ምርኮኞች አያያዝን በሚደነግገው የጄኔቫ ቃል ኪዳን ሰነድም ላይ ለቅጥረኞች የዓለም አቀፉ ሕግ ከለላና ጥበቃ አልሰጣቸውም። በጦርነቱ ወቅት ቢማረኩ

እንደ ታጋይ ተጋዳላይ አይቆጠሩም፡ እንደ ደረቅ ወንጀለኛ እንጂ። በቅጠረኝነት በሌላ ወገን ጦርነት ለገንዘብ ብቻ የሚሰለፉ አስካሪሶች ወይም በዘመናዊ አጠራር መርሲናሪስ (Mercinaries) በሞራል ሚዛን አሁንም ድረስ የቀለሉ ናቸው።

እንግሊዛዊው ፈላስፋ ጆን ሎክ (John Locke) ‹I own less fully mine› በሚለው የሞራል ትምህርቱ፡

*“ከተፈጥሮ (ከፈጣሪ) ያገኘናቸውና ከእኛ የማይነጠሉ መብቶች ከሆኑት ውስጥ ዋናው የሰው ልጅ ሕይዎት ነው። የሰው ልጅ ሕይዎት ለሽያጭ፣ ለንግድ፣ ለድርድር በማንኛውም መልኩ ሊቀርብ አይገባም”* ይላል።

ሎክ ሲያብራራም እነዚህ መብቶች ከእኛ እንዳይነጠሉ ሁነው ተሰጡን እንጂ የእኛ አይደሉም። ከእኛ የማይነጠሉ መሆናቸው ደግሞ የበለጠ የእኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

በአድዋው ጦርነት ሦስት ዓይነት ሰዎች ተሰልፈው ነበር፡

ሕይዎቱን ለነጻነት፣

ሕይዎቱን ለግፍ፣ እና

ሕይዎቱን ለገንዘብ አሳልፎ የሰጠ ናቸው።

ሞራልና እውነት ምንጊዜም ያሸንፋሉና ሕይዎቱን ለነጻነት ያሰለፈው ወገን አሸነፈ።





ይሁን እንጂ ከጦርነት ባሻገር አሁንም ድረስ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ‹የአስካሪስ ሕይዎት› የሚገፉ ተዋናያን በግልጽ የሚታዩ አይደለምን?!

ሰው እንዴት የእርሱ ላልሆነ ግብ፣ ለማይጋራው ርዕይ መተኪያ የሌላትን ክብርት ሕይወቱን፣ ድጋሚ የማትገኘውን ዘመኑን ለገንዘብና ለጊዜያዊ ጥቅም ለሽያጭ ያቀርባል?!

# <እንዲህ ብለህ ጻፍ>

ቻይና ጓንዡ ከሚባለው ግዛቷ ከአንዱ ከተማ ኤርፖርት ስንወጣ አካባቢው በሙሉ ማለት ይቻላል በግንባታ ክሬንና ማሽን ተሞልቷል። በቃ ጥድፊያው ለጉድ ነው። ‹ምንድን ነው?› ስንል ኤርፖርቱ አካባቢ በርካታ ሆቴሎችና የምርት ማሳያ ኤግዚቢሽን አዳራሾች እየተገነቡ ነው ተባልን። ሁሉም ቦታ የሚታየው ከተማ ማበልጸግ፣ ገጠርን ማሳደግ፣ መሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ ኢንዱስትሪ ፓረክ ግንባታ ነው።

ከመካከላችን አንዱ ሲደመም ቆይቶ፣

“እኛ ኢትዮጵያውያን ስምንተኛው ሺ ገብቷል፣ ዓለም ሊያልፍ ትንሽ ቀርቶታል እንላለን። ወይ ንስሓ አንገባ ወይ አንገነባ! ቻይና ግን ዓለም ገና አሁን የተፈጠረ ይመስል በግንባታ ትጣደፋለች!” አለና የምሬት ፈገግታ አላበሰን።

የጓደኞችን ቀልድ አዘል ምሬት ውስጤን ነካው። የሆነ ነገር በአእምሮዬ ውስጥ አቃጨለ።

“...ወደ ኢትዮጵያ ሰዎች እንዲህ ብለህ ጻፍ” አለኝ...

> “... ቻይና ትገነባለች! ቀን ከሌሊት፣ ዓመት እስከ ዓመት ትሠራለች! ድሆች ይበለፅጋሉ፣ ጋራ ሸንተረሩ አረንጓዴ ግምጃ ይለብሳል፣ አካባቢ ይጸዳል! ባቡሮች ይወነጨፋሉ፣ መኪኖች ይርመሰመሳሉ፣ መርከቦች ወደ መላው ዓለም ይቀዝፋሉ፣ ፋብሪካዎች ያጓራሉ! ንኩሌር ይብላላል፣ ወንዝ ይገደባል፣ የብስና ባሕሩን ድልድይ ይናኝበታል። ለድሃም ለባለጸጋም፣ ውድም ርካሽም ምርትና ሸቀጥ ይመረታል! ገኸ ወይም ሻጭ እንጂ ወዳጅና ጠላት የሚባል የለም! ዜጐች ያለዕረፍት ከሀገር ውስጥ እስከ መላው ዓለም ይታትራሉ!
>
> የተራራ ማፍረሻ የዋሻ መቅደጃ ደማሚት እንጂ የሚፈነዳ ቦንብ የሚጮህ ጥይት የለም! ስርቆትና ውንብድና የለም! በሙስና ለመዘፈቅ ስታስብ የስቅላት ገመድህን አብረህ መግዛት አለብህ! በሙያ እንጂ በጎጥና ጎሳ ተደራጅቶ ጠቦ ማጥበብ





> አይቻልም! የኢኮኖሚ ንግድ እንጂ የፖለቲካ ንግድ አይፈቀድም።
>
> እስካሁን ለመጣችበትም ለወደፊቱም ጉዞዋ የማንንም ቡራኬና ዕርዳታ አትሻም። ቻይና ልማቷም ጥፋቷም ተስፋዋም በታታሪ ልጆቿ እጅ ነው! ልጆቿ ደግሞ ሁሉን ይበላሉ፡ ሁሉን ይሠራሉ!”

ይህን ጽፌ ስጨርስ ‹ተቀበል› አለኝ ደግሞ፡

> “በሌላ በኩል የአፍሪካ ሀገራት ሕዝቦች የኅብረታቸው ምልክት የሆነውን ጽ/ቤታቸውን አዲስ አበባ ላይ ሲገነቡ የኅብረቱን ጽ/ቤት ከቻይና በእርዳታ ተቀበሉ። ልብ በል! የጥቁር አፍሪካውያን የኅብረታቸው ምልክት የሆነው ጽ/ቤታቸው የታነፀው ቻይና በሰጠችው ምፅዋት ነው። እውነታው ግን የአፍሪካ የራሷ ሀብት ይህንን ህንጻ 100 ጊዜ የሚገዝፍ ሊያሠራ የሚያስችል መሆኑ ነበር። የአፍሪካ መሪዎች ግን ልመናንና እርዳታን መጀመሪያ ለፍላጎት ማሟያ ቀጥሎ ለቅንጦትም አደረጉት። ልመና ሲበዛ ሱስ ይሆናልና!

ወደፊት የዛሬ 100 ዓመት ይህን ጽ/ቤት ብታየው ለማኝ እንደነበርክ እንጅ እስኪ ሌላ ምንን ያመለክታል? ለቻይናውያን በራስ መተማመንና ብርታትን ሲያጉናፅፍ ለእኛ ግን ውርደትን ብቻ ያከናንበናል። የሚገርመው ቻይና በብልጠት ከአፍሪካ ከምታግበሰብሰው ሀብት ቆንጥራ ይህን

የምፅዋት ሓውልት ስታቆምልን እኛ ለመጭው ትውልድ ሞራልና ክብር አለማሰባችን ነው።

ለመጪው ትውልድ በእርዳታ በዱባይ መስታወትና በቻይና ሴራሚክ የሚያብለጨልጭ ቢሮ ሠርተን ከምናልፍ በአፍሪካ ጥቁር ዲንጋይ መሠረቱን ብቻ እንኳን ሠርተን ብናልፍ ትልቅ ታሪክ ለልጆቻችን ይሆን ነበር። ያም ሆነ ይህ ግን ልመና ባለወርቅ ካባ ሆኖ ድርጅት ሲቋቋምለት፣ መ/ቤት ሲገነባለት፣ የልመና ሥራም ሞያ ሆኖ ሲቪ ሲጻፍበት ማየት ምን ያክል ልመና የባለሙያ፣ የመንግሥታትና የሀገራት ካንሠር መሆኑን ያሳያል።

የአፍሪካ መሪዎችና ሚኒስትሮች የርዳታና ብድር ውል ሲፈራረሙ ከአበዳሪዎቹና ከመጽዋቾቹ የበለጠ ፈገግታና ኩራት ሲያሳዩ ስታይ እነዚህ ሰዎች በማን ሕሊና በምን አእምሮ ነው የሚያስቡት ያስብላል።

ምፅዋት ተቀብለህ ችግርን ለማለፍ ከመሞከር ይልቅ ጥምህን ለመቁረጥ የራስህን የውኃ ጉድጓድ ቆፍር። ምናልባት ውኃ ሊወጣ ሲል አቅቶህ ትሞት ይሆናል። የድካምህን ውጤት ውኃውን ግን ከአብራክህ የወጣው ልጅህ ለመጠጣት ይችላል። ያንጊዜ ችጋርን ወደ ብልጽግና የቀየረ የማዕዘን ድንጋይ የሚል ታሪክና ክብር ይኖርሃል!..." ብለህ ንገርልኝ አለኝ!





# ከታሪክ መማር

በቅርብ ዓመታት የተጀመረውና ‹ጣና ፎረም› የሚባለው በባሕር ዳር ከተማ በየዓመቱ በሚካሄደው የመሪዎች ስብሰባ ወቅት ተጓዳኝ ውይይቶችና ዲስኩሮች ይደረጋሉ። በአንድ ወቅት ይኸው ተጓዳኝ ወይይት በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ በምሥራቅ አፍረካ የዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዚዳንቶችና ቻንስለሮች መካከል ተደርጎ ነበር። እንደማስታውሰው የውይይቱ ጭብጥ በዩኒቨርሲቲዎች ሀገራዊ ፋይዳ ላይ ነበር። በውይይቱ የተገኙት ፕሬዚዳንቶችና ቻንስለሮች የየሀገራቸውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከዳሰሱ በኋላ የዩኒቨርሲቲያቸውን ሚና አብራሩ።

ከደቡብ ሱዳን ጁባ ዩኒቨርሲቲ የመጡ ቻንስለር ተራቸው ሲደርስ አዲሲቷ ሀገራቸው የገጠማትን የፖለቲካና ሁለንተናዊ ቀውስ ካብራሩ በኋላ፡

"አሁን ግን ከስሕተታችን ተምረን ለማስተካከል እየሞከርን ነው" አሉ።

ከተሰብሳቢው መካከል ቁጭ ብለው ውይይቱን ሲከታተሉ የነበሩት የቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ኦሎሲጌኖ ኦባሳንጆ እጃቸውን አውጥተው እንዲናገሩ እንዲፈቀድላቸው ጠየቁና ሲፈቀድላቸው ቁመው በተለይ ለደቡቡ ሱዳን ቻንሰለር የሚከተለውን አሰተያየት አቀረቡ፡

"ወንድሜ እንደተናገሩት ከስሕተት መማር ትልቅ ነገር ነው። ሌሎች የሠሩትን ስሕተት እየደገሙ ግን ከስሕተት እየተማርኩ ነው ማለት ግን ሞኝነት ነው።

እናንት ደቡብ ሱዳናውያን ወንድሞቻችን ያለፋችሁበትን ፈተና በርካታ ሀገራት አልፈውት ነበር። ከእነርሱ አልተማራችሁም። በዚህ በጣም አዝናለሁ።

ከስሕተታችን ለመማር ከሆነ ስሕተቱ አዲስ መሆን አለበት። አዲስ ሥራ አምጥቶ አዲስ ስሕተት ሠርቶ ከዚያ መማር ትልቅ ነገር ነው። እንዴት አንድን ስሕተት እየደጋገምን፣





ሌሎች የሠሩትን ሰሕተትም እየደገምን ከስሕተት እየተማርን ነው እንላለን? ይህ የአብዛኛው አፍሪካውያን ችግር በመሆኑ በጣም ያሳዝነኛል!" ብለው ሐዘናቸውን ለሁላችን አጋርተው ቁጭ አሉ።

የፕሬዚዳንት ኦባሳንጆ ቁጭት አጥንቴ ውስጥ ዘልቆ እንደተሰማኝ አስታውሳለሁ። ግለሰብ፣ ሕዝብ፣ ሀገር፣ ዓለም ከታሪክ ይማራሉ። ኢትዮጵያውያንም ከታሪክ ተምረዋል፣ ይማራሉም። ይሄ ጠቅላላ ሐሳብ ነው። በእኔ ግንዛቤ ግን አንድ አዋቂ ሰው እንዳለው እኛ ኢትዮጵያውያን ከታሪክ የተማርነው ነገር ቢኖር ከታሪክ አለመማራችንን ነው።

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ፖለቲካ ውስጥ በጠፋው ጥፋት አለመፀፀት እና ከጥፋቱ አለመማር ዋነኛ መለያ ናቸው።

የፖለቲካ አዛውንቶቻችን በሴራ በተተበተበው ፖለቲካቸው፣ ያለ አቻና አምሳያ ከውጭ እንደወረደ አምጥተው ባዳቀሉት ርዕዮተ-ዓለም ለተመዘዘው መዘዝ፣ አገር ላይ ላወረዱት ፍጅትና መከራ ቅንጣት ታክል ሲፀፀቱ አይታዩም። እንዲያውም ኑሮ የገፉቸውን ስሜታውያን እያነሳሱ፣ ለጥይት እያጋፈጡ፣ ነገሩ ሲከፋም ወደ አውሮፓና አሜሪካ ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እያሸሹ፣ ነገሩ ሲበርድ ተመልሰው ከች ይሉና እንደገና ዘመኑ ያስከፋውን ወጣት ሆድ እያስባሱ የተለመደ ያረጀ ያፈጀ የኀፈነነ የ40 ዓመት ፖለቲካቸውን ይግቱናል።

ዕድሜያቸው ቢያረጅም፣ ከኩተት እስከ ሽበት ቢገረጅፉም ያንኑ የቀረና ሴራ እንደገና ይዘው ብቅ ይላሉ። እድሜ አያስተምራቸውም። ያንኑ የሞተ ፈረሳቸውን እየጋለቡ ወደ ሥልጣን ተራራ ይቋምጣሉ። አንድም ቀን ፀፀት የተሰማቸው መሆኑን አይገልፁም! በእነርሱ ምክንያት ለጠፋው የወጣት ሕይወት፣ ለወደመው ንብረት እነርሱ ድርሻ የላቸውም፡፡ ሁልጊዜ ለበደላቸው ሥርዬት በእጃቸው ነው። አዛውንቶቹ እስከበደላቸው ወደ መቃብር ሲወርዱ ‹ኑ ወደ ገሃነም አብረን እንውረድ› ይሉናል። ዕድሜያቸውን ጨርሰው ጅምር ዕድሜ ያለውን ወጣት ይዘውት መቀመቅ ሊወርዱ ይመኛሉ!

በሌላ በኩል ወጣት ፖለቲከኞቻችን ከአዛውንቶቹ ስህተት ሳይማሩ ያንኑ ይደግማሉ። አሮጌውን ወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ለመክተት ይጣደፋሉ። ተስፋ የጨለመበትን ወጣት እያበሳጩ ወደ እቶን ይማግዳሉ። ታዋቂነትንና ዝናን ማግኘትን እንጂ የወገናቸው መከራ አያሳስባቸውም፤ የሥልጣን ናፍቆት እንጂ የሞራል ዕዳ የለባቸውም። መብት እንጂ ግዴታና ሓላፊነት ያለባቸው አይመስሉም። በዚህም ‹‹ያልተማሩ›› የሚባሉት የሠሯትን ትልቅ አገር አፈራርሰው ትንንሽ ካላደረግን ብለው ተማርን ያሉት ይራኮታሉ!

እኛም ኅብረተሰብ የምንባለውም ቢሆን ከታሪክ የምንማር አልሆንም። ለምን፣ እንዴት፣ መቼ፣ የት የሚል ጥያቄ አንጠይቅም። በስሜት እንቃወማለን በጭፍን እንደግፋለን! ተሰለፍ ሲባል መሰለፍ መንጋጋት ነው። ለተቃውሚችን





ምክንያት የለን፤ ለድጋፋችን ለከት የለን! ያገኘ የሚጋልበን ሌጣ ፈረስ፣ ሁሉ የሚጭነን የህዳር አህያ ሆነናል።

ሲፈልጉ እናት ክልል ሌላ ጊዜ እናት ሀገር፣ አንድ ጊዜ በቋንቋችን ሌላ ጊዜ በሃይማኖታችን፣ ሲፈልጉ በርስትና ጉልት በፈቀዱት አነሳስተው ያሰልፉናል። አንድ ጊዜ ጸረ-ኢምፔሪያሊስት ሌላ ጊዜ ጸረ-ኮሚኒስት ሆነን ባልገባን ርዕዮት ተሰልፈን በሠንሠለት ታስረን እንገረፋለን። ይህ ሁሉ ሲሆን መከራው እነርሱን የማይነካ መሆኑን እስካሁን ድረስ አልተገለጠልንም። ‹የራስን ዕድል በራስ መወሰን› የሚል መፈክር አሲዘው አቁመውን ሲያበቁ እነርሱ የእኛን ዕድል ሲወስኑ እንደተደገመበት ጋኔን ቁመን እናያቸዋለን። ‹ሳያሽ የበላ ዝንጀሮ ሲስል ይውላል› እንደተባለው ትናንት ብልጣብልጦች ያደረጉብንን ረስተን ዘመነኞችን ያለጥያቄ እየተቀበልን አበሳችንን እናያለን። ‹ትናንት ማን ነበርክ? ነገስ ምን ልትሆንብኝ አስበሃል?› ብለን አንጠይቅም። ምንም ማንም ብትሆን ድምጼን እንጂ ሕይወቴን አልሰጥህም አንልም!

እንደ ኅብረተሰብ ታሪክ የመውደዳችንን ያክል ከራሳችንም ከሌሎችም፣ ከቅርብም ከሩቅም ታሪክ መማር አለመቻላችን ይደንቃል!

እንዴት ከታሪክ መማርን መማር ያቅተናል?!

# ‹ነገኘ መፍራት›

በሥራዬ አጋጣሚ የገጠር ልማት ፕሮጀክቶችን ውጤት ለማየት ከተባባሪዎች ጋር ወደ መስክ እወጣለሁ። ሰሜን ወሎ ዋድላ ወረዳ ውስጥ የምሠራበት ድርጅት (አመልድ) ከሚያካሂዳቸው የገጠር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ተግባራት መካከል አንዱን ለማዬት ወደ አንድ ታታሪ አርሶ አደር ቤት ጎራ አልን። ይህ ድሀ አርሶ አደር በፕሮጀክቱ ድጋፍ ሥልጠናና ብድር ወስዶ ዶሮ በማርባትና በግ በማድለብ በአንድ ዓመት ውስጥ ወደ 87 ሺ. ብር ገቢ እንዳገኘ በደስታ ገለጸልን።

እኛም ለጥረቱ አመስግነነው ስናበቃ

“ባገኘሽው ገንዘብ ምን አደረክ?” አልነው

ከሚኖርበት መንድር ወደ ሃያ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ አስፓልት ዳር ከምትገኘው ‹ጋሸና› ከምትባል ከተማ ውስጥ ትንሽ መሬት ገዝቶ የቆርቆሮ ቤት እንደሠራ አጫወተን።

“ለምን እዛ ሠራህ?” ስንለው፡

“ለልጆቼ ለወደፊት ሕይወታቸው ቅርስ እንዲሆናቸው ነው” አለን።

የራሱና የባለቤቱ ገጽታ፣ የልጆቹ ቁመና በአጠቃላይ የቤቱና አካባቢው ሁናቴ ካገኘው ገቢ የተነሣ ትንሽ እንኳ መሻሻል እንዳልተደረገበት ያሳብቃል።

በገጠመው መልካም እድልና በጥረቱ ባገኘው ገንዘብ የልጆቹን ጥብቆ ሳይቀይር፣ ሳሙና ገዝቶ የራሱንና የሚስቱን ልብስ ሳያጥብ፣ የልጆቹን አመጋገብ በትንሹ ሳይቀይር ከተማ ውስጥ ትንሽ መሬት ገዝቶ የቆርቆሮ ቤት መሥራቱ ነገን እንጂ ዛሬን የማይፈልግ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ ተሰማኝ።

በድህነት የሚማቅቁት እርሱና ባለቤቱ፣ በርሀብ የሚንገላቱት ልጆቹ በዚህ የመከራ ድርብርብ ጤናቸው ሊዛባ፣ ዕድሜያቸው ሊያጥር፣ የሕይወት ጸጋ ልታልፋቸው እንደምትችል አልተረዳውም። ዛሬን አጥቶ ነገንም ሊያጣ እንደሚችል አልተረዳም። ባገኘው መጠነኛ ገቢ ኑሮውን በመጠኑ





ሳያሻሽል፣ የመኖሪያ አካባቢውንም ሳይታደግ፣ እራሱንና አካባቢውን አጎሳቁሎ ከደረጃ በታች የሆነ ኑሮ እንደገና ከተማ ሀ-ብሎ ሊጀምር ይታትራል።

ይህ ዛሬን ገድሎ ነገን በተስፋ የሚያልም አስተሳሰብ ገጠሩን ከጉስቁልና አያወጣውም። እንዲያውም ይህ በጉስቁልና የተሞላ ከገጠር ወደ ከተማ ጉዞ ውጤቱ የተራቆተ ገጠር እና የተበላሸ ከተማ መፍጠር ሆኗል። የግብርና ዕድገታችን ገጠርን ገድሎ ከተማንም ማሳመም ሆኗል። የወደፊት ዕጣ ፈንታችን ከሁለት ያጣ ጎመን ይመስላል። ተፈጥሮ ሀብቱ የተሟጠጠ ገጠር፤ ዕቅድና ስልት፣ ውበትና ብልፅግና የሌለው ቅጥየለሽ ከተማ መፍጠር ሆኗል!

ለዘመናት በድህነትና በመከራ በመኖራችን፣ መጭው ዘመን እየከፋ እንጅ እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ባለማየታችን ነገን እንፈራለን። ነገ የባሰ እንጅ የተሻለ ይሆናል ብለን አናስብም። ክፉ ነገር ሲገጥመን እንኳ ለምን ሆነ ከማለት ይልቅ ‹የባሰ አታምጣ› እንላለን። መጽሐፍ ‹ስለነገ አትጨነቁ ነገ ለራሱ ክፋቱ ይበቃዋል› የሚል ቢሆንም ነገን ተስፋ ለማድረግ ዕምነት ይከዳናል።

ስለሆነም ዝግጅታችን ሁሉ ዛሬን ተጎሳቁለን የባሰውን ነገን መቀበል ላይ ያተኩራል። መቆጠብ፣ አባካኝ አለመሆን፣ ነገን ማሰብ ተገቢ ቢሆንም፣ በዛሬ ጥረት ነገን የተሻለ ማድረግ አርቆ

አሳቢነት ቢሆንም ዛሬን ገድሎ ነገን ለመውለድ ማሰብ፣ ዛሬን አበላሽቶ ነገን ማሳመር፣ ዛሬን አጨልሞ ነገን ማብራት ግን ሞኝነት ነው። ዛሬን አቆሽሸን ነገን ማፅዳት አይቻልም። ዛሬ ልጆቻችንን አጎሳቁለን ለነገ ኑሯቸው ልናመቻች አንችልም። ሁሉም በመጠኑና በሚዛኑ መሆን ይኖርበታል።

ዛሬ ራሳችንንና ልጆቻችንን በጉስቁልና በቆሻሻ እያኖርን ነገን ብናልም ነገ የእኛ ስለመሆኑ እርግጠኞች አይደለንም። በርሃብ የቀጨጨ ልጅ፣ የቆሸሸና የተጎሳቆለ ህፃን ለነገ ወርቅ ብናከማችለት ጤናው ላይ ያሳደርነው ጠባሳ ጊዜውን ቆጥሮ ዕድሜውን ያሳጥረዋል። ድሃ ሆኖ በመናጢ ድህነት ውስጥ እየኖሩ ገንዘብ እያጠራቀሙ ሀብታም ለመሆን ማለም ስቃይ ነው!

ማንኛውም የብልፅግናና የዕድገት ጉዞ የሚጀመረው ደግሞ ዛሬ ነው። ዛሬ ጠንክረን የምንሠራበትና በጥልቅ የምናስብበት ብቻ ሳይሆን የብልፅግና ኑሮን የምንጀምርበት፣ ንፅህናን የምንለማመድበት ነው! የሀብትን ጣዕም ቤተሰቡ እየቀመሰ ከፍ ላለ ብልፅግና መትጋት ይኖርበታል ። ከገጠርም ይሁን ከየትኛውም የሀገር ጫፍ የሚገኝ ሀብት ረድኤቱና ቱሩፋቱ መጀመሪያ መድረስ ያለበት ሀብቱን ላመነጨው ሰው፣ ቤተሰብና አከባቢ መሆን ይኖርበታል። መቼ የሚለው ደግሞ ከዛሬ ጀምሮ መሆን ይገበዋል ብዬ አስባለሁ።





# ገራገር እናት በአሜሪካ

ካሊፎርኒያ ሳንፍራንሲስኮ ከተማ በሥራ አጋጣሚ ሰነባብቼ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ከሳንፍራንሲስኮ በመነሣት ወደ ዋሽንግተን ዳላስ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ መጥቼ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ተሳፍሬ መምጣት ስለነበረብኝ መሽትሽት ሲል ወደ ሳንፍራንሲስኮ አውሮፕላን ማረፊያ ተጓዝኩ።

እንደተለመደው የአውሮፕላን ማረፊያ ጣጣዎቼን ጨርሼ በተባለው ሰዓት ወደ አውሮፕላኑ ተሳፈርኩ። በአውሮፕላኑ የመጨረሻ የኋላ ክፍል ከሁለት ሴት ፈረንጆች ጋር ተቀመጥኩ። እንደተለመደው የአውሮፕላኑ አስተናጋጆች አለቃ "ሁሉም መንገደኞች ስለተሳፈሩ ከ5 ደቂቃ በኋላ

መንቀሳቀስ እንጀምራለን" ብላ አስታወቀች። የተባለው 5 ደቂቃ ከሞላ በኋላ እንደገና ካፒቴኑ "አንድ መንገደኛ ስለቀረብን ትንሽ ታግሰን በ10 ደቂቃ ውስጥ ወደ ማኮብኮቢያው እናመራለን" አለ። ደቂቃዎች አለፉ። ጊዜ ጊዜን እየወለደ ምንም እንቅስቃሴ ስለማይታይ የአውሮፕላኑ ተሳፋሪዎች በሙሉ ግራ ተጋባን።

አብዛኛው ተሳፋሪ ወደ አውሮፓ እና ወደ ሌሎች ሀገሮች ከምሥራቁ የአሜሪካ ክፍል ከዋሽንግተን ተነሥቶ ሌላ ዓለም አቀፍ በረራ ይዞ የሚቀጥል ስለሆነ አውሮፕላን ያመልጠኛል በሚል የመጨነቅ ስሜት ይቁነጠነጥ ጀመር። ይሁንና በ10 ደቂቃ እንነሣለን የተባለው ቀርቶ ከ20 ደቂቃ በላይ እየረዘመ ሲሄድ መረበሽና በሁሉም ዘንድ መተያየትና ማጉረምረም ተጀመረ። አስተናጋጆች ከኋላ ከፊት ውርውር ይላሉ። በዚህ መካከል አውሮፕላኑ ውስጥ የመነጋገሪያው ማይክራፎን ተከፈተና የሆነ ጭቅጭቅ የሚመስል ነገር ይደመጥ ጀመር። እስከዚህ ሰዓት ምንም ትኩረት አልሰጠሁትም ነበር። ምክንያቱም የኢትዮጵያ አየር መንገድን ለመያዝ የ4 ሰዓት ጊዜ ልዩነት ስለነበረኝ ለእኔ ያን ያክል የሚያሳስብ አልነበረም። እንደሌሎቹ ተሳፋሪዎች ብዙም ችግር ሳይታይብኝ ዘና ብዬ ተቀምጬ ነበር። ይሁንና አሁን ግን ስጋቱ ወደእኔም መጋባት ጀመረና ጆሮዬን አቅንቼ ሳዳምጥ በአውሮፕላኑ ማይክራፎን ውስጥ ድንገት አማርኛ የሰማሁ መሰለኝ። ይህም አማርኛ የሴት ድምፅ የሚመስል ሆኖ ልክ እሰጥ አገባና ውዝግብ ውስጥ ያለ ይመስላል። በዚህን ጊዜ ‹ምናልባት ያለመግባባት





ችግር ተፈጥሮ ይሆን? ለምን ሴትዮዋ አማርኛ ይናገራሉ?› አልኩኝና የቋንቋ አለመግባባት ችግር ከተፈጠረ ላግዝ እችል ይሆናል ብዬ እንደተቀመጥኩ ወደ ላይ እጄን አወጣሁኝ።

በዚህን ጊዜ ከኋላ የነበረችው አስተናጋጅ እየሮጠች መጣችና "እባክህ ትንሽ ታገሰን፣ ችግር ስለገጠመን ነው" አለችኝ በእንግሊዝኛ።

"አይ ችግር ለማቅረብ አደለም። አሁን በማይክራፎኑ ውስጥ የምንሰማውን ቋንቋ መናገር እችላለሁ፤ ምን አልባት የማግዝ ከሆነ ብዬ ነው" አልኳት።

እንዴት እንደተደነቀችና እንደተደሰተች ልነግራችሁ አልችልም። በቃ ልክ እንደ ስፓይደር ማን (Spider Man) ከብዙ ችግር የሚያድን ዓይነት ሰው አድርጋ እየቸኘች "እባክህ ተከተለኝ!" አለችኝ።

ከኋላው የአውሮፕላን ክፍል ወደ ፊት ስጓዝ ብዙ ተሳፋሪ ችግሩን የሚፈታ ሰው ተገኘ በሚል ስሜት በአድናቆትና በክብር በዓይኑ ሸኘኝ ።

የቢዝነስ ክላሱን አቋርጬ ፊት ለፊት ስደርስ የበረራ ክፍል በር ላይ ካፒቴኑ ቆሞ ወደ ጐን ደግሞ የአውሮፕላኑ ሓላፊ ከአንዲት ኢትዮጵያዊት እናት ጋራ ሲወዛገቡ ደረስኩ። ኢትዮጵያዊቷ እናት የአውሮፕላኑ በር እንዳይዘጋ በሩ ላይ ቆመው ይማፀናሉ። በቀጥታ ሄድኩና፤

"ይህን ቋንቋ መናገር እችላለሁ፤ ምን ችግር ተፈጠረ?" ስለው

ካፒቴኑ እጆቹን ዘርግቶ እቅፍ አደረገኝና፡

“እባክህ በጣም ችግር ውስጥ ገብቻለሁ። እኚህ ሴትዮ ምን እንደሚሉና እንደፈለጉ አልገባኝም። ብቻ በሩን አላዘጋም ብለው ይኸው ከመጡ ጀምሮ ቆመዋል” አለኝ በጭንቀት። ቀጠለና፡

“በእርግጥ ሴኪዩሪቲ ጠርቼ ላስወርዳቸው እችላለሁ። ግን የሆነ ያስጨነቃቸው ነገር እንዳለ ስለተረዳሁ ዝምብዬ ጥያቸው መሄድ አልፈለኩም። እባክህ እርዳኝ?” አለኝ።

በዚህን ጊዜ ወደ ሴትዮዋ ዘወር አልኩና፡

“እማማ እንደምን አደሩ? ምን ችግር ገጠመዎት?” ስላቸው

“መድኃኔዓለም ደረሰልኝ ማለት ነው!” አሉና እርሳቸውም መጥተው እቅፍ አድርገው ሳሙኝና፡

“ልጄ.. ልጄ! እንደወጣሁ ብቀር ይሻለኛል! ልጆቼ ለመጦሪያ ብለው የሰጡኝን እንዲሁም ደግሞ አገር ቤት ላሉ ሌሎች ሰዎች ለእናቶቻቸው የላኩትን ብዙ ብር የያዘ ቦርሳ እዚህ መንገድ ላይ ጠፋብኝ ፍተሻው ላይ። እንዴት ብዬ አገሬ እገባለሁ? የእኔስ ይሁን ልጄ፡ የሰው አደራ በላሁ” አሉና እንባቸውን ዘረገፉት።

እኔም ለካፒቴኑ አስተረጎምኩ።

“ከ10 ሺ.ህ ዶላር በላይ የያዘ ቦርሳ መፈተሻው ላይ ጥለው ስለመጡ ነው የቸገራቸው አልኩት።”

እርሱም መልሶ “እዚህ ቅርብ ቦታ የመጨረሻው መግቢያ ላይ ከሆነ ችግር የለውም። ግን ምናልባት መጀመሪያው ፍተሻ ቦታ ከሆነ ግን ቢሄዱም አያገኙትም፡ ያን ያክል ጊዜም የለኝም። እባክህ የት እንደጣሉት በድጋሚ ጠይቃቸው?” አለኝ።

ሴትዮዋን ዘወር አልኩና “በትክክል የት ነው የጣሉት፡ ከወዲያ ከፍተሻው ከሆነ አይገኝም” ስላቸው፡

“አይደለም አይደልም፡ እዚህች እመጨረሻዋ ላይ ልገባ ስል ወረቀቴን ለማሳየት ስል ቁጭ እንዳደረኩት ነው” አሉኝ።

ይህንኑ አስተረጎምኩና የቦርሳውን ቀለም እንድጠይቃቸው ጠየቀኝ። እርሳቸውም ቤዥ ቀለም ያለው ከእጅ ቦርሳ ከፍ ያለ እንደሆነ ነገሩኝ። ይህንኑ ስናገር የአስተናጋጆቹ ሓላፊ እየሮጠች ሄደች።

በደቂቃዎች ውስጥ የተባለውን ቦርሳ አንጠልጥላ መጣች። አውሮፕላኑ ውስጥ የነበሩት በተለይ ቢዝነስ ክላስ አካባቢ የነበሩ ሰዎች በአድናቆት ቆመው አጨበጨቡ። በዚህን ጊዜ የአውሮፕላኑ በር በፍጥነት ተዘጋና ካፒቴኑ ዘሎ ወደ ማብረሪያ ክፍሉ ሲገባ ሴትዮዋ የሚያደርጉት ጠፍቷቸው መሬት ከሳሙ በኋላ፡

"በሉ እማማ! አሁን እንግዲህ ቶሎ በሉና ወደ መቀመጫዎ እንሂድ፡ ጊዜ ስለፈጀን ይሂዱና ይቀመጡ? አልኳቸው።

"እንዴ ምን ሆነሃል? እዚህ ውስጥ ገብቼማ ሳላመሰግነው አልሄድም" አሉ ወደ በረራ ክፍል እያመለከቱ።

"እንዴ! የበረራ ክፍሉ ውስጥ እኮ አይገባም!" አልኩኝ በድንጋጤ

" በፍፁም! ይህንን የተቀደሰ ሰውማ ሳላመሰግነው እንዴት ብዬ?!"

"ኧረ እባክዎት እማማ!"

በዚህ መካከል ስንጨቃጨቅ ትዕግስቷ ያለቀባት የአስተናጋጆች ሓላፊ

"Now What!?" አለች።

"አይ ካፒቴኑን ገብቼ ካላመሰገንኩት አልሄድም ነው የሚሉት" ስላት።

"Ofcourse he deserves/ ሊታመሰግነውማ ይገባል ችግር የለውም" ብላ ለካፒቴኑ በውስጥ መገናኛ ስትነግረው የበረራ ክፍሉ በር ተከፈተ። በጣም የሚደንቀው ድራማዊ በሆነ መንገድ ሴትዮዋ ዘለው ከበረራው ክፍል ገቡና ለመነሳት እድል ሳይሰጡት ተጎንብሰው ሁለት ጉንጮቹን ይዘው አገላብጠው ሳሙት። ይኼ ሰውዬ በሕይዎት ዘመኑ ጉንጨን ተስሞ ስለማወቁ እርግጠኛ አይደለሁም። ልክ በኢትዮጵያዊ





አሳሳም አይነት አገላብጠው ከሳሙት በኋላ መርቀውት ወደ መቀመጫችን አመራን።

ተሳፋሪው ሁሉ ከሰዓቱ መግፋት የተነሣ ጭንቀት ላይ ስለነበረ

"በሉ እማማ ፈጠን ብለው ራመድ ይበሉና ቁጭ ይበሉ" እያልኩኝ ከኋላ ከኋላ ለመግፋት ስሞክር እርሳቸው ጭራሽ በየክፍሉ ሲደርሱ እንደ መቆም እያሉ እጃቸውን ወደ ላይ ዘርግተው በአማርኛ ቃና ዘና ብለው ፡

"ጉድ ሞርኒግ! ሁላችሁም ታንኪው!" እያሉ ሰላምታቸውን ቀጠሉ። ከፍተኛ ደስታ ላይ ናቸው። የሰው የጊዜ ጭንቀት ምናቸውም አልነበረም። ብቻ እንደምንም እየገፋሁ ወንበራቸው ላይ አስቀመጥኳቸው።

ልክ አስቀምጨ ስጨርስ ተሳፋሪው በሙሉ እንደተማከረ ሁሉ ቆሞ አጨበጨበልኝ። በአስደናቂ ተአምር ከብዙ ፈተና የታደኩ ያክል ወደ አውሮፕላኑ የኋላ ክፍል ወደሚገኘው መቀመጫዬ ስሄድ "ታንኪው ሰር" እየተባልኩ ከምስጋና ጋር የጀግና አቀባበል ተደረገልኝ።

ከረጅም መዘግየት በኋላ አውሮፕላኑ ወደ ማኮብኮቢያው ሜዳ ሲያመራ ካፒቴኑ የእኔን ስም ጠርቶ የገጠመውን ችግር ለመፍታት ላደረኩት ትብብር በበረራ ቡድኑና በራሱ ስም ከፍተኛ ምስጋና ማቅረብ እንደሚፈልግ ገለጸ። በበረራው ወቅት የካፒቴኑ ልዩ መልዕክተኛ ሆና የአስተናጋጆች ሓላፊ በተደጋጋሚ እየመጣች የፈለኩትን ምግብና መጠጥ

እንድስተናገድ ትእዛዝ የተሰጣት መሆኑን ገልጻ በተደጋጋሚ ትጠይቀኝ ጀመር። አጋጣሚ ሆኖ እለቱ ሐሙስ ለዓርብ ሌሊት ስለነበር የፆም ሰዓት ስለደረሰ ምንም መስተናገድ እንደማልፈልግ ከምስጋና ጋር ስነግራት በጣም ቅሬታ ተሰማት።

ለማንኛውም በዚህ ሁኔታ ወደ ዋሽንግተን ጉዟችንን ቀጠልን። ነገር ግን ከ40 ደቂቃ በላይ ዘግይተን ስለተነሣን የአብዛኛው ተሳፋሪ ወደ ሌላ አውሮፕላን የመሳፈሪያ ጊዜ ተጣቦ ነበር። ስለዚህ ገና አየር ላይ እንዳለን ፓይለቱ እንዲህ ሲል ቃል ገባ፡

“በተቻለኝ መጠን ፍጥነት ጨምሬ ጊዜውን ለማካካስ እሞክራለሁ። ከዚህ ውጭ ደግሞ እንዳረፍን በተለዩ ኮሪደር እንድትስተናገዱ ጥረት ይደረጋል” አለ።

በዚህ መሠረት ልክ ዳላስ ኢንተርናሽናል ኤርፖርት እንዳረፍን ‹ረጅም ጊዜ ያላችሁ ተሳፋሪዎች እዛው እንደተቀመጣችሁ ቆዩ› ተባልንና አጭር ጊዜ ያላቸው ስማቸው እየተጠራ ቀደም ብሎ በተነገረው መሠረት በተለዩ ኮሪደር በፍጥነት እንዲያልፉ ወደ አውሮፕላኑ በር አመሩ።

እኔም በቂ ጊዜ ስለነበረኝ ዘግይቼ ስወርድ ካፒቴኑ ከአውሮፕላኑ በር ላይ ጠብቆ እጄን ጨብጦ በድጋሚ አመስግኖኝ ወረድኩኝ። በእውነቱ በዛ ደረጃ ሊያስመሰግነኝ የሚችል እርዳታ ያደረኩ አልመሰለኝም ነበር። የሚደንቀው ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩ በኋላ ስሜንና አድራሻዬን





ከትኬቱ ላይ ወስደው ይመስለኛል የአየር መንገዱ ባለቤት የሆነው ዩናይትድ ኤርላይንስ ቢሮ የምስጋና ደብዳቤ በኢ-ሜል ልኮልኛል። እና አማርኛ ቋንቋ እንደዚህ አድርጎ በልዩ ክብር እንዳመጣኝ አስታውሳለሁ።

ይህች እናት ከአውሮፕላኑ ወርደን ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ለመሳፈር ስንመጣ እንዳወጉኝ ረጅም ዘመን መንግሥትን ያገለገሉና በጡረታ ላይ ያሉ ሃይማኖተኛ ሴት መሆናቸውን ተረድቻለሁ። ከሁሉ ያሳሰባቸው ነገር በአደራ ይዘውት የነበረው አራት ሺህ ዶላር መጥፋቱ እንደነበር አጫወቱኝ። ደብረ ብርሃን አካባቢ እንደሚኖሩ ነግረውኝ እንድጠይቃቸው ሁሉ አሳስበውኝ ነበር። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ግን ስልክ ሳልይዝ ስለተለያዩን ልጠይቃቸው አልቻልኩም።

# <የሥልጠናው አካል ነው>

**ባሕር ዳር ለክልሉ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች ከፌደራል መንግሥት በሚላኩ ባለሥልጣናት ለአራት ቀናት የሚቆይ ሥልጠና እንዳለና የመጀመሪያው ቀን ከጠዋቱ 2፡30 እንሚጀመር ተነገረ። በዚህ መሠረት ሠልጣኙ ከየዞኑ፣ ከክልል ቢሮዎችና ተቋማት ቢሮ እየተዘጋ ወደ ጉባዔ አዳራሽ ተመመ። በዐባይ ወንዝ ዳርቻ የተገነባውና የተንጣለለው የጉባዔ አዳራሽ ከ2፡30 ጀምሮ ጢም ብሎ ሞልቷል። ሠልጣኙ ቢገኝም አሠልጣኞቹ ግን አንዱም ብቅ ያለ የለም። ሦስት ሰዓት ተኩል ሆነ አሁንም የውኃ ሽታ ሆኑ።**

ኋላ ላይ ከአስተናባሪዎቹ አንዱ ወደ መድረክ ወጣና፡

"አሠልጣኞቹ ዛሬ ጠዋት ነው ከአዲስ አበባ በአውሮፕላን የገቡት እና ቁርስ ይቅመሱ ብለን ነው" አለ።

ከአዲስ አበባ በጠዋት ወደ ባሕር ዳር የሚመጣው የመጀመሪያው አውሮፕላን የሚደርሰው ጠዋት ሦስት ሰዓት ላይ ነው። ይታያችሁ ሠልጣኙ ግን አዳራሽ እንዲገኝ የተነገረው ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ነው። በምትቀጥረው ሰዓት እንደማትገኝ እያወክ ቀድመህ መቅጠር ለሰዎች ያለህን ንቀት ከማሳዬቱም በላይ እምነት እንዳይጣልብህ የሚያደርግ ይመስለኛል።

አሠልጣኞቹ ባሕር ዳር ሲደርሱም ሠልጣኙ አደራሽ ገብቶ እየጠበቀ መሆኑ እየታወቀ ቁርስ ሊቀምሱ ወደ ሆቴል መሄዳቸው ደግሞ የበለጠ ይገርማል። እርግጥ ቁርስ ‹ሊበሉ› ሳይሆን ‹ሊቀምሱ› ነው የተባለው። ስለሥልጣናቸው ሲባል ለትህትና ነው እንጂ እንደነዚህ ያሉ ለሰው የማይጨነቁ ፍጡሮች አንኳን በመቅመስ በመብላትም የሚመለሱ አይደሉም።

በኋላ ሰው ማጉረምረም ጀመረ። "ለምን ሰዓት አይከበርም? ሥልጠና ተብሎ እንዴት በሰዓቱ አይጀመርም?" የሚል ጉምጉምታ ተሠማ።

በዚህ መኻል ከጎኔ ተቀምጦ የነበረ አንድ ተረበኛ ወዳጄ፡

"አያችሁ መዘግዬትና ማስጠበቅ ራሱ አንዱ የሥልጠናው





አካል ነው" አለን።

ልማት ልናፋጥን፣ ዲሞክራሲ ልናሰፋ፣ ፍትህ ልናሰፍን እንችል ዘንድ ዕውቀት ልንጨምር ልንሠለጥን ተጠርተን ‹ሰዓት አለማክበርን› ‹በወቅቱ አለመጀመርን› በተግባር ሠለጠን።

ፍጥነትን በመዘግዬት፣ መልስ መስጠትን በማጉላላት፣ ሥራ ለማቀላጠፍ ሥራን ዘግቶ በመጠበቅ ጀመርነው።

ወደ አራት ሰዓት ሲጠጋ አሠልጣኞቹ ወደ አዳራሹ ሲገቡ በክብር ለመቀበል ተነሣን። ወደ አዳራሹ ሲገቡ ሰዓት አርፍዶ እንደመጣ ሰው እየተሽቆጠቆጡ ሳይሆን እየተንጎማለሉ ከፊት ክፍት ሆኖ ወደሚጠብቃቸው ቀይ ወንበር አመሩ።

ድንቁርናችን ከመግዘፉ የተነሣ ነውራችን ክብራችን ሆነ። በመዘግዬታቸው የተሰማቸው የሕሊና ወቀሳ ስለመኖሩ እጠራጠራለሁ። እኛም ቢሆን የለመድነው ስለሆነ፡

‹ና ብትይኝ መጣሁ፡ ብመጣ አጣሁሽ

በድሌ አዘንኩ እንጂ፡ መች ተቆጣሁሽ›

እንዳለው የአገሬ አፍቃሪ በእድላችን አዝነን ቀጠልን። የዘገዬን ሰው አክብረን መቀበልን ስለለመድን የነውሩ ተካፋዮች ሆንን። ‹ግም ለግም ተያይዘህ አዝግም› መሆኑ ነው!

ጊዜና የጊዜ ግንዛቤ የሰው ልጆችን ከሌሎች እንስሳት የሚለዩት ጉዳዮች ናቸነው። አምና፣ ዘንድሮና ከርሞ፤ ትናንት፣ ዛሬና ነገ እንዲሁም ቅድም፣ አሁንና ኋላ በእንስሳት ዓለም ውስጥ የሉም። የሰው ልጅ ግን ቅድምንና አሁንን ለይቶ የማወቅ የሞራል ግዴታ አለበት።

እድሜ ጊዜ ነው። ሰው ሞተ የሚባለው እኮ ጊዜው ሲያልቅ ነው። ጊዜ ሲረዝም እድሜ ሲያልቅ ደግሞ ሞት ነው። ሞት መራራ ከሆነ ምነው የጊዜ መባከን ቢያንስ ህመም አይሆንብንም? ሰው ቀጥሮህ ሲቀር ከእድሜህ እየቀነሰብህ ነው። የሆነ ሰው ያለአግባብ የወሰደብህን ገንዘብ አንድ ቀን ሊመልስልህ ይችላል፤ የወሰደብህን ጊዜ ግን መቼም አይመልስልህም። አንድ ሊቅ እንዳለው ለሰው የምትሰጠው ትልቁ ስጦታህ ጊዜ ነው። እንዴት? የሠጠኸው ጊዜ ከእድሜህ ላይ የቀነስከው ነውና!

በመጽሐፍ ቅዱስ፡

‹እናንት የአባቴ ብሩካን… ብታመም ጠይቃችሁኛል፤ ብታሰር ጎብኝታችሁኛል…› ብሎ በመጨረሻው ዘመን አማኞችን የሚያመሰግነው ሰዎችን ለማበረታታትና ለማጽናናት ከእድሜያቸው ቀንሰው ስለሰጡ ነው።

እንደ ማኅበረሰብ ሰዓት ያለማክበራችን ችግር የበረታው ከሚጠበቀው ሰው ፍጥነትና ስጋት ይልቅ የጠባቂዎቹ ረብ





የለሽ ትዕግስት ከፍ ማለቱ ይመስለኛል። ዘግይቶ በመምጣቱ የሚያመልጠው ነገር የለምና! በሂደት ለእርሱ መዘግዬት መብት ለአንተ ደግሞ መጠበቅ ግዴታ ይሆናል። በመጨረሻም ጊዜህን በግዴለሽነት ሲገድልብህ ትዕግስት አልቆ ትተህ ብትሄድ እንኳ ትዕግስት የለሽ ተብልህ ልትፈረጅበት ትችላለህ!

ጆርጅ ዋሽንግተን የተባለው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባንድ ወቅት ጸሐፊው አምስት ደቂቃ ዘግይቶ መጣ። ጸሐፊው መዘግይቱን ሲረዳ ለፕሬዚዳንቱ እንዲህ አለ፡

“ይቅርታ የዘገየሁት ሰዓቴ ስለተበላሸ ነው” አለ

ዋሽንግተን መልሶ፡

“ለነገ ወይ አንተ ሰዓት ትገዛለህ

ወይ ደግሞ

እኔ ጸሐፊ እቀይራለሁ” አለው።

የጆርጅ ዋሽንግተን አስተያየት ድክመትን የሚያስታምም ሳይሆን አክሞ የሚያድን መድኃኒት ሥርነ ቀል መፍትሄ የሚያመጣ ማርከሻ ነበር።

እንደ ሀገርና ኅብረተሰብ በጊዜ ክቡርነትና ውድነት ላይ ያለንን ህመም መታከምና ማከም ይምንችለው እንደ ጆርጅ ዋሽንግተን አይነት የሞራል ልዕልና ስናመጣ ብቻ ነው!

# ፍሬ ከናፍር

**በ2011 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች የምረቃ በዓል ላይ እንግዳ ሁኜ እንድገኝ ቢጋበዘኝ መሠረት ለተመራቂዎች የሚከተለውን አልኩ፡**

**ወድ ተመራቂዎች!**

**ክቡራንና ክቡራት!**

**በዛሬው ዕለት በዚህ መርሐ-ግብር ላይ ተገኝቼ ንግግር እንዳደረግ ስለተጋበዝኩኝ የተሰማኘን ክብር እየገለጽኩ ምስጋና እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ! አመሰግናለሁ!**

ዕውቀት ረቂቅ ነገር ናት! ላልያዛት ምንም አትመስለውም፤ ለያዛትም ቢሆን ያንያክል አትደንቅም። ያላወቃት ስለማያውቃት አይናፍቃትም፣ ያወቃትም በእጁ ስለገባች ተራ ነገር ትመስለዋለች። ይህን አንድ ሊቅ የጠቀሰውን ምሳሌ ወስጄ ላስረዳ፡-

አንድ ሽማግሌ ዓሣ በጠዋት ከጕሬው ወጥቶ ህጻናት ዓሳዎች ዋና ሲለማመዱ ያገኛቸዋል። ‹ልጆች እንዴት ናችሁ? ዛሬ ውኃው ሙቅ ነው ወይስ ቀዝቃዛ?› አላቸው። ልጆቹም እርስ በርሳቸው በአግራሞት ተያይተው "ውኃ ምንድን ነው?" አሉት። ሽማግሌው የውኃ ምንነትን ማወቅ ይህንን ያህል ትልቅ ነገር ስላልመሰለው ነበር። ውኃን ላያውቁ ይችላሉ ብሎ ለአፍታ እንኳን አልተጠራጠረም።

እውነታው ግን ተራ የመሰለንን ነገር እንኳን የማያውቁ መኖራቸው ነው። በዚህ የተነሣ በዚህ ዓለም ዕውቀትን በመፈለግና ዕውቀትን በማክበር የሚተጋው ውስን በመሆኑ በተለይም በሀገራችን ከዕውቀት አልተጠቀምንም ወይም በማወቅ አላደግንም።

የዩኒቨርሲቲ ዋናው ዓላማ ዕውቀትን ሁሉ ለተማሪዎች ማስጨበጥ አይደለም፣ አይቻልምና!፤ የዕውቀትን ምንነትና ጥቅምን እንጅ። ስለሆነም እናንተ የዛሬ ተመራቂዎች ለማወቅ የተዘጋጃችሁ፣ የዕውቀትን ጥቅም የምታውቁ፣ የዕውቀትን ኃይል የምትረዱ ሆናችኋል። በኮምፒውተር ቋንቋ ፎርማትድ (Formatted)፣ በኪነጥበብ አነጋገር የተቃኘ





ክራር፤ በእናቶቻችን አነጋገር ደግሞ የተሟሸ ምጣድ እንጂ አዋቂዎች አይደላችሁም፤ ማሰብ እንድትጀምሩ እንጂ አስባችሁ ስለጨረሳችሁ ዛሬ አልተመረቃችሁም።

ውድ ተመራቂዎች!

በዛሬው ዕለት ተመራቂ ስትባሉ በአንድ የሙያ መስክ በዓለም ላይ ምን ያክል ዕውቀት እንዳለ፣ ያም ዕውቀት እንዴት ሀብትና ብልፅግና ፣ ደኅንነትና ሰላም፣ ፍትህና ዲሞክራሲ እንደሚሆን በጥቅሉ ድንጋይ እንዴት ዳቦ እንደሚሆን፣ ውኃ እንዴት መብራት እንደሚሆን፤ መርዝ እንዴት መድኃኒት እንደሚሆን፤ ጊዜ እንዴት ገንዘብ እንደሚሆን፤ ዕውቀት ካለ ውኃን ሽቅብ ማፈሰስ ጉምን መዝገን እንደሚቻል የዕውቀት ብልጭታ በአዕምሮአችሁ መፈጠሩን ለማመልከት ነው። ልክ ክብሪት እንደመጫር ነው። በርቶ ይጠፋም ይሆናል ወይም ያቀጣጥል ይሆናል። ብልጭታውን ወደሚቀጣጠል የዕውቀት እሳት መቀየር ከዚህ በኋላ ለእናንተ ዛሬ የተሰጣችሁ ሓላፊነት ነው።

ዛሬ ሰውሩ የዕውቀት ዓለም መጋረጃ ለእናንተ የተገለጠ ስለመሆኑ የምስክር ቀን ነው። ለዕውቀት መቅደስ ምሥጢር ተካፋይ ለመሆን ብቁ እጩ መሆናችሁ የተገለጠበት ዕለት ነው።

ስለሆነም ዋናው የዕውቀት ፍለጋ ዋናው ትምህርት ቤት ከፊት ለፊታችሁ ነው። እስከ ዛሬ መምህራን ያስተምሯችሁ ነበር፤ ከዚህ በኋላ ግን እራሳችሁን በራሳችሁ ታስተምራላችሁ።

እስከዛሬ በሳምንት ማብቂያ ወይም በሰሚስተር ማለቂያ ላይ መምህራኖቻችሁ ይፈትኗችሁ ነበር፤ ከአንግዲህ ወዲህ ደግሞ ኑሮ በየቀኑ ትፈትናችኋለች። እስከ ዛሬ የፈተና ውጤታችሁን መምህራኖቻችሁ ያርሙላችሁ ነበር፤ ከዚህ በኋላ ግን ሕይወት ታርምላችኋለች። የእስከ ዛሬው የትምህርት ውጤታችሁ A እና B ወይም ቁጥር ነበር፤ ከዚህ በኋላ ግን የፈተና ውጤታችሁ ብልጽግና ወይም ድህነት፣ ፍቅር ወይ ጥላቻ፣ ሹመት ወይ ሽረት፣ ክብር ወይ ውርደት፣ ሕይወት ወይም ሞት ሆኖ ይመጣል።

ግን ልብ በሉ!

በዩኒቨርሲቲ ቆይታችሁ በጥልቀት የማሰብን አቅም፣ የዕውቀትን ጉልበትና ኃይል ተረድታችኋል። ‹የዕውቀት ድሃ እንጂ የገንዘብ ድሃ› የሚባል ነገር እንደሌለ ከሳይንስ ተምራችኋል። ማንም ሰው ሲወለድ እርቃኑን ይሁን እንጂ ምጡቅ የብልጽግና ምንጭ የሆነ አእምሮ ከፈጣሪ ዘንድ ይዞ እንደሚመጣ ተረድታችኋል። የሰው ልጅ እጣ ፋንታ በሌሎች ሰዎች እጅ ሳይሆን በአእምሮው ወስጥ እንደተቀመጠለት አውቃችኋል።

በዩኒቨርሲቲ ቆይታችሁ በተደጋጋሚ ትፈተኑ ነበር። መፈተን ምን እንደሆነ፣ የፈተና ውጤት ምን ሊያስከትል እንደሚችል በአግባቡ ተለማምዳችኋል። አዕምሯችሁ የፕሮብሌምን ሶሉሽን በወረቀት ላይ ማምጣትን ተምሯል። እንድታብራሩ፣ ከብዙ ምርጫዎች ትክክለኛውን እንደትመርጡ፤ እውነትንና ውሸትን እንድትለዩ፣ በየወገኑ እንድታዛምዱ ተጠይቃችሁ አልፋችኋል። አሁን የልምምድ ጊዜ አብቅቶ እውነተኛው የፈተና ሕይወት ከዚህ በኋላ ይጀመራል። ሙሉ ትጥቅ ይዛችኋልና ይህንን ነባራዊ ዓለም ለመቀበል ልበሙሉ እንጂ የምትሸበሩ አይደላችሁም። የችግር ሁሉ መፍቻ እውቀት መሆኑን ተረድታችኋልና።

በተማራችሁበት የሙያ መስክ በመሰማራት እራሳችሁንና ወገናችሁን አገልግሉ በሚል ምክር ላስራችሁ አልፈልግም። ይልቁንም የልባችሁን ፍላጐትና መሻት ተከተሉ (follow your heart) እላችኋለሁ እንጂ። የሠለጠናችሁበት ሙያ መነሻችሁ እንጂ መድረሻችሁ ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አይቻልምና። ከዩኒቨርሲቲው ያገኛችሁት ሙያ መስፈንጠሪያ (springboard) እንጅ መታሰሪያ ገመድ አይሁንባችሁ። የምትወዱትን ሥሩ፣ የምትሠሩትን ውደዱ!

ውድ ተመራቂዎች!

አንድ ሊቅ እንዳለው መጥፎ ሰው ጥሩ ባለሙያ ሊሆን አይችልም፤ መጥፎ ባለሙያም መልካም ሰው ሊሆን አይችልም። የተዋጣላችሁ ለሀገር ለወገን መከታ የምትባሉ፣ ምሁር፣ ባለሙያ የምትሆኑት የተስተካከለ ስብዕና ሲኖራችሁ ነው። ቅንነትን፣ ደግነትን፣ አዛኝነትን፣ ታታሪነትን፣ ለመማር ዝግጁነትንና ፈጣሪን መፍራትን ገንዘብ አድርጉ። በጋራ መሥራት እንጅ በጋራ ማሰብ አይቻልም። ብቻችሁን ሁናችሁ አስቡ ሥራ ላይ ግን ተባበሩ!

ልብ በሉ! በሀገራችን ብዙ ባለዲግሪዎች አሉ ብዙ አዋቂዎች ግን የሉንም፤ ብዙ ባለሙያዎች አሉን ችግር የሚፈቱ ግን ብዙ የሉንም፤ ብዙ የሚናገሩ እንጂ ብዙ የሚሠሩ የሉንም፤ ብዙ ስሜታውያን እንጂ ብዙ በምክንያትና በጥልቀት የሚያስቡ የሉንም፤ ብዙ የሚወስዱ እንጂ ብዙ የሚሰጡ የሉንም፤ ሀገር የሚያቆስሉ እንጂ ሀገር የሚያክሙ ብዙ የሉንም። እንግዲህ እናንተ የትኛውን ቁጥር ትጨምራላችሁ?!

የብዙዎቻችሁ ወላጆች የእናንተን ዕድል አላገኙም። እነርሱ ያላገኙትን ዕድል ለእናንተ ሰጡ፤ ከዚህ በላይ የፍቅር ዕዳ የለምና ወላጆቻችሁንና ሀገራችሁን ውደዱ ሁሌም ስለደጎንነታቸው አስቡ። ለታላቅ ሀገራዊ ሓላፊነት እራሳችሁን አዘጋጁ።

ሕይወት በምዕራፍ የተከፋፈለች ናት። አንድ ምዕራፍ ሲያልቅ ሌላ ይከፈታል። በሕይወት ዘመናችሁ አንዱንና ወርቃማውን ምዕራፍ ዛሬ በስኬት ዘግታችሁታል። እንኳን ደስ አላችሁ! ለነገ ለራሱ ክፉቱ ይበቃዋል እንደተባለ ዛሬ ከወዳጅ ዘመዶቻችሁ ጋር ደስ ይበላችሁ። ደስታችሁን ቀድሱት። ያለልክ በመብላትና በመጠጣት ሳይሆን በሕሊና እርካታ ወላጆቻችሁን በማመስገን በልዩ ደስታ አክብሩት! ሂዱ ዛሬን ደስ ይበላችሁ!

በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ!

እግዚአብሔር ዘመናችሁን ይባርክ!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባረክ!





# <ሰልጨርሰካብልዲም>

በ1983 ዓ.ም. በዓለማያ ግብርና ዩኒቨርሲቲ (በአሁኑ ሃሮማያ) የ3ኛ ዓመት ተማሪ ነበርኩ። የዓመቱን ትምህርታችንን ወደ ማገባደድ አካባቢ ሳለን ተማሪዎች ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ተቋማት ሄደው እንዲሰለጥኑና በወቅቱ በነበረው የእርስ በርስ ጦርነት በመንግሥት በኩል እንዲሰለፉ ተወሰነ። በዚሁ መሠረት ተማሪዎች ሁሉ ወደ ብላቴ ወታደር ማሠልጠኛ እንዲዘምቱ ሲደረግ እኔም እንደ ተማሪነቴ ወደሥልጠናው ለመሄድ በግቢው ውስጥ የሚደረገውን ወታደራዊ የጤና ምርመራ ለማድረግ ተሰለፍኩ። ይሁንና በነበረኝ የጤና ችግር ምክንያት የጤና ምርመራውን ማለፍ ስላልቻልኩኝ በወቅቱ አጠራር (Medically Unfit) በሚል ግቢው ውስጥ እንድቀር ተደረገ።

ከወታደራዊ ሥልጠና የቀረነው በማኅበራዊና ኢኮኖሚ ዘርፍ በኩል ልትዘምቱ ትችላላችሁ በሚል በጣት የምንቆጠር ተማሪዎች እዛው ዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ቀርተን እንድንጠባበቅ ተደረገ። በዚህ አጋጣሚ ግቢ ውስጥ የቀረነው ተማሪዎች ቁጥራችን በጣም ትንሽ ስለነበረ ካሉት ሕንፃዎች በአንደኛው ሕንፃ ተሰባስበን በራሳችን ፈቃድ በየክፍሎች እንዲሁ ተከፋፍለን መኖር ስንጀምር የዚህ ጽሑፍ ታሪክ ባለቤት የሆነውን ሰው የመገናኘት እድሉን አገኘሁ።

ይህን ሰው በሚገርም ሁኔታ ምናልባትም በሚያሳፍረኝ ሁኔታ ስሙን አሁን በእርግጠኛነት የማላስታውሰውና የት እንዳለና በሕይወት ስለመኖሩ እንኳን መረጃ የሌለኝ በመሆኑ የልቤ ሐዘን ከባድ ነው።

ይሁንና አሁን የምነግራችሁ ተረት ከዚህ ሰው የሰማሁት ነው። ‹የነገረህን ተረት አስታውሰህ ስሙን ግን እንዴት ልተረሳው ቻልክ?› ብሎ የሚጠይቅ አንባቢ ይኖራል። ጥሩ ጥያቄ ነው። ለምን እንደሆነ ግን መልስ የለኝም።

ይህ ሰው በእድሜው ከእኛ በጣም ተለቅ ያለ በ1960ዎቹ መጨረሻ አካባቢ በኢህአፓ አባልነት ተጠርጥሮ በደርግ እስር ቤት ውስጥ ግርፋት የደረሰበትና ረጅም የእስር ጊዜ ያሳለፈ ነው። በዚህ ግርፋት የተነሣም እግሮቹ ላይ በደረሰበት ጉዳት እንደልብ ፈጠን ብሎ መራመድ የማይችል፣ ፀባዩ ለስላሳ፣ ተጫዋችና የዋህ ሰው እንደነበረ አስታውሳለሁ።





ከደርግ እስር ቤት የተረፈችውን ሕይወት በተስፋ ሞልቶ የግብርና ሳይንስ በዲፕሎማ ካጠና በኋላ የተወሰነ ጊዜ ሥራ ሠርቶ በኋላ ከእኛ ጋራ የዲግሪ ትምህርት ለመቀጠል ‹አድቫንስ ስታንዲግ› በሚባለው ፕሮግራም የገባ ሰው ነው። በሕይወቱ ብዙ መከራን፣ እንግልትን ያዬ፣ ማጣትና ማግኘትን የሚያውቅ ስነበረ ከእርሱ ጋራ መኖር ብዙም የሚከብድና የሚያስቸግር አልነበረም።

ይህ ሰው በጣም ከሚወዳቸው ነገሮች አንዱ ምናልባትም በእስር ቤት በተዘጋ በር ውስጥ ለረጅም ዓመታትን በማሳለፉ ሊሆን ይችላል ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ረጅም የእግር ጉዞ ማድረግ ይወዳል። ዶርም ውስጥ መቀመጥ ይጨንቀዋል። በዚህ ረጅም የእግር ጉዞው ውስጥ ሁሌም አብሬው እንድሄድ ይፈልግ ነበረ። እኔ ደግሞ የእግር ጉዞ ማድረግ ብዙም ደስ አይለኝም። ይልቁንም አልጋዬ ላይ ሁኜ በአካዳሚክ ነፃነት ያገኘሁትን መጽሐፍ ዝም ብሎ ከላይብረሪ እየወሰዱ ማንበብ አለበለዚያ ደግሞ ቁጭ ብሎ ማውራት የሚቀናኝ አይነት ሰው ነበርኩ። እናም ሁልጊዜ አብሬው እንድሄድ ለማግባባት የሚያደርገው ጥረት ብዙ ጊዜ ባይሳካለትም አልፎ አልፎ አብሬው እሄዳለሁ።

እንደተለመደው አንድ ቀን፡

“ስማ እስኪ! ዛሬ ቀኑ ደስ ይላል፣ አየሩ ነፋሻማ ነው። አሁን ወጥተን በዚያ በሀይቁ በኩል አድርገን ዞረን ብንመጣ ምን ይመስልሃል?” አለኝ።

ሀይቁ የሚለው ከግቢያችን ደቡብ ምዕራብ የሚገኘው ‹የሃሮማያ ሀይቅ› ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ግቢ ከዚህ ሐይቅ ጋር ተጎራባች ነው። እንደተለመደው፡

“አይ ደክሞኛል አልሄድም” አልኩት።

ሁልጊዜ ማባበሉ ሲሰለቸው ጊዜ ነው መሰለኝ ድንገት ቁጭ አለና ዝም ብሎ የሆነ ነገር ማውራት ጀመረ። ከዚህ በኋላ የምነግራችሁን ታሪክ በዚህ መልኩ የጀመረው ነበር።

አንድ አምስት ደቂቃ ካወራኝ በኋላ ዝም ብሎ ተነሣና ጫማውን አድርጎ ከዶርሚተሪ ወጥቶ መሄድ ጀመረ። እኔም በፍጥነት ጫማዬን አድርጌ ተከትዬው ሄድኩኝ። ጥሎብኝ ተረትና ወግ እወዳለሁ!

የምንኖርበትን ሕንፃ ለቀን ወደ ሀይቁ አቅጣጫ ቁልቁል በዝግታ እጆቹን ከኪሱ ከቶ እየተራመደ ሲሄድ እኔ ከጎኑ ሆኜ “እሺ… የሚገርም ነው” እላለሁ። እርሱ በዝግታ ተረቱንም መንገዱንም ይዞ ይራመዳል። እኔም ሳይታወቀኝ በተረቱ ገዝቶኝ እርሱም የሚፈልገውን የእግር ጉዞ የሚፈልገውን እርቀት እና ጊዜ ከተጓዝን በኋላ ተመልሰን ወደ ዶርማችን ስንመለስ ተረቱ አላበቃም ነበር።

“ለዛሬው እዚህ ላይ ይብቃ” አለኝ ዶርም ስንደርስ።

“እንዴ! እንዲህማ አይሆንም ትጨርስልኛለህ” አልኩት።

“አይ ነገርኩህ እኮ! ነገ እቀጥልልሃለው” አለኝ።





ይህንን ያቆመበትን ቦታ በታሪኩ መካከል ስለማስታውሳችሁ እናንተም ስትደርሱበት ምን ያክል ወጣቱን ልቤን እንዳንጠለጠለው ልትረዱት ትችላላችሁ። ለማንኛውም በዚህ መልክ ማታ እራት በልተን ስንመለስ ብለምን ባደርግ ብሠራው ሊቀጥልልኝ አልፈለገም። ስለዚህ የሚቀጥለውን ቀን አስራ አንድ ሰዓት መጠባበቅ ነበረብኝ። በሚቀጥለው ቀንም ይህን ትረካውን ቀጠለ፤ ያን ቀንም አላለቀም። ንዝንዝ ሳደርገው ደግሞ፡ “እስኪ የሰማሃውን ለማንሰላሰል ጊዜ ይኑርህ” እያለ ይቀልድብኛል።

ብቻ እንዲህ እያደረገ የእግር ጉዞውንም ተረቱንም ለቀናት ቀጠለ።

ይሁንና የሚነግረኝ ትረካ ፍፃሜ ሳያገኝ “ጀግናው የኢሕአዴግ ሰራዊት አዲስ አበባ ገባ” የሚል ዜና ሰማንና በእግር እየተንሸራሸርን ጣፋጭ ትረካ የምንሰማበትና የምናጣጥምበት ስሜት ጠፍቶ በጭንቀት ተዋጥን። ከቤተሰቦቻችን ጋር የምንቀላቀልበት ጊዜ እየናፈቀን ሁላችንም ተሸብረን ተረቱንም ሳይጨርስልኝ እነሆ ለመለያየት በቃን።

ሁላችንም ወደ የቤተሰቦቻችን በብዙ ጭንቅ ተጉዘን ከደረስን ከወራት በኋላ ወደ ግቢ ብንመለስም ይህ ሰው ተመልሶ ወደ ግቢ ስለመምጣቱ እርግጠኛ አልነበርኩም። ምክንያቱም የሁለት ዓመት ትምህርት በአንድ ዓመት መጨረስ ስለነበረብን ወከባ ላይ ስለነበርን በዛ ላይ የጥናት መስካችን የተለያዩ ስለሆነ ይመስለኛል።

ያም ሆነ ይህ ግን የተረቱን ፍፃሜ ሳይነግረኝ በመቅረቱ ሁል ጊዜ ይቆጨኛል። የትረካውን ፍሰት ተከትዬ በምናቤ ልጨርሰውና ልጻፈው እልና መብቱን የተጋፋሁት ስለሚመስለኝ አቅም አጣለሁ። ይሁን እንጂ እርሱ የተረከልኝን ያክል ባይሆን እንኳን በተቀራረበ ትውስታ የነገረኝን ለአንባቢ ለማካፈል ወሰንኩ።

ተረቱን ሲጀምርው እንዲህ ብሎ ነበር።

"በድሮ ጊዜ..." አለ እረጋ ብሎ "በድሮ ጊዜ ዓለም እንደ አሁኑ በአህጉር ተቀምራ፣ በሀገራት ተከፋፍላ ብዙ ከመሆኗ በፊት በአራት ንጉሠ ነገሥታት ትመራ ነበር። የምዕራቡ ንጉሥ፣ የምሥራቁ ንጉሥ፣ የሰሜኑ ንጉሥ፣ የደቡቡ ንጉሥ እየተባለ በዚህ መንገድ ትመራ ነበረ። አሁን የማወራህ በምዕራቡ ንጉሥ እና በምሥራቁ ንጉሥ የተፈፀመ አንድ ገራሚ ታሪክ ነው።

ይገርምሀል! የምዕራቡ ንጉሥ እጅግ ሲበዛ ልጅ ይወድ ነበር። መንግሥቱ የተደላደለ፣ ሀገሩም ልምላሜ የተሞላ፣ ሕዝቡም በሰላም ይኖራሉ ቢባልም ይህ ሰው ግን የልጅ ፍቅር ያንገበግበው ነበር። ከሕግ ሚስቱ ከንግሥቲቱ አንድ ወንድ ልጅ ብቻ የወለደ ሲሆን በዛ ሁሉ ሀብቱ እና በዛ ሁሉ ግዛቱ ግን ብዙ ልጆች ሊኖሩት ሲችል አንድ ልጅ ብቻ ወልዶ በመቅረቱ ሁልጊዜ በጣም ያዝን ነበር። ይህንንም ልጅ ወደ ኋላ እድሜው መጨረሻ እንደወለደው ይነገራል።



ሰበዝ

አንድ ቀን በሰረገላ ተጭኖ በወታደርና በመኳንንት ታጅቦ ሲሄድ አንዲት የእኔ ቢጤ ሴት መንገድ ዳር ቁጭ ብላ ስትለምን ያያል። ይህች ሴት ከእርሱ ልጅ በእድሜ እኩያ የሆነ ወንድ ልጅ ከጎኗ ቁጭ ብሏል። ልጁ በእርሱ ልጅ እድሜ አካባቢ ያለ በመሆኑ የሆነ ልቡን የሚነካው ነገር መጣና ከሰረገላው ወርዶ ከአጀቡ ተለይቶ ወደ ሴቷ ጠጋ ብሎ፡

“የምትፈልጊውን ዋጋ እከፍልሻለሁ፡ ይህንን ልጅ እንደ ልጄ አድርጌ በአባትነት ፍቅር ላሳድገው እባክሽ ስጭኝ?” ይላታል።

ሴትዮዋም “እዚህ ጎዳና ከእኔ ጋራ በችግር ከሚጠበስ በንጉሥ እልፍኝ የንጉሥ ልጅ አምሳል ይዞ ቢያድግ ምን ከፋቶኝ” አለችው። ንጉሡም ለዚህች ሴት ብዙ ብርና ወርቅ ከሰጣት በኋላ ልጁን ወደ ቤተ-መንግሥት ይዞ ሄደ።

ከዚህ በኋላ ለመለየትና ለታሪኩ አተራረክ እንዲመች ከቤት የተወለደውን ልጅ ‹የንግሥቲቱ ልጅ› ይኼኛውን ልጅ ደግሞ ‹የደሃይቱ ልጅ› እንለዋለን። ለነገሩ ንጉሡ እንደ ልጅ አድርጎ እንደወሰደው እናውቃለን።

ንጉሡ ሁለቱንም ልጆቹን በእኩል ዓይን እያዩ በቤተ-መንግሥት በልዩ ፍቅር፣ በባለሟልነት፣ በክብር አሳደጋቸው። እንደ ሀገሩ ወግና ልማድ፣ እንደ ንጉሥ ልጅነታቸው በፈረስ ጉግስ፣ በጦር ውርወራ፣ በአደን፣ በውኃ ዋና... በተለያዩ ትምህርቶች ተኮትኩተውና ሠልጥነው አደጉ።

እኩል ሥልጠና እኩል እንክብካቤ ቢያገኙም መቼም እኩል ስጦታ፣ እኩል ችሎታ አይኖርምና፤ የደሀይቱ ልጅ ግን አንድ የተለዩ ችሎታ ነበረው። ይኸውም የሚደንቅ የሥዕል ችሎታ ነበረው። ያየውን ነገር ልክ የፎቶግራፍ ያክል በሥዕል ማስቀረት አቅም አለው። ይህን ችሎታውን አባቱ እያበረታታው የበለጠ እያዳበረው ሄደ። በሌላውም ሙያ ቢሆን የተዋጣለት ነበር።

በወንደማማቾች መካከል ሁሌም እንደሚሆነው ከወንድሙ ጋራ በአደን ፉክክር ገጠሙ። ሁልጊዜ አደን ሲወጡ አደጋ ጣዮች አደጋ እንዳያደርሱባቸው በብዙ አጃቢዎች ተከበው ቢሆንም አልፎ አልፎ የገደሉትን እያነሱ ‹እኔ ብዙ ገድያለሁ፤ አይ እኔ ነኝ ብዙ የገደልኩ› በሚል ይፎካከራሉ። ነገር ግን አጃቢዎቹም ወታደሮቹም ስለሚተኩሱና አብረው አደኑ ላይ ስለሚካፈሉ በትክክል የእነርሱ የሥራ ውጤት ብቻ አለመሆኑን ራሳቸውም ያውቁታል።

አንድ ቀን የንግሥቲቱ ልጅ፡

"በትክክል ጥሩ ተኳሽና ጥሩ አዳኝ መሆናችንን፣ ከእኔና ከአንተ ማን እንደሚበልጥም ለማወቅ ለምን ተደብቀን ማንም ሳይከተለን ወደ ጫካ አንሄድም? ከዛ ግዳያችንን ይዘን ወደ ማታ እንገናኛለን። ብዙ የገደለ አሸናፊ ይባላል" የሚል የፉክክር ጥያቄ ያቀርባል።





በሐሳቡ ይስማሙና በጠዋት አጃቢ ሳያስከትሉ ከቤተ-መንግሥት ሹልክ ብለው መሣሪያዎቻቸውንና ፈረሶቻቸውን ይዘው ማለቂያ ወደሌለው የሀገራቸው ጫካ ገቡ። ከዚያም አንድ ቦታ ጀመሩና ‹አንተ በዚህ አቅጣጫ ሂድ እኔ ደግሞ በዚህ አቅጣጫ እሄዳለሁ። ተመልሰን እዚህ ቦታ እንድንገናኝ› በሚል ተቀጣጥረው ተለያዩ።

የደሃይቱ ልጅ ብዙ አውሬዎችን እየገደለ ከሚገለውም ለምልክት ይሆን ዘንድ ከአካላቸው ትንሽ እየቆረጠ በኮሮጆው እየከተተ በስሜትና በጀግንነት ወደፊት ነጎደ። በሙሉ ትኩረቱ የነበረው አውሬዎችን አነጣጥሮ መግደል፣ የገደለውን ቆርጦ መያዝ ስለነበረ ረጅም ጉዞ እንኳ እንደተጓዘ አልታወቀውም ነበር። የመጣበትን አቅጣጫ ተመልሶ ለመሄድ በሚያስችል ሁኔታ እንኳን አላገናዘበም ነበር።

በዚህ ሁኔታ ብዙ ከገደለ በኋላ ቀኑ እየመሸ ሲሄድ ድንገት ቀና ብሎ ጀምበርን ሲያይ የተቀጣጠሩበት ሰዓት መድረሱን አወቀ። ነገር ግን እንዴት እንደሚመለስ ምልክት ባለመያዙ በዛ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ መንገድ ጠፋበት። ጫካ ውስጥ ያለ ሰው በጥንቃቄ ምልክት ካላደረገ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አቅጣጫ መሳቱ የተለመደ በመሆኑ ይህ ልጅ የሄደበትን አቅጣጫ ትቶ በተቃራኒ የባሰ እየራቀ መሄድ ጀመረ። አንድ ቀን ሙሉ የመጣበትን መንገድ ጭራሽ በተቃራኒ አቅጣጫ ስለሄደ ጨርሶ መመለስ እንደማይችል ሲያውቅ ከአንድ ዛፍ ላይ ወጥቶ ምሽቱን ለማሳለፍ ተገደደ።"

(የመጀመሪያው ቀን ትረካ እዚህ ላይ ነበር የቆመው)

"…..በቤተ-መንግሥት ተቀማጥሎ ያደገ ልጅ በዚህ ድቅድቅ ጨለማ ዛፍ ላይ ወጥቶ ጠብመንጃውን ተንተርሶ ማደር ግዴታው ነበር። በማግስቱ እንደገና ከወንደሙ ጋር ወደ ተቀጣጠረበት ለመመለስ ፍለጋ ጀመረ። አሁንም የባሰ እንጂ የተሻለ አቅጣጫ ስላልያዘ ጨርሶ ከሃገሩ እንደጠፋ ተረዳ። ርሃብና ድካም ተጋግዘው ተስፋ አስቆረጡትና በመጨረሻ አመሻሽ ላይ ከአንዲት ዛፍ ሥር ቁጭ እንዳለ እንቅልፍ ወሰደው።

ለምን ያክል ጊዜ እንደተኛ ባያውቀውም ድንገት ጎኑን የሆነ ሹል ነገር ወ..ጋ.. ሲያደርገው ከእንቅልፉ ባንኖ ተነሣ። ተደናብሮ ‹ምንድን ነው? የት ነው?" ሲል ፀጉራቸው የተንጨበረረ፣ ልብሳቸው የቆሸሸ እጅግ አስፈሪ መልክ ያላቸው ሽፍቶች ዙሪያውን ጠብመንጃ ደቅነው ከበውታል። እጅግ ደነገጠ!

ምንም ሳያናግሩት ተነሥቶ እንዲከተል በምልክት አዘዙትና ቀኑን ሙሉ ሲጓዙ ውለው ሊመሽ አካባቢ የሆነ ቦታ አረፍ ብለው የታደነ አውሬ ጠባብሰው ከበሉ በኋላ እሳት ከበው እዛው አደሩ።

በማግስቱ እስከ እኩለቀን ከተጓዙ በኋላ ጫካውን ጨርሰው የሆነ ተራራ አካባቢ ሲደርሱ ዓይኖቹን በጨርቅ ሸፍነው አንድ ሰው ገመድ ከእጁ አስሮ እየመራው መንገዳቸውን ቀጠሉ። ተራራውን ወጥቶ ቁልቁል የሚወርድ በሚመስል መንገድ አንደሚጓዝ ቢገምትም የት አንደሚወስዱት፣ ለምን





እንደሚወስዱት የነገረው የለም። እጅግ አስጨናቂ ጉዞ ነበር!

ለአንድ ለሦስት ሰዓት አካባቢ ከተጓዙ በኋላ ዓይኖቹን ሲከፍቱለት ዙሪያውን በለመለመ ደን የተከበበ ደልዳላ መሬት ላይ ያረፈ እጅግ የሚያምር ቤተ-መንግሥት የሚመስል ሕንፃ ፊት ለፊት ደርሰዋል።

ሰዎቹ የያዙትን ንብረት ካራገፉ በኋላ መንገድ ላይ ያደኑትን ግዳይ ጠብሰው እርሱን ጨምሮ ሁሉም በረንዳው ላይ ሆነው በሉ። ማታ ላይ የሆነ ለክፉ የማይሰጥ ክፍል ውስጥ ተዘግቶበት አደረ። በሚቀጥለው ቀን እንዲሁ የተራረፈ ሥጋ እንደነገሩ ተጠባብሶ ተበልቶ ትንሽ እረፍት እንዳደረጉ ወደ ቤቱ ውስጥ ይዘውት ዘለቁና ሁሉንም የቤቱ ክፍሎች አስጎበኙት። እንደ እንግዳ ተቀብለው የሚያስጎበኙት ያክል ተሰማው። ቢያንስ አሁን ከእነርሱ ጋር መነጋገር ጀምሯል፣ አብሯቸውም በልቷል። ያልሰለጠኑና ሽፍቶች ቢሆኑም ለጊዜውም ቢሆን ቀቅለው የሚበሉት ጭራቆች ወይም ቆራርጠው የሚጥሉት ጨካኞች አይመስሉም። የመረጋጋት ስሜት ተሰማው።

በየክፍሉ በዓይነትም በመጠንም የበዛ ንብረት ተዝረክርኮ ተከማችቷል። ውድ ጌጣጌጥ፣ አልባሳት፣ መጠጦች፣ የምግብ ጥሬ ዕቃ፣ ሌላው ቀርቶ የሚወደው ቀለምና ብሩሽ በዓይነት ተከማችቷል።

"ስማ!" አለው ከመካከላቸው አንዱ፣

"ከዚህ በኋላ ከዚህ ቤት ውስጥ ካለው ነገር ሁሉ የፈለከውን

ነገር መጠቀም ትችላለህ። ቤቱ ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ ያንተ ነው” አለና “የማይፈቀድልህ አንድ ነገር ቢኖር ይህን ቤት ለቆ መሄድ ነው። ለቅቄ እሄዳለሁ ካልክ ያኔ እንደሞትክ ቁጠረው” አለ ፈርጠም ብሎ በአመልካች ጣቱ እያስፈራራ።

ቆየና “ተከተለኝ!” አለው። ሁሉም ተያይዘው ወደ ፎቅ ሲወጡ ቀደም ብሎ በደንብ ያላስተዋለው የተለየ ክፍል ደረሱ። ክፍሉ ግድግዳው በጌጠኛ ገመድ እየታሰረ በቀርቅሃ የተገደገደ ነው። አንድ ክፍት ጠባብ መስኮት ሲኖረው በር ግን የለውም።

ሌላኛው ድምጸ ሸካራ ሰው ጉሮሮውን እንደማጽዳት ‹እህ.ህ.› አለና

“እዚህ ክፍል ውስጥ አምላካችን አለ እና...” ሲል ድንጋጤ መጣበትና ሲርበተበት አይቶት

“ምንም የሚያስፈራ ነገር የለም” ሲል የሚጉረጠረጡት አይኖቹ ከሸካራው ድምጹ ጋር ተዳምሮ በራሱ የሚያሸብር መሆኑን አልተረዳውም።

“ብቻ ማድረግ ያለብህ ... እ.. ከምትመገበው ምግብ እና ከምትጠጣው መጠጥ ውስጥ ቢያንስ ጠዋትና ማታ በመስኮቱ በኩል ፊትህን አዙረህ ሳትመለከት የሚበላውን በሳህን የሚጠጣውን በብርጭቆ አድርገህ ታቀርባለህ።” አለ





መጀመሪያ ያናገረው ቀበል አደረገና “ልብ በል! ወደ መስኮቱ ፊትህን ሳታዞር ተጠግተህ ማቀበል አለብህ። እያየኸው ከሰጠኸው ግን መሞትክን እንድታውቀው” አለው።

“ይኼ ሰውዬ ትሞታለህ ከማለት ሌላ አያውቅም እንዴ?” አለ በልቡ።

እነርሱ እንደ ለመዱት የአደን ግዳያቸውን በጥሬውና ጠብሰው እየበሉ እርሱ ቤት ውስጥ ካለው በሚፈልገው መልክ እየሠራ እንዲታዘዘው ለራሱ ካዘጋጀው እየቀነሰ ‹ለአምላካቸው› በመስኮት እያቀበለ ሦስት ቀናትን ያክል አብረው ቆዩ።"

(የሁለተኛው ቀን ትረካ እዚህ ላይ ነበር የቆመው)

"....መረጋጋቱንና የተሰጠውን ‹አምላካቸውን› የመቀለብ ሥራ እየተወጣ መሆኑን ሲያረጋግጡ ለተለመደው ዘረፋቸው ሊወጡ ተዘጋጁ።

“ወደ ምሥራቁ ንጉሥ ለዘረፋ ልንሄድ ነው፣ አስራ አምሥት ቀናት ቆይተን እንመለሳለን። ቤቱና ቤቱ ውስጥ ያለው ነገር በሙሉ ተሰጥቶሃል። ድጋሜ የምናስጠነቅቅህ ነገር ቢኖር ከዚህ ቦታ ወጥተህ ብናገኝህ መሞትህን እንዳትረሳ ነው!”፤

“አምላካችንንም እንዳትረሳ” አሉት እየተቀባበሉ።

ከዚያም ወደ ተራራው አቅጣጫ ከዓይኑ እየራቁ ሄዱ።

ከተወዳጅ አባቱና ቤተሰቡ ከተቀማጠለው የቤተ መንግሥት ኑሮ ተለይቶ የት እንዳለ በማያውቀው ስፍራ የቁም እስረኛ

ሆኖ መቀመጡ አሳዛኝ ነበር። ቢሆንም እውነታውን ከመቀበል ያለፈ ለጊዜው የሚያደርገው ምንም ነገር ስላልነበር ግቢውንና የቤቱን ክፍሎች አንድ ባንድ ማጥናት ጀመረ።

የሕይዎትን ዕጣ ፈንታ በፀጋ ተቀብሎ ቀለል ለማድረግ የሚወደውን ሥዕል እየሣለና ቤት ውስጥ በተቀመጡት ሙዚቃ ማዳመጫዎች ሙዚቃ እያዳመጠ እንደታዘዘው ጠዋትና ማታ ምግብ እየሠራ ከሠራው ምግብ ‹ለአምላካቸው› ፊቱን እያዞረ እየሰጠ እርሱም እየተቀበለው 15 ቀናትን ቆዬ።

ቤቱን ሲያጠና እነዚህ ሽፍቶች ሀብትና ንብረት እየዘረፉ ያመጣሉ እንጂ የሚያመጡትን ሀብትና ንብረት እንዴት እንደሚጠቀሙት እንደማያውቁ ተገንዝቧል።

ምግባቸው የዱር አውሬ ሥጋ ብቻ እንደሆነ ተረድቷል። እናም በሚመጡበት ቀን ዳቦ ጋግሮ፣ ከመጠጡም ሊመጥናቸው የሚችለውን መጠጥ አዘጋጅቶ፣ ሻይ ቡናም እንደምርጫቸው አዘጋጅቶ ጠበቃቸው።

እንደተለመደው ዘርፈው ያመጡትን ሀብት በየክፍሉ አኑረው ሲጨርሱ ግብዣውን አቀረበ። ከለመዱት ውጭ የበሰለና የሚጣፍጥ ነገር ሲቀምሱ በጣም ተደሰቱ። ልጁንም ወደዱት።

"እንዲህማ ከሆነ በጣም ነው የምንወድህ! በቃ አንተ እኛ ጋር ነው የምትኖር" እያሉ አሞካሹት። እንደተለመደው ከሦስት ቀናት በኋላ





"አሁን ደግሞ ወደ ደቡቡ ንጉሥ አገር ልንሄድ ስለሆነ ስንመጣ ደግሞ በጣም የሚጣፍጥ አዘጋጅተህ እንድትቆየን እሺ?" አሉትና ተሰናብተውት ሄዱ።

ወደ ደቡብ በሄዱ በሁለተኛው ቀን እንደተለመደው በጠዋት ምግብና መጠጥ አዘጋጅቶ ‹ለአምላክ› ተብዬው ሊያቀብል ሲሄድ የሆነ ነገር በአዕምሮው ተመላለሰ።

"ለምንድን ነው ፊቴን ዙሬ የምሰጠው? ለምን ፊት ለፊት አልሰጠውም?" አለ።

"እንዴ ብሞትስ?" አለ ለራሱ።

"በዚህ ሁኔታ መኖርም መሞትም ያው አንድ ነው! የማላውቀውን ፍጥረት እየቀለብኩ ከመኖር የሚመጣውን መቀበል ይሻላል" አለና ራሱን አደፋፈረ። ሽፍቶቹ አፍነው ያመጡት ‹የአምላካቸው ቀላቢ› እንዲሆን ፈልገው እንደሆነ አምኗል።

"ከመሞት መሰንበት አይሻልም?" የሚል ስሜት እንደገና ታገለው።

ከራሱ ጋር ብዙ ከታገለ በኋላ ፊቱን ሳያዞር ፊት ለፊት እያዩ ለመስጠት ወሰነና ወደ መስኮቱ ጠጋ ብሎ የምግብ ሳህን የያዘውን እጁን ዘረጋ።

በዚህን ጊዜ ከመስኮቱ ውስጥ አንድ ድምፅ ተሰማ።

“እንዳትዞር!....እንዳትዞር!” የሚል ነበር።"

(የሠላተኛው ቀን ትረካ እዚህ ላይ ነበር የቆመው)

"...በጣም ከመደንገጡ የተነሣ በቁሙ ሊወድቅ ምንም አልቀረውም ነበር። ራሱን አረጋግቶና ሕሊናውን ሰብስቦ ሲያዳምጥ እንደገና፡

“ወደ እኔ እንዳትዞር! ፊትህን እንደታዘዝከው አድርገህ ስጠኝ” የሚል ድምፅ ሲሰማ፤ የሴት ድምፅ መሆኑን ተረዳ።

“ማን ነሽ አንቺ?!” አለ።

“እባክህ እንዳትዞር ይገለሃል! እንዳትዞር ይገለሃል፣ ፊትክን ዙርና ስጠኝ!” አለችው።

“ቤት ውስጥ ከእኔ በስተቀር ማንም የለም እኮ” አላት

“ሽፍቶቹ የት ሄዱ?” አለችው

“ለ15 ቀናት ወደ ደቡብ ሄደዋል። ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም” አላትና “ይልቁንስ አንቺ ማነሽ? እስኪ ወደ መስኮቱ ጠጋ ብለሽ አናግሪኝ?” ብሎ ተማጸናት።

እርሷም ወደ መስኮቱ ጠጋ ስትል ከውጭ ባለው ብርሃን ሙሉ ፊቷን ለማየት ቻለ። እጅግ የምታምር ውብ ሴት ናት። የልዕልትነት ማዕረግ ያላት መሆኗንም ከላይዋ ላይ ባደረገችው አክሊል ለመረዳት ቻለ። ቁንጅናዋ ይኼነው የሚባል አልነበረም።





ያየውን ለማመን ተስኖት ለሴኮንዶች ፈዞ ቀረ። ቆይቶ እንደመባነን አለና፡

“ለመሆኑ ማነሽ? እንዴት እዚህ ውስጥ ትኖሪያለሽ? ሰዎቹን የምታገርያቸው አንቺ ነሽን?” አላት አከታትሎ።

“የምሥራቁ ንጉሥ ልጅ ነኝ። ባጋጣሚ ለሽርሽር በወጣሁበት እዚህ ጠልፈው አመጡኝ።” አለች በሐዘን።

“ታዲያ ለምን እዚህ ውስጥ ቆለፉብሽ?” አላት እርሱም ሐዘኗ ተጋብቶት።

“እዚህ ካመጡኝ በኋላ ከመካከላቸው ‹ማን ያግባት› በሚለው እርስ በርሳቸው ተጣልተው በመካከላቸው በተነሣ ግርግር ግማሾቹ ተገዳድለው ዛሬ የምታያቸው ከበፊቱ ከነበረው ቁጥራቸው ግማሾቹን ብቻ ነው።” አለች

“እና መጨረሻው ምን ሆነ?” አላት ጓጉቶ። አሁን በመስኮቱ ግራና ቀኝ ቁመው ለረጅም ጊዜ እንደሚተዋወቁ ሁነው ነው የሚያወሩት።

“የቀሩት እርስ በርስ መጣላቱ የትም እንደማያደርሳቸው ሲያውቁ ባንድ ነገር ተስማሙ” አለችው

“በምን?” አላት ጥድፍ ብሎ።

“እርስ በርሳችን ከምንገዳደል ከመካከላችን እርሷ የመረጠችውን ለምን አታገባም? ከመካከላችን መምረጥ የእርሷ ግዴታ ሆኖ ምርጫዋን ማክበር የእኛ ግዴታ ይሁን ብለው ተስማምተው

ይህንኑ ትዕዛዝ ነገሩኝ" አለች።

"እና አንቺ መረጥሽ?" አላት ብሽቅ ብሎ። ለምን እንደበሸቀ ለራሱም አልታወቀውም።

"እንደምትገምተው ከመካከላቸው መምረጥ ለእኔ ፈጽሞ የሚታሰብ አልነበርም። መምረጥ ግን መብቴ ሳይሆን ግዴታዬ ነበር። በወቅቱ ‹ከመካከላችሁ የሚሆነኝ የለም!› ብዬ ብናገር ሞት የሚጠብቀኝ መሆኑን አውቃለሁ" አለች።

"እና ምን አደረግሽ?" አላት አለመምረጧን ሲያውቅ አየተረጋጋ።

"ይኸውልህ! የአዕምሮ ልኬታቸውን ተረድቼ ጥያቄውን በጥያቄ ጥበብ ለመብለጥ ፈልኩ። በዚህም ጊዜ ለመግዛት እንደምችል ገመትኩ።" አለች

"እንዴት?" አላት ፈገግ ብሎ

"ከመካከላቸው አንደኛውን ለማግባት ፈቃዴ እንደሆነ፣ ነገር ግን ከመካከላቸው የምፈልገውን የሚያሟላልኝ ሰው ከተገኘ ብቻ እንደማገባ ቃል ሰጠኋቸው።"

"ምንድን ነበር እንዲያሟሉልሽ የጠየቅሽ?" አላት በጉጉት። በሐሳቡም ሞልቶ የተረፈውን የአባቱን ጌትነት እያሰበ።





"ምን መሰለህ ያልኳቸው! እ... ‹ከመካከላችሁ ከምፈልጋቸው ነገሮች አንዱን ይዞ ቀድሞ የመጣ እውነትም ባሌ የሚሆን ጀግና ነው። ፈቃዴ ሁሉ ለእርሱ ትሆናለች። ይህንን ካላደረጋችሁ ግን ማንንም ከመካከላችሁ አላገባም። ለምን ጀግና አይደላችሁምና?›። ይህን ስል ጀብደኞች በመሆናቸው ‹በዓለም ላይ ያለ ማንኛውንም ነገር ጠይቂን እናመጣለን!› አሉ በኩራት። እኔም መልካም አልኩና ከሚከተሉት አንዱን ቀድሞ ያመጣ ሰው የእኔ ባል ይሆናል አልኳቸው።" ስትል

"እና ምንድን ነበር?" አላት በጉጉት።

"ልነግርህም አይደል? አለችውና፣

" የበቅሎ ክበድ በሐር ገመድ ታሥሯ፣ ወይም

የተጠበሰ ቅቤ በገደል ማር ታሽቶ፣ ወይም

በዶሮ ታርሶ የተመረተ የገብስ እሸት፣ ወይም

በወንፊት የተቀዳ የምንጭ ውሃ፣ አለበለዚያ ደግሞ

ነጭ ኑግ በጥቁር ወተት ተለውሶ በሶ፣" ነበር አለችው።

"እና እነርሱ ምን አሉ?" አላት

"እነርሱማ ሁሉም ፈነጠዙና፣

‹ይህንንማ በምዕራቡም፣ በምሥራቁም፣ በደቡቡም፣ በሰሜኑም ሄደን በየጋራው፣ በየሜዳው፣ ቤተ-መንግሥት ሳይቀር ኀዳ

ጎድጓዳውን አስሰን ከመካከላችን አንዱ ማምጣቱ የማይቀር ነው።› አሉና ‹ እስከዛ ምን ይሁን?› ሲባል።

‹ማንም ሰው ይህንን ሳያሟላ ለጋብቻ ጥያቄ ወይም ለሌላ ጉዳይ እርሷ ዘንድ እንዳይደርስ በአንድ ክፍል ውስጥ ተቆልፋ ትቀመጥ። ክፍሉ ደግሞ በቀላሉ መከፈትና መዘጋት የሚችል ሳይሆን እንዳውም ግድግዳውንም አፍርሶ መልሶ ሊጠግነው በማይቻለው ሁኔታ ተሠርቶ መቀመጥ አለባት ተባለ። አንድ ሰው ብቻ እየቀረ ምግብ እያቀበለኝና እየጠበቀኝ፡ ያም ሰው እኔ ውስጥ እንዳይገናኝ ተመልከተው ግድግዳው በልዩ ሁኔታ የተሠራ ነው። በልዩ የገመድ ማሰሪያ በጌጥ የታሰረ ነው። ተፈትቶ እንደገና ቢታሰር አስተሳሰሩ ስለሚጠፋ መፈታቱ ይታወቃል። እና ሲመጡ ሊገድሉት ይችላሉ። በዚህ ምክንያት ወደ እኔ እንዳይቀርብ ፊቴንም አይቶ እንዳይፈተን ፊታቸውን እያዞሩ እንዲሰጡኝ በወሰኑት መሠረት አንተ እስከመጣህበት ጊዜ ድረስ በምታየው ሁኔታ አስቀመጡኝ" አለችው።

ባሳለፈችው ፈተና እጅግ ሲያዝን የቀረበላትን ፈተና የተወጣችበትን መንገድ ደግሞ "በጣም ይገርማል" እያለ እጅግ ሲያደንቅ ቆዬና፡

"እንዲያው ለመሆኑ ከዘረዘርሻቸው ውስጥ አንዱ እንኳን የሚገኝ ይመስልሻል?" አላት

"ዋናው ነገር እርሱ አይደል?" አለችውና ተሳሳቁ።





"እና አሁን በያገሩ የሚንከራተቱት ይህንኑ ፍለጋ መሆኑ ነው?" ሲላት

"ነው እንጂ። ንብረትማ ቤቱ ውስጥ የሞላው ዘላለም ያኖራቸው አልነበር?" አለች።

በመካከላቸው ለሴኮንዶች ዝምታ ሰፍኖ ከቆዬ በኋላ

"ስለአንተ እኮ አልነገርከኝም!" አለችው። ድምጿ እንደ መልኳ ያማረ ሙዚቃዊ ቃና ያለው ነው። ያሳለፈችውን ፈተና ስታወራ መከራዋን ሳይሆን ለስላሳ ሙዚቃ የሚደመጥ ያክል ልብን ይሰረስራል።

"የእኔም እንዳንቺ ተመሳሳይነት አለው" አለና የምዕራቡ ንጉሥ ልጅ እንደነበረ የልጅነት ሕይወቱን ጭምር፣ ከወንድሙ ጋር በመገዳደር ለአደን ወጥተው አቅጣጫ ጠፍቶበት ከወንድሙም፣ ከአባቱም ሳይገናኝ ሲንከራተት እነዚህ ሰዎች እንዳገኙት ተረከላት።

ተመሳሳይ ደረጃ የነበራቸውና ተመሳሳይ ዕጣ ፈንታ የገጠማቸው መጪው ተስፋቸውም የተሳሰረ መሆኑን ስለተረዱ ልቦናቸው ተቀራረበ።

"ለምን ከዚህ ጨለማ ክፍል አትወጭምና ምን ማድረግ እንዳለብን አንመካከርም?" አላት

"አይሆንም! ልወጣማ አልችልም!" አለች ፈርጠም ብላ

"ለምን?" አላት ምክንያቱን ቢያውቀውም ከእርሷ መስማት ፈልጎ

"እንዲገድሉህ አልፈልግም! ግድግዳው እየው እንዴት እንደታሰረ፣ አንዴ ገመዱን ከፈታኸው መልሰህ ማሰር ስለማትችል አደጋ ውስጥ እንወድቃለን" አለች።

"ለዚህ እንኳን አታስቢ፡ ዘዴ አለው" አለና ወደ ሌላኛው ክፍል በፍጥነት ሄዶ ወረቀት፣ ብሩሽና ቀለም ይዞ ተመለሰ። በተካነው የሥዕል ችሎታው ግድግዳውንና የገመዱን አጠላለፍ በጥንቃቄ ንድፉን ሣለና ገመዱን ፈትቶ ከጨለማው ክፍል አወጣት።

የናፈቃትን የፀሐይ ብርሃንና ንጹህ አየር እንደልቧ አገኘች። የምትፈልገውን ምግብ አዘጋጅታ ለመመገብ በቃች። ግሩም የሆነ ፒያኖ የመጫዎት ችሎታዋን አወጣችው። አለንጋ ጣቶቿን ፒያኖው ቁልፍ ላይ እያራወጠች የሙዚቃውን ስልት ተከትላ አንገቷን ስትሰብቀው ጸጉሯ በበኩሉ በትክሻዋ ወርዶ ሽንጧ ላይ ንፋስ እንደሚያዘምው የስንዴ እሸት ዛላ ድንገት ከላይ ወደታች ክንብል ይላል።

‹ጠንካራው ምኞቴ› የሚለውን ክላሲካል ድርሰት ስትጫዎት ከመመሰጧ የተነሣ ከፊት ለፊቷ ቁጭ ብሎ ሚሥላት እንኳን አላየቻውም ነበር። ሙዚቃውን ስትጨርስ ሥዕሉን ሲያሳያት በችሎታው በእጅጉ ተደነቀች። በሁሉም ነገር አቻዋ የሆነ የመከራዋ ደራሽና ታዳጊዋን ያገኘች ሆኖ ስለተሰማት ስሜትዋ ለቀቅ ሲል ውበቷም የጨመረ መሰለ።





ከ15 ቀን በኋላ እንደሚመጡ ስለሚያውቁ እርግጠኛ ሆነው 12ቱን ቀናት እየተወያዩ እየተሳሳቁ ሐዘናቸውን እረስተው የደስታ ጊዜ አሳለፉ።

የእርሷ ከጨለማ ክፍል መውጣት ለእርሱ ተጨማሪ ጉልበትና ዕውቀት ሰጠው። አጋቾቻቸው ሲመጡ የተለየ የሚያስደስትና የሚጣፍጥ ምግብና መጠጥ ለማዘጋጀትም አገዛቸው። ይህም የበለጠ ታማኝነት እንዲያተርፉና ረጅም ጊዜ በዚያው እንዲቆዩ ለመጠየቅ የሚያስችላቸው ነበር።

ሁሉንም በአግባቡ አዘጋጅተው ሲጨርሱ በ13ኛው ቀን ላይ እርሷን ወደ ነበረችበት ቦታ አስገብቶ የሣለውን ንድፍ እየተመለከተ ገመዱን ጠላልፎ ግድግዳውን እንደነበረ አቁሞ ቆያቸው።

ሲመጡ ሁሉም ነገር እንዳስቀመጡት ሲሆን የተለየው ነገር ከዚህ በፊት ሊኖሩት የማያስቡት፣ ቀምሰውት የማያውቁት ምግብና መጠጥ በልዩ አቀራረብ ተዘጋጅቶ መቆየቱ ነበር። እጅግ ደስ አላቸው። አራት ቀናትን በምቾት አሳለፉ። በእርሱም ላይ እምነት ጣሉበት።

"እንደዚህ ዓይነት ምግብ ድጋሜ ትሠራልናለህ? አሁን እኮ ወደ ሰሜን ልንዘርፍ ልንሄድ ነው" አሉት።

"አዎ በደንብ እሠራላችኋለሁ። ነገር ግን በ15 ቀን የምትመጡ ከሆነ አይደርስም። ስለዚህ ምናልባት አንድ ሀያ ቀን ከቆያችሁ ከዚህ የተሻለ አዘጋጅቼ ልቆይ እችላለሁ" አላቸው።

"ምንም ችግር የለም፡ ሀያ ቀን ቆይተን እንመጣለን! ብቻ አንተ ልዩ እንደዛሬው ዓይነት እንድታዘጋጅልን እሺ!" አሉትና ተሰናብተውት ሊሄዱ ሲል፡

"እኔ ምላችሁ እንደው እዚህ ስለሰለቸኝ እስኪ ትንሽ ልሸኛችሁ?" አላቸው።

ሙሉ እምነት ስለነበራቸው እንዲሸኛቸው ፈቅደውለት ከቤቱ ወጥቶ የተራራውን መውጫ ሰርጥ ለማየት ቻለ። ከዚህ በላይ መሄድ ጥርጣሬ ስለሚፈጥር ተሰናብቷቸው ተመለሰ።...."

(የአራተኛው ቀን ትረካ እዚህ ላይ ነበር የቀመው)

"....ከእነርሱ ተሰናብቶ እንደተመለሰ በናፍቆት እየተጫወቱ ያንኑ የግድግዳ ማሰሪያ ገመድ መፍታት ጀመረ። በመኻል

"ልዕልት ሆይ!" አለና "እ..." ሲል

"ምነው ልዑል ሆይ!" አለችው እርሷም እየቀለደች።

"እ.. አለና ሲያቅማማ ቆይቶ "እ... እኔስ በዚህ የጋብቻ ፉክክር ውስጥ ብገባ ምን እንዳመጣ እጠየቅ ይሆን?" አላት።

እውነት ለመናገር መታገቷን አሁን እየወደደው መጥቷል። ከሞት ጋር ሳይሆን ከለምለም ሕይዎት፣ ከብቸኝነት ጋር ሳይሆን ከብዙ ወዳጆች የሚያስንቅ አብሮነት ጋር፣ ከጭንቀት ጋር ሳይሆን ከፍስሓ ጋር የተቆራኘ፣ ዕጣ ፋንታው ባማረ





ስፍራ የወደቀችለት እየመሰለው መጥቷል።

"አው...ለአንተ ሌላ ይሰጥሃል" አለች እየተሽኮረመመች። መላው አካልዋ ከንግግርዋ ጋር እንደ አለንጋ ታጥፎ ይዘረጋል።

"እኮ ምንድን ነው?" አላት አሁንም ገመዱን እየፈታ።

"እ...እጅ በሌለው ሸማኔ የተሠራ፡ ሰማይን የሚያክል ጥበብ ኩታ ካመጣህልኝ!" አለችው። "ጉደኛ ነሽ! አይሆንም ማለት አይሻልም " አላት ፈገግ ብሎ።

"ማን ጠይቅ አለህ? ‹ሳትዋጋ ንጉሥ ቢሉት ግድ ተዋግቼ!፡ አለ ያገሬ ሰው" አለች ዞማ ጸጉሯን እየነሰነሰች።

እንዲህ ውስጠ ወይራ የሆነ ቀልዳቸውን እየተቀላለዱ ገመዱን ፈትቶ ሲጨርስ ምድር ቤት ካለው ሳሎን ቁርሳቸውን በልተው የማምለጫ እቅዳቸውን በቁም ነገር መወያየት ጀመሩ።

ትልቁ ችግራቸው ያሉበትን ቦታና አንጻራዊ አቅጣጫ አለማወቃቸው ነበር። ይሁንና ልዕልቲቱ እንዲህ አለች፡

"የእኔ አባት የምሥራቁ ንጉሥ ነው፣ ምሥራቅ የፀሐይ መውጫ ነው። ስለዚህ አሁን ካለንበት አቅጣጫ የፀሐይ መውጫን ተከትለን ብንሄድ ከሞላ ጎደል ወደ አባቴ ግዛት ልንደርስ እንችላለን። ሌላው ምልክት ሊሆነን የሚችለው ደግሞ የአባቴ ግዛት ማብቂያው ወይም መጀመሪያው ትልቅ ባሕር

አለው፣ መርከቦችም አሉት። ወደዚህ ከተጠጋን በትክክል መድረሳችንን እናውቃለን" አለችው።

ኢጋቾቻቸው በአሁኑ ጉዞዋቸው ወደ ሰሜን ስለሆነ የሄዱት መንገድ ላይ የመገናኘታቸው እድል ጠባብ ስለሆነ ጊዜው ለማምለጥ አመች መሆኑን አመኑበት። ስለዚህ በሚቀጥለው ቀን ለጉዞ የሚያስፈልጋቸውን ምግብ፣ መጠጥ፣ በገንዘብ የሚለወጡ ውድ ጌጣጌጦችን ፣ አልባሳትን እንዲሁም ለሥዕል መሣያ የሚያስፈልጉ ቀላል ነገሮችን ተከፋፍለው ተሸክመው ታግተው ከሚኖሩበት ቤት ወጥተው በማለዳ ጉዟቸውን ቀጠሉ።

እነዚህ ሁለት ወጣት ልዑልና ልዕልት ረጅሙን የተራራ ሰርጥ ወጥተው ደልዳላው ስፍራ ሲደርሱ የምሥራቅን አቅጣጫ ተከትለው ነጎዱ። ብዙ ቀናትን ተጓዙ። እርሱ አብሮ ሲጓዝ የሚውል ቢሆንም ሌሊት ላይ እርሷን ከክንዱ ላይ እቅፎ ከአውሬ መጠበቅ ግዴታው ነበር። ሲደክማት እየተሸከመ፣ ተስፋ ስትቆርጥ እያፅናና፣ አንዳንዴም አቅቷት ማረፍ ስተፈልግ ቁጭ ካለችበት ሜዳ ላይ ከአካባቢው መልክ ዓምድር ጋር አብሮ እየሳለ በሥዕሉ እያስደሰተ ረጅም ጉዟቸውን ቀጠሉ።

የምሥራቁን አቅጣጫ ተከትለው በሄዱ በአምስተኛው ቀን የባሕር ዳርቻ እንደደረሱ ተመለከቱ። ልዕልቷ እጅጉን ፈነደቀች። በደስታ እላዩ ላይ ተጠመጠመችበት።





"ተመልከት! አላልኩህም! አሁን ያባቴ ሀገር ግዛት ደርሰናል። ወደ የብሱ የምንሻገርበት መርከቦች ካገኘን ከአባቴ ግዛት ገባን ማለት ነው። ቢበዛ በሁለትና በሦስት ቀናት ውስጥ መርከብ መምጣቱ አይቀርም። ማንኛውም መርከብ ደግሞ በአባቴ ፈቃድ የሚንቀሳስ ስለሆነ እዚህ ቁጭ ብለን ምልክት አሳይተን መሄድ ብቻ ነው" አለችው ፍንድቅድቅ እያለች።

ከባሕሩ ትይዩ በዛፎች የተከበበ ካንድ ትልቅ ቋጥኝ ሥር ማረፊያቸውን አመቻቹ። ረጅም የእግር ጉዞ ባልሰላ መንገድ ላይ በመጓዛቸው ሁለቱም ተጎሳቁለዋል። አሁን ግን ተሰፋ የደከመውን ገላቸውን አበረታው፣ የጠወለገ ገጻቸውን አወዛው።

ወደማለቂ ከተጠጋው ስንቃቸው ትንሽ ቀማምሰው የደከመ ገላቸውን ለማሳረፍ ጋደም እንዳሉ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰዳቸው።

ከሰዓታት በኋላ እርሱ ቀድሞ ነቅቶ ወደ ባሕሩ ሲመለከት ጀንበሯ የምዕራቡን አቅጣጫ ይዛ እየወረደች ነው። ከወዲህ የጠራው ሰማይ በወዲያ በኩል ቀስተ ደመና ሠርቶ ተአምራዊ ትዕይንት ፈጥሯል። ትዕይንቱ እንዲያመልጠው አልፈለገም። በእንቅልፍ ላይ ያለችውን ተወዳጇን ልዕልት የትዕይንቱ አካል አድርጎ በግሩም ሁኔታ ሣለው።

ድንገት የሆነ ነገር በአእምሮው ብልጭ አለበትና ትዕይንቱ እንዳያመልጣት ቀሰቀሳት። በመጠኑም ቢሆን ከድካም ስላረፈች ከእንቅልፏ ስትነቃ ደስታ ፊቷ ላይ ይንጸባረቅ ነበር።

“ተመልከች! አገኘሁ እኮ!” አላት እርሱም በደስታ ስሜት ወደ ባሕሩ አቅጣጫ ወደ ሰማይ እጁን ዘርግቶ፡

“ምንድን ነው ያገኘኸው?” አለች ግራ ገብቷት

“እጅ በሌለው ሸማኔ የተሠራ፡ ሰማይን የሚያክል ጥበብ ኩታ” አላት በጠራው ሰማይ ላይ በወዲያ በኩል የተዘረጋውን ቀስተ ደመና እያሳዬ፡

ከት ብላ ሳቀችና “የኔ አሸናፊ!” ብላ ዘላ ተጠመጠመችበት።

ይህ የመከራችን ማብቂያ፣ የደስታችን መጀመሪያ፣ የውበትሽ መገለጫ ነው ብሎ የሚለውን አሳያት።

የእርሷም ነፍስ ለጥበብ የቀረበች ስለነበር ሥዕሉን ከልቧ ወደደችው። እጅግ ተደሰተች። ከመከራ ወጥተው ወደ ተስፋ ሲመጡ የበለጠ እየተዋደዱ፣ ተስፋቸው ከፍቅር እያደረሳቸው እንደሆነ ሁለቱም ተገንዝበዋል። እናም እንዲህ አለችው፡

“የአባቴ ሀገር እንደገባን የመጀመሪያው ተግባሬ የሚሆነው በአባቴ ክብር በሀገሬ ሕዝብ ፊት አንተን ማግባት ነው፤ ይኼ የማልቀይረው ቃል-ኪዳኔ ነው!” አለችው።

በርከክ ብሎ እጇን ሳመ።

ቀጠለችና “ከተጋባን በኋላ በታላቅ አጀብ ወደ አባትህ ሀገር ወደ ምዕራቡ ንጉሥ እንሄዳለን። በዚህም የምዕራቡ ንጉሥና የምሥራቁ ንጉሥ በእኔና በአንተ ምክንያት ወደ አንድ ትልቅ ግዛት የሚተባበሩ፣ ከፍ የሚሉ ይሆናሉ” አለችው።





እጅግ ደስ አለው። ፀጉሯን እያሻሸ ጉንጮቿን እየደባበሰ ተስፋ፣ ፍቅር፣ ሕይዎት በልቡ ሲሞላው ታዬው። ይሁንና የያዙት ምግብ እያለቀ መርከቡም የመምጣቱ ሁኔታ አስተማማኝ አለመሆኑ ቢያጠራጥራቸውም ፍቅር ባለበት ተስፋ አለና ተስፋቸው አሸንፎ ከባሕሩ ዳርቻ በተቀመጡ በሁለተኛው ቀን አንድ መርከብ በርቀት ተመለከቱ።

ከወዲያ ወዲህ እየተራወጡ ልብሶቻቸውን አውልቀው ወደ ላይ እያውለበለቡ ለመርከቡ ምልክት ማሳዬት ጀመሩ።

እንደ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ መርከበኞቹ አይተዋቸው ኖሮ ወደ እነርሱ ተጠጉላቸው። በደስታ ጮቤ ረገጡ። መርከቡ እየተጠጋ እየተጠጋ ሲመጣ ከቆመችበት ቋጥኝ ላይ ልዕልቲቱ በግልፅ ታዬች። በዚህ ጊዜ ካፒቴኑ መርከቡን ወደ ዳር ካስጠጋ በኋላ እነርሱ የቆሙበት ቋጥኝ ከመርከቡ እጅግ ከፍ ያለ ስለነበረ በአንክሮ ሲመለከት በልዕልቲቱ ልዩ ውበት አፉን ከፍቶ ቀረ።

ድንገት ተመልሶ ወደ መርከቡ የውስጥ ክፍል ገባና የሆነ ፎቶ ግራፍ ይዞ ተመለሰና ከቋጥኙ ላይ ከቆመችው ሴት ጋር አስተያዬ። በእርግጥ ፎቶ ግራፉ ላይ ያለው ማንነትና ማዶ ከቋጥኙ ላይ ከአንድ ምስኪን ወጣት ጋር የቆመችው ቆንጆ ሴት አንድ ሲሆን እርሷም የምሥራቁ ንጉሠ ነግሥት ልዕልት ነበረች።

ጠፋች ተብላ አገር የሚታመሰላት፣ በእድል ያገኛት ሁሉ ወደ ንጉሡ በክብር እንዲያመጣት የታዘዘላት ልዕልት መሆኗን ሲያረጋግጥ ደስታው ወሰን አጣ። እርሷን በማግኘቱ የሚጠብቀውን ሽልማት ሲያስብ ደስታ አሰከረው።

ጠጋ አለና፡ "ልዕልት እመቤቴ ሆይ! እንችን በማግኘታችን እጅግ ደስ ብሎናል! ከፍ ያለ ክብርም ይሰማናል አለና በትህትና እጅ ከነሳት በኋላ "እባክሽን ከቋጥኙ ወደ እኛ ዝለይ እንይዝሻለን!" አለና ጠንካራ እጆቹን ዘርግቶ ወደ እርሱ እንድትዘል አሳያት።

ልዕልቲቱ ጊዜ አላጠፋችም። ከቆመችበት ቋጥኝ ብ.ድ.ግ አለችና ድንገት ወደ መርከቡ ተወርውራ እራሷን ስትጥል ጠንካራው ካፒቴን በሁለቱ ክንዶቹ እ.ቅ.ፍ አደረጋት። እንደታቀፋት ክንዶቹ ሳይዝሉ ወደ መርከቡ ውስጠኛው ክፍል ይዞ ገብቶ በልዩ ክብር አስቀመጣት።

"ልዕልት ሆይ ወጣቱን ደግሞ ማምጣት ይገባናል!" አላትና ተመልሶ ወጥቶ ሄደ። ነገር ግን ቀጥታ ተመልሶ ወደ ልጁ ከመሄዱ በፊት ወደሆነ ክፍል ገብቶ የሆነ እቃ አውጥቶ ሄደና አሁንም ልክ ልዕልቲቱን በተቀበለበት አኳኋን እጁን ዘረጋና፡

"ዝለል የእኔ ወንድም" አለው።

የምዕራቡ ንጉሥ ልጅም ልዕልቲቱን በሙሉ ኃይሉና በሙሉ ክንዱ ሲቀበላት ስላዩ በሙሉ እምነቱ እርሱም ወደ ላይ





ዝ..ል..ል.. አለና ወደ ካፒቴኑ ሲወረወር ካፒቴኑ ከጎኑ ይዞት የነበረውን ጩቤ ድንገት ላጥ አደረገና ሆዱ ላይ ሽጥ ሲያደርግበት በደም ተነክሮ ወደ ጥልቁ ባሕር ተወረወረ። ካፒቴኑ ጊዜ አላጠፋም ወደ ማዘዣ ክፍሉ ገባና መርከቡ እንዲንቀሳቀስና በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ንጉሥ ዋና ከተማ እንዲቀዝፍ አዘዘ።"......

(የአመሻተኛው ቀን ትረካ እዚህ ላይ ነበር የቆመው)

".....ከደመቀችው የምሥራቁ ንጉሥ ዋና ከተማ ወጣ ብሎ በታላቁ የባሕር ዳርቻ የሚኖሩ አንድ አሳ አጥማጅ አዛውንት ነበሩ። እኚህ አዛውንት ጧሪ ደጋፊ የሌላቸው የዕለት እንጀራቸውን ከባሕሩ አሳ በማጥመድ ግማሹን ለቀለብ የሚተርፈውን ደግሞ ከተማ ወስዶ በመሸጥ የሚተዳደሩ ምስኪን ሰው ነበሩ። እንደተለመደው በምሽት የጣሉትን መረብ ተስፋ አድርገው ከባሕሩ ዳርቻ ካለችው ጎጆ ቤታቸው በጠዋት ወጥተው ወደ ባሕሩ ዳርቻ ወረዱ። ፈጣሪም የዕለት እንጀራቸውን እንዲሰጣቸው ተማምነው መረባቸውን ወደ ዳር ለመጎተትና የታዘዘላቸውን አሳ ለመልቀም!

ከተለመደው ጊዜ ለየት ባለ መልኩ መረቡ ብዙ አሳ ያጠመደ ያክል አቅማቸውን በሚፈትን ሁኔታ ከበዳቸው።

"አይ ፈጣሪዬ የዕለት እንጀራ ብልህ ይኼን ሁሉ ከአቅሜ በላይ የሆነ አሳ ያዝክልኝን?" በማለት እያመሰገኑ እንደገና እንደምንም ያለ የሌለ አቅማቸውን ተጠቅመው መረቡን ወደ ዳር መጎተት ጀመሩ። በሸማግሌ ኃይላቸው የተቻለውን

ያህል ተሟሙተው መረቡን ወደ ዳር ጎትተው መሃል አካባቢ ሲደርስ እንደገመቱትና እንዳሰቡት የሚበላና የሚሸጥ የአሳ ክምችት ሳይሆን ተጠማዞ የወደቀ የወጣት እሬሳ ሆኖ አገኙት። በድንጋጤ ተውጠው ይህንን ወጣት እንደምንም ጎትተው ወደ ባሕሩ ዳርቻ አደረሱት።

ተስፋ የሌለውና የሞተ የመሰላቸውን ዘርግተው ጠጋ ብለው የልብ ትርታውን ሲነኩ ግን በጣረሞት ላይ ያለ ጨርሶ ያልሞተ መሆኑን ተረዱ። እንደምንም ብለው ወደ ዳር አውጥተው ከሳምባው ውስጥ የገባውን ውኃ ደረቱን ጫን ጫን ሲያደረጉ በአፉ ውኃ ቡልቅ ቡልቅ እያለ ወጣ። ከዛም አፋቸውን አፉ ላይ ገጥመው ትንፋሽ እየሰጡ እንዲተነፍስ አድርገው ያለ የሌለ ኃይላቸውን ተጠቅመው እንደምንም ተሸክመው ወደ ጎጇቸው ወሰዱት።

ከጎጇቸው አስገብተው የለበሰውን በማዕበል የተቀዳደደ ልብስ ጨርሰው ሲያወልቁ ጎኑ ላይ በጩቤ የተወጋው ቁስል ብዙ ደም ፈሶት በመጨረሻ ወደ መርጋት ተቃርቦ ተመለከቱ። በሽማግሌ ጉልበታቸው በተቻለ ፍጥነት ወዲያና ወዲህ እየተራወጡ ደሙን በንጹህ ጨርቅ ካጠቡ በኋላ የአሳ ዘይት ጨምረው ግጥም አድርገው በጨርቅ የወገቡን ዙሪያ አሰሩ። እሳት አንድደው ሙቀት እንዲሰማው አደረጉ። ለክፉ ቀን ብለው ያስቀመጡትን የአሳ ቋንጣ አውርደው ሾርባ ሠርተው ከአንገቱ ቀና አደረጉና ትንሽ ትንሽ እንዲቀምስ አደረጉ።





ወጣቱ ሙቀት ሲያገኝና የደም መፍሰሱም ቁሞ በተወሰነም ደረጃ ፈሳሽ ምግብ በመውሰዱ በሦስተኛው ቀን እንደምንም እራሱን ማንቀሳቀስ ቻለ። ቀስ በቀስም እራሱን እያወቀ መጣ።

እራሱን ባወቀበት ሰዓት ሽማግሌውን የት እንዳገኙት ጠየቃቸው። እርሳቸውም የዕለት እንጀራቸውን ለማግኘት ወደ ባሕር ቢወርዱም መረባቸው ውስጥ አሳ ሳይሆን የእርሱን የደከመ ሰውነት እንዳገኙና እንደምንም ተሸክመው ጎጇቸው አምጥተው እንዳተረፉት ተረኩለት።

እንደምንም ብሎ አዕምሮውንና አካሉን እያሰባሰበ ወደ ውስጥ ማሰብ ሲጀምር በመጨረሻ ሰዓት የሆነውን ሁሉ ለማስታወስ ቻለ። በቁስልና በስቃይ ውስጥ ሆኖ ከተወዳጅ ልዕልቱ፣ ከመከራ ካወጣት ፍቅረኛው ጋር የተለያየበትን የመጨረሻውን ቅጽበት አስታወሰ። በአባቷ አገር ግዛት ውስጥ በሚኖር መርከብ እርሷን በክብር የተቀበላት ካፒቴን እርሱን ግን በጩቤ ወግቶ ባሕር ውስጥ እንደጣለው ተረዳ።

ይሁንና እርሱ ወደ ባሕር ተወግቶ ሲጣል ልዕልቲቱ ተከታትላ ልታድነው ሲገባት በዚያ ሁኔታ ጥላው በመሄዱ በእጅጉ ተበሳጨ። ሐዘን ልቡን ሰበረው። ፍቅር ወደ ጥላቻ ተቀየረ፣ ተስፋ በጥልመት ተሞላ። ነገር ግን ሕይወት ነውና መቀጠል ነበረበት።

ሰውነቱ እያገገመና እየዳነ በሄደ ጊዜ ሽማግሌው ስለማንነቱ እንዲነግራቸው ጠየቁት። እርሱ ግን ምንም ነገር መናገር አልፈቀደም። ላደረጉለት መልካም ውለታ አመስግኖ ምንም መሄጃና መምጫ የሌለው ተራ መናኝ በመሆኑ ቀሪ ዘመኑን ከእርሳቸው ጋር ማሳለፍ እንደሚፈልግ፣ ላደረጉለት በጎ ሥራም በጉልበት ከእርሳቸው እርሱ ስለሚሻል የአሳ ማጥመዱን ሥራ በርትቶ በመሥራት ኑሯቸውን መለወጥ እንደሚችል ቃል ገባላቸው። በዚህ መሠረት በየቀኑ ወደ ባሕር እየወረደ አሳ ማጥመዱን ሥራዬ ብሎ ተያያዘው።

እድል እና በረከት ሆኖለት በየቀኑ የአሳ መረብ በጣለ ቁጥር በርካታ አሶችን ይይዝ ነበር። ይህም ከምግብ ፍጆታቸው አልፎ በጣም ብዙ ስለሚተርፉቸው ሽማግሌው ወደ ከተማ እየወሰዱ እንዲሸጡ አደረገ። እርሱ ግን ከተማ መሄድ ፈጽሞ ፍላጎት የለውም ነበር።

በዚህ ሁኔታ ለሳምንታት ኑሯቸውን ሲገፉ በሚገርምና በማይታመን መጠን ብዙ ገንዘብ እያገኙ መጡ። ሽማግሌውም ደስተኛ ነበሩ። ለእርሱም ለእርሳቸውም ልብስ ይገዛሉ፣ ከአሳ በተጨማሪ ሌሎች ምግቦችን ይገዛሉ፣ የቤት ኑሯቸውን ሁሉ አሻሻሉ።

አንድ ቀን እንዲህ አላቸው "አባቴ እስኪ እባክዎት ከተማ ሲሄዱ የሥዕል መሳያ ቡርሽና ቀለም ገዝተውልኝ ይምጡ" አላቸው።





እንደ ልጃቸው የሚያዩትና ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸው በረከት መሆኑን አምነው ስለተቀበሉ በደስታ የጠየቃቸውን የሥዕል መሳያ ወረቀትና ቡርሽ ቀለም ገዝተውለት መጡ።

ከአሳ ማጥመድ ውጭ ባለው ጊዜ የመጀመሪያ ሥዕሉን አሐዱ ብሎ መሳል ጀመረ። ሥዕል ሐዘኑንና የጎዳውን ነገር ምሥጢሩን የሚገልፅበት ብቸኛው መንገዱ ነበር። በአብዛኛው መልክዓ ምድርን፣ ተፈጥሮን ወይም አበቦችን፣ ወንዝና ተራሮችን ፣ ዛፎችን ቢስልም በመሃል ግን የራሱን የሕይወት ገጠመኞች የሚመለከቱ ጥልቅ ምሥጢር ያላቸው ሥዕሎችን በተለየ ሁኔታ ይሥል ነበር።

የመጀመሪያው ሥዕል ከእናቱ ጋር መንገድ ዳር ቁጭ ብሎ ንጉሡ በሰረገላ ሲያልፍ የሚያሳየው ትዕይንት ነበር። ከብዙ ሥዕሎች መካከል ይህ ሥዕል ተደባልቆ ተቀመጧል።

በሚቀጥለው ጊዜ ሽማግሌው ወደ ገበያ ሲሄዱ እንዲህ አላቸው፦

"እስኪ ከንጉሡ ከተማ ምን እንደሚወራ፣ ምን አዲስ ነገር እንዳለ ጠይቀው ይምጡ" አላቸው።

"አይ ልጄ! በደመቀው ባሸበረቀው የንጉሥ ከተማ፣ ምን የማይደረግ፣ ምን የማይወራ ነገር አለ? ግን ለእኔና ለአንተ ምን ይሠራል ብለህ ነው?" አሉት።

ቢሆንም "ጠይቀውልኝ ይምጡ?" አላቸው።

እርሳቸውም በጠየቃቸው መሠረት አሳቸውን ሸጠው ሲመለሱ ከተማ ውስጥ የሚወራውን አፍለኛ ወሬ ይዘውለት መጡ።

"ምንድን ነው አፍለኛው ወሬ?" አላቸው።

"ሸረ የሚገርም እኮ ነው የኔ ልጅ" አሉና " የንጉሡ ልጅ ልዕልቲቱ ጠፍታ ይገርምሃል አገር ሲጨነቅና ሲታመስ ነበርና፤ አንዱን መስፍን አግብታ መንግሥቱን ትወርሳለች ሲባል በመጥፋቷ ንጉሡም በዚህ እጅግ አዝነው ብዙ አደጋ ላይ ደርሰው ነበረ።" ብለው ሊቀጥሉ ሲሉ

"እና ምን ሆነች?" አለ ድንግጥ ብሎ

"እየውልህ በደኅና ተገኘች! እንዲያውም ፈልጎ ያገኛት እርሷን አግብቶ የመንግሥቱ ወራሽ ይሆናል ብለው አውጀው ኖሮ... ይኸውልህ አንድ መርከበኛ አገኛት ተብሎ አሁን ንጉሡም ቃላቸውን ጠብቀው ለዚሁ ሊድሩለት የሰርግ ቀን ተቆርጦ አገሩ በሙሉ እንዲደግስ መዋጮም አድርጎ ትልቅ ፈንጥዚያ እንዲደረግ ተብሎ አገሩ በሙሉ በደስታ ላይ ነው።" አሉና ሳያውቁት እርሳቸው ደግሞ ሌላ የቂጭት ጩቤ ሰኩበት።

" እና.." ቀጠለ " ልጄ በጣም ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው። ንጉሡም ደስ ብሏቸዋል አገሩም ደስ ብሎት ይኸው ለድግስ እየተዘጋጀ ነው "አሉት እርሳቸውም ደስታው ተጋብቶባቸው።

ደጉና አዳኙ አዛውንት ይኼ በጎ ታሪክ መስሏቸው በስሜት ሲያወሩለት ለእርሱ ግን ልቦናው ውስጥ በእጅጉ የሚሰነቀር ትልቅ ጦር ነበርና ክፉኛ ተጎዳ።





"በፈተና ውስጥ አልፈን እኔ ሳልጠይቃት ቀድማ ቃል-ኪዳን ሰጥታኝ ስታበቃ እንሆ እኔን በጩቤ አስወግታ ባሕር ላይ አስጥላ እርሱን ለማግባት በዚህን ያክል ጥድፊያ መወሰኗ ምን አይነት አውሬ ብትሆን ነው?" ብሎ እጅግ ተበሳጨ።

በውስጡ አንዳች የሚገፋው የበቀል ስሜት ተጠነሰሰ። ይሁን እንጂ ሁሉን ችሎ የአሳ ማጥመድ ኑሮውን ቀጠለ። ሥዕሎቹንም እንደዚሁ። የተለመደና ምንም ታሪክ የሌላቸው ሥዕሎችን ይስልና ቀጥሎ ‹ከወንድሙ ጋራ ለአደን ሲወጡ የሚያሳይ አንድ ሥዕል› ሳለ።

በሚቀጥለው ሳምንትም ለገበያ ሲሄዱ እንዲሁ ምን አዲስ ነገር እንዳለ እንዲጠይቁለት አሳሰባቸው።

አዛውንቱም "አይ የኔ ልጅ እንዲያው ወሬ ምን ያደርጋል ብለህ ነው?" ቢሉም ግዴለም ይጠይቁ ስላላቸው በከተማው ውስጥ የሚወራውን ወሬ አድምጠው ተመለሱ።

በከተማው ውስጥ የሚወራው አዲሱ ወሬ ከበፊቱ ደስታ የራቀ ሐዘን እንደሆነ ነገሩት። ንጉሡ በልጃቸው መገኘት ደስ ብሏቸው ፈልጎ ላመጣላቸው መርከበኛ ለመዳር ሽር ጉድ በሚሉበት ወቅት ልዕልቲቱ ግን በአዕምሮ መታወክ ታማ በቤተ-መንግሥት እልፍኝ ውስጥ ተዘግታ እንደምትውል ማንንም ማነጋገር እንደማትፈቅድ ሰማ።

በዚህ ጊዜ ልቡናው አንዳች ነገር ተጠራጠረ። ልዕልቲቱ ከአቅሟ በላይ የሆነ ነገር እንደገጠማት፣ ሆኖም ይኼን ነገር መፍታት አለመቻሏ ግራ አጋባው። ቢሆንም አሳውን እያጠመደ፣ ሥዕሉን እየሳለ ኑሮውን መግፋት ቀጠለ።

ሦስተኛው ሥዕል እነሆ ጫካ ውስጥ ከወንድሙ ተለይቶ በጠፋበት ወቅት ከሁለት ቀናት በኋላ በርሃብና በድካም ውስጥ ሆኖ ከተኛበት ዛፍ ሥር ዙሪያውን በሽፍቶቹ ተከቦ ጎኑን በጦር ተወግቶ ሲቀሰቅሱት የሚያሳየውን ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ቤተ መንግሥት ውስጥ ልዕልቲቱ ማንንም ማነጋገር የማትፈቅድ፣ ምንም ነገር የማይጥማት፣ የማትናገር፣ የማትጋገር ሆና ቁጭ ብላለች። በቤተ-መንግሥት እልፍኝ ውስጥ ካለው ብዙ ነገር ሁሉ ቀልቧን የሚስብ ነገር ቢኖር ግድግዳ ላይ ያሉ ሥዕሎች ብቻ ናቸው። ሥዕሎቹን በእጅጉ አተኩራ ትመለከታለች። ከዛ ውጭ የሚበላም፣ የሚጠጣም፣ የምትወደው ሙዚቃም፣ የምትወዳቸው ቤተሰቦቿም እንዳቸውም ትኩረቷን/ቀልቧን አይስቡትም። ከማንም ጋር መነጋገር ጨርሶ አትፈቅድም።

በአገሩ ያሉ ሁሉ ባለመድኃኒቶችና አዋቂዎች በሙሉ ተፈልገው እንዲያክሟት እንዲረዷት ቢደረግም መፍትሄ የሚሰጥ አልተገኘም። ነገር ግን አንድ ፍንጭ ታይቷል። ሥዕል ቀልቧን እንደሚገዛው።





ስለዚህ የቤተ መንግሥቱ ባለሟሎች፣ መኳንንትና መሳፍንት መክረው ምናልባት ሥዕል አዕምሮዋን የሚሰበስበው ከሆነ ደኅና ደኅና ሥዕል በከተማው ያሉ ሠዓሊያን እየሣሉ እንዲያመጡ ቢደረግ ይሻላል ተባለ።

በዚህ መሠረት በከተማው ውስጥ ያሉ ሠዓልያን በሙሉ እየሣሉ እንደዚሁም መኳንንቱና መሳፍንቱ አውቀዋለሁ ከሚል ጥበበኛ ሠዓሊ እየሄደ እያሣለ ሥዕል ማጉረፍ ጀመረ። ይሁንና ሥዕሎቹን ቀና ብላ የምታያቸውና ትኩረት የምትሰጣቸው ቢሆንም አይታ ወዲያው ትተዋቸዋለች።

በአጋጣሚ አንደኛው መኳንንት ወደ እኒያ አዛውንት አሳ አጥማጅ ሰፈር ለሽርሽር ሲመጣ አዛውንቱ ጎጆ አካባቢ ሥዕሎች ተደርድረው አየና ደጅ ላይ የነበረውን ወጣት፣

"እስኪ ሥዕሎችን አሳዬኝ?" አለው። ወጣቱም በቀለም ያሸበረቁ የተለያዩ ሥዕሎችን ከራሱ ምሥጢራዊ ታሪክ ካላቸው ሁለቱ ሥዕሎች ጋር ጐን ለጐን አድርጐ አሳዬው።

"አንተ ነህ ሠዓሊው?" አለው

"አይ አባቴ ነው" አለ በርቀት ባሕሩ ዳር መረብ የሚጥሉትን አዛውንት እያሳዬ።

መኳንንቱም "እነዚህን ሥዕሎች ልግዛህ?" አለው በቀለም ያሸበረቁትን የአበቦችና የወንዝ ዳርቻ የሚያሳዩትን ሥዕሎች ለይቶ።

“ለይቼ እንኳን አልሸጥም። ከገዙ አንድ ላይ ይግዙኝ?” አለ።

“ግዴለም ይሁን” አለና አንድ የሚያምር አበባ ያለው ሥዕል መንገድ ዳር ተቀምጠ ከእናቱ ጋር ከሚያሳየው ሥዕል እና ከወንድሙ ጋራ ለአደን ሲወጡ የሚያሳይ አንድ ሥዕል ጋር በአንድ ላይ ገዛው። ያ መኳንንት ሁሉንም ሥዕሎች ወስዶ ቤተ-መንግሥት አደረሰ። እንደተለመደው የቤተ-መንግሥቱ አጋፋሪዎች እነዚህን ሥዕሎች ወስደው ከልዕልቷ ፊት አስቀመጡ።........"

(የአጽአተኛው ቀን ትረካ እዚህ ላይ ነበር የቆመው)

"........ከሁሉም ሥዕሎች መካከል ሁለት ሥዕሎች ላይ የበለጠ ትኩረት አደረገች። የሚያምሩ አበቦች፣ ፏፏቴና ወንዝ ተራራ የሚያሳዩት ሥዕል ሳይሆን አንዲት መንገድ ዳር የተቀመጠች የእኔ ቢጤ ከህፃን ልጅ ጋራ ከፊቷ የንጉሥ ሰረገላ ቆሞ ያለውንና ሁለት ወጣቶች ለአደን ሲወጡ የሚያሳይ ሥዕሎችን በልዩ አድናቆት ስትመለከተው ሲያዩ ማንም ምሥጢሩ ሊገባው አልቻለም።

እነዚህን ሥዕሎች ለይታ ስታስቀምጥ ጊዜ ይኼ መኳንንት ያመጣው ሥዕል አንዳች ነገር እንዳለው ተረዳቸውና አሁንም በድጋሚ ሥዕል እንዲያመጣ ታዘዘ።





መኳንንቱም ተመልሶ ወደዚያ አዛውንት ጎጆ ሲሄድ ያንኑ ወጣት አገኘውና፡

“እስኪ ሌላ ሥዕል ደግሞ ስጠኝ” ሲለው፡ አሁን ደግሞ ከወንድሙ ጋር ተለያይቶ በሽፍቶች ተከቦ የሚያሳየውን አሁንም ከሌላ ሥዕል ጋር ቀላቅሎ በከፍተኛ ዋጋ ሸጠ።

መኳንንቱም እወደድ ባይ ስለነበረ ብዙ ዋጋ ከፍሎ ይሄን ሥዕል ወሰደ። ስለዚህ ወጣቱ የሥዕሉ መልዕክት እየደረሰ እንደሆነ ስለገባው አሁንም ተከታዩን ሥዕል ሳለ። ተከታዩ ሥዕል ደግሞ በዛ ረባዳ ሥፍራ ላይ ታስረውበት የነበረው ቤት ነበር። ይህን ሥዕል ስሎ ከሌሎች ሥዕሎች ጋር ቀላቅሎ አሁንም በከፍተኛ ዋጋ ሸጠ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ብዙ መኳንንት በየቦታው ሥዕል እያሣለ ያመጣ ነበር። ግን ሥዕሎቹን ታይና ከእነዛ ሁሉ ሥዕሎች አሁንም የልጁን ብቻ መርጣ መደርደር ያዘች። በቤተ መንግሥቱ እስካሁን ስለጉዳዩ ግልፅ የሆነለት ሰው የለም።

ነገር ግን ልጁ ሥዕሉን ቀጥሏል። የታሰረችበትን ክፍል የሚያሳይ እንደዚሁም ቁጭ ብላ ፒያኖ ስትጫወት ከረጅም ፀጉሯ ጋራ የሳለውን ሥዕል አሁንም ከሌሎች ሥዕሎች ጋር ቀላቅሎ በከፍተኛ ዋጋ ሸጠ።

ያስጠጉትና ሕይወቱን ያዳኑት አዛውንት እርሳቸውም በማያውቁት ምሥጢር ከፍተኛ ሐብት ወደ እርሳቸው እየጎረፈ እንደሆነ ተረድተዋል። ልጁም በማይታመን መጠን የሥዕሉን ዋጋ እያናረ ሄደ። እንዲያውም ሌሎች መኳንንቶች ይኼ መኳንንት የሚያመጣው ሥዕል ላይ ትኩረት እንደምታደርግ ስላወቁ ወደዚህ ልጅ ይጎርፉ ጀመር። ስለዚህ ዋጋውን እያስወደደ ከፍ እያደረገ ብዙ ሃብት መሰብሰብ ያዘ።

ከዚህ ቀጥሎ የተሳለው ሥዕል ከታገቱበት አምልጠው የአባቷ ባሕር ዳርቻ ሲደርሱ በፀሐይ መግቢያ ከባሕሩ ጋራ ስለውበቷ መታሰቢያ የሣለው ነበር። ይህ ሥዕል በከፍተኛ ዋጋ ከመሸጡም በላይ ልዕልቲቱን ከነበረችበት የዝምታ አዘቅት ውስጥ ያወጣ ነበር።

"የዚህን ሥዕል ሠዓሊ ማግኘት እፈልጋለሁ?" አለች። መኳንንቱ ሁሉ ተተራመሰ። መጀመሪያ ከልጁ ሥዕሉን የገዛው መኳንንት ተጠርቶ መጣና ከየት እንዳገኘው ሲጠየቅ፡ "አይ አንድ አዛውንት አሳ አጥማጅ ጎጆ ደጅ አንድ ወጣት ነው የሚሸጥልኝ። እርሱ ለመሳሉም እርግጠኛ አይደለሁም" አለ።

‹አይ ይኼ የህመሟ ምልክት ነው እንጂ አንድ ባሕር ዳርቻ የሚኖር አሳ አጥማጅ አዛውንት ከልዕልቲቱ ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም› በማለት ነገሩን ለማለባበስ ሞከሩ። እርሷ ግን ብትጮህም የሚሰማት አጣች። እና ሥዕሎቿን ደርድራ በአግባቡ አስቀምጣ ልጁን ማግኘት ባትችልም በሥዕሎቹ





ለመጽናናት ስትል "ቢያንስ እሽ ሥዕሉን ማምጣት አታቋርጡብኝ" ብላ ተማጸነች።

ፈጽሞ ባያድናት እንኳን ቢያንስ የሚያረጋጋት ሥዕሉ መሆኑ ስለታወቀ መምጣቱ ቀጠለ።

የመጨረሻዎቹን ሥዕሎችና እጅጉን ውድ ዋጋ ያወጡትን ሁለት ሥዕሎች ማለትም የመርከቡ ካፒቴን እርሷን ሲቀበል በክንዱ ሲያሳርፍ የሚያሳየውንና እርሱ ልክ እንደእርሷ ሲዘል በጩቤ ሲወጋው የሚያሳየውን ሥሎ፤ የእርሷን ሥዕል በመጀመሪያው ሳምንት ላከ። ልዕልቲቱ እጅግ ተደሰተች። ይኼ እውነተኛ እርsሱነቱን የሚያረጋግጥላት በመሆኑ መልበስ ማጌጥ ጀመረች። ሥዕሎቹን አሁንም በጥንቃቄ ማስቀመጥ ጀመረች። ይሁንና አሁንም ከልጁ ጋር የሚያገናኛት ማንም እንደሌለ ተረድታለች።

በሌላ በኩል ወጣቱ ግን ከሥዕሉ ሽያጭ ያጠራቀመው ከፍተኛ ገንዘብ ስለነበረ የሕይወቱን አዳኝ የሽማግሌውን ሕይወት መለወጥ ስለነበረበት ባገኘው ከፍተኛ ገንዘብ ከተማ ውስጥ ትልቅ ቤት ገዛ። ትልቅ መሬት አደራጀ።

ከዚህ ቀጥሎ መኳንንቱ ሁሉ እየተገዳደረ የመጨረሻውን አስደናቂ ሥዕል በጩቤ ሲወጋ የሚያሳየውን ትዕይንት በከፍተኛ ዋጋ ገዝተው ወሰዱ። ልዕልቲቱ ይህን ስታይ ግን እንደገና መሬት ላይ ተዘረረች። በእጅጉ አዘነች። መጨረሻ ተስፋ ቆረጠች። ቤተሰቡም ተስፋ ቆረጠ። ከሁለት ቀን በኋላ

ግን እንደገና በጥልቅ ስታስበው አንድ ጥያቄ በአእምሮዋ ተጫረ፡

‹በጩቤ ተወግቶ ሕይወቱ አልፎ ቢሆን ኖሮ ይህን ሥዕል ማን ይሥለው ነበር?› የሚለው ነው። ‹በትክክልም ይህ ሰው በሕይወት አለ!› የሚል ድምዳሜ ላይ ደረሰች። እናም አባቷን አስጠርታ፡

“አባዬ በእኔ የተነሣ ትልቅ ሐዘን ላይ እንዳለህ አውቃለሁ፣ የእኔን ክብርና ማዕረግ እንደምትፈልግም አውቃለሁ፣ ሙሉ ጤነኛ ሁኜ ደስ ብሎኝ እንድኖር የአንተም ፈቃድ ይፈፀም ዘንድ ግን ለአንድ ልጅህ የምጠይቀውን አድርግልኝ?” አለቻቸው።

ንጉሡም “ምንድን ነው?” አሉ።

“መጀመሪያ ቃል ግባልኝና?” አለች

“እሺ ቃል ገባሁልሽ” አሉ በመረጋጋቷ ደስ ብሏቸው።

“በመጀመሪያ የትም ይሁን የትም ይሔን ሥዕል የሣለውን ሰው ከዚህ ቤተ መንግሥት እንድታመጣልኝ፣ ቀጥሎ አገኘኋት ብሎ ወደ አንተ ያመጣውን የመርከብ ካፒቴን እርሱንም ከቤተ መንግሥት እንድታመጣልኝ እፈልጋለሁ” አለች።

ንጉሡም ከብዙ ወራት በኋላ በተረጋጋና በፍፁም ልቦና እንዳነጋገረችው ስለገባቸው ይህ ሠዓሊ ካለበት ተፈልጎ እንዲመጣ አዘዙ።





በሌላ በኩል ወጣቱ ለሽማግሌው ቀደም ብሎ እጃቸውን ይዞ፡

“ማንም ሰው እነዚህን ሥዕሎች የሣለው ማነው ብሎ ቢጠይቀዎት እኔ ነኝ ይበሉ” ብሏቸው ነበር

“እማይሆነውን” ቢሉትም

“ግዴለም እሺ ይበሉኝ” ብሎ አሳምኗቸዋል።

ያ ቀደም ብሎ ሥዕሎቹን የገዛው መኳንንት በወታደር ታጅቦ በጠዋት አዛውንቱ ጎጆ ደረሰና ተጣራ።

አዛውንቱ ወደ ደጅ ወጥተው እጅ ሲነሱ መኳንንቱም እየተጀነነ ሰላምታ ሰጣቸውና፡

“አባቱ! ወደ ቤተ መንግሥቱ እንዲመጡ ንጉሡ አዘዋል” አላቸው።

አዛውንቱ በጣም ደነገጡና “ምን አጠፋሁ ጌታዬ?” አሉ ቤተ መንግሥት ድረስ የሚያስጠራ ምንም ማዕረግም ጉዳይም ስለሌላቸው።

“ግዴለም ለበጎ ነው። ሥዕሎችዎን ስለወደዱ ሊሸልምዎት ነው” አላቸው ፈገግ ብሎ።

“እኔ እኮ አይ....” ብለው ሳይጨርሱት ወጣቱ ድንገት ከቤት ወጣና፡

“ጌታዬ ለመዘጋጀት ትንሽ ደቂቃ ቢፈቀድልን?” አለና አስፈቅዶ ወደ ቤት ይዟቸው ገባ።

“እነዚህ ሰዎች እኮ የሚሉት ‹ሥዕሉን የሣለው ማነው› ብለው ንጉሡ ጠይቀው እሸልመዋለሁ እሾመዋለሁ ስላሉ ነው የመጡት” አሉ ግራ ተጋብተው

“ገብቶኛል እኮ። ቀደም ብዬ እንደነገርኩዎት እባክዎትን ‹እኔ ነኝ የሣልኩት› ይበሉና እርስዎ ይሂዱ። እኔ ለዚህ አልታደልኩም!” አላቸው ክፍት ብሎት።

በእርሱ ግምት የተፈለገው ለሥራው ሽልማት ቢጤ ተሰጥቶት በዚያውም በሰርጓ ዕለት በእንግድነት እንዲገኝ ታስቦ ይሆናል። ይህ ለእርሱ ደግሞ የበደል በደል ነበር።

“እባክህ ልጄ እንዲህ አትበለኝ። ኑሮዬን የለወጥከውን ፈጣሪ የሰጠኝን ልጄን ያንተን ድካም ልወስድ አልችልም። የሣልከው አንተ ነህ! ክብርና ማዕረግ ሹመትም ሽልማትም የሚገባህ አንተ ነህ” አሉት ፈርጠም ብለው።

“የሚወዱኝ ከሆነ ይህን ብቻ አድርጉልኝ።፡ ይሂዱና እኔ ነኝ ብለው የሚሰጠዎት ነገር ካለ ተቀብለው መምጣት ብቻ ነው፡ አለቀ!” ብሎ ሲለማመጣቸው አንጀታቸው አልችል አለና እሺ አሉት።

በቅርቡ ቤት ለመግዛት ከተማ ሂዶ ሳለ የገዛላቸውን አዲስ ልብስ አልብሶ ከመልእክተኞቹ ጋር ሸኛቸው።





ደጉ አዛውንት ታጅበው ቤተ መንግሥት ደረሱና ወደ ንጉሡ እልፍኝ ገብተው እጅ ነሡ።

ንጉሡም፡

“ይህን ሥዕል የሣሉት እርስዎ ነዎት?” አሏቸው።

“አዎን ንጉሥ ሆይ እኔ ነኝ የሣልኩት” አሉ ውስጣቸው እየተሳቀቀ።

“መልካም! ይበሉ ልጄ ትፈልገዎታለች ይከተሉኝ” አሉና ንጉሡ አስከትለዋቸው ወደልጃቸው እልፍኝ ገቡ።

ልጅቱም ድንገት ብድግ ብላ “ምንድን ናቸው?!” አለች ግራ ተጋብታ።

“ልጄ! እኚህ አዛውንት ናቸው የምትወጃቸውን ሥስዕሎች የሣሉት” አሉ የልጃቸው መዳን የቀረበ መስሏቸው በተስፋ ፈገግ ብለው።

“አባባ እርስዎ አልሣሉትም! እርስዎ እንዳልሣሉት አውቃለሁ! በፈጠረዎት የሣለውን ያምጡልኝ” አለችና እንባዋን እያዘራች ከእግራቸው ሥር ተንበረከከች።...” አለና በረጅሙ ተንፍሶ ዝም አለ።

"ከዚያስ?!" አልኩት ልቤ ጥልጥል ብሎ።

"ደግሞ ነገ እንቀጥላለን" አለኝ።

"አሁን እኮ ለሰባተኛ ጊዜ ልታሳድረው ነው። ለምንድን ነው ልቤን የምትሰቅለው?" አልኩት ምርር ብዬ።

"ስማ ጓደኛዬ! ለምንም ነገር ከመጠን በላይ አትጓጓ። በዚህ ዓለም አምሮን የሚቀር ብዙ ነገር አለ። ሕይዎት ደግሞ እኔ እንዳወራሁልህ ጣፋጭ ተረት አይደለችም መራራ እውነት እንጂ" አለኝ ኮስተር ብሎ። ከዚያ በፊት እንደዚህ ኮስተር ብሎብኝ፣ መክሮኝም አያውቅም ነበር። ቆየና፡

"ለማንኛውም ነገ ደግሞ ወክ እናደርግ የለ? ነገ እጨርስልሃለሁ" አለኝ እያፌዘብኝ።

በማግስቱ ሀገር ድብልቅልቁ ወጣና በየፊናችን ተለያየን።


እስካሁን ድረስ ተረቱን ለምን እንደማልረሳውና መጨረሻውን ለማወቅ እንደሚያጓጓኝ ለራሴ ይገርመኛል። እርሱ እንዳለው ሕይወት ጣፋጭ ተረት ሳትሆን መራራ እውነት መሆንዋን ከነገረኝ ማግስት ጀምሮ ተረድቻለሁ።


ካገኛችሁት ግን፡

<በቂ መራራ እውነት ተግቻለሁ፡ ጣፋጩን ተረት ግን አልጨረስክልኝም እኮ> በሉልኝ ያንን ልብ እንጠልግዶ!



# የደራሲው የቀደሙ መጻሕፍት







ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ. ማኅበር
+251 111 565 352

ዋጋ፡ 100.00 ብር